ኙ ሰዎች ለእግዚአብሔር የሚሰጡት «ስጦታ» አላቸው:: «ወጣቱ» ለእግዚአብሔር የሚሰጠው ጉልበትና ጉጉት አለው:: ሐዋርያት ሁሉ ክርስቶስ በመረጣቸው ጊዜ ታዳጊዎች ወይም በ20ዎቹ የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ወጣቶች ነበሩ:: ሥራው ብዙ በመሆኑ የወጣቶችን ተሳትፎ ይጠይቅ ነበር:: ስለሆነም ኢየሱስ ጊዜ ወስዶ 12ቱን ወጣቶች በመሪነት አሠልጥኗቸዋል:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ወጣቶችን መናቅ የለባቸውም፤ ይልቁንም፣ የአገልግሎት ዕድሎችን በመስጠት ጉልበታቸውን ለእግዚአብሔር ክብር እንዲያውሉ ማስቻል አለባቸው:: ለወጣቶች መስጠት ያለበት እንደ ጽዳት ዓይነት የጉልበት ሥራ ብቻ መሆን የለበትም:: ወደ ዋና ዋና አገልግሎቶችም ዘልቀው እንዲገቡ ልናበረታታቸው ይገባል:: ወጣቶች በምስክርነት፣ በማስተማርና መጠነኛ ኃላፊነቶችን በማስተዳደር ሊያገለግሉ ይችላሉ:: ጉልበታቸውን ለእግዚአብሔር መንግሥት እንዲያውሉ ማስቻሉ ተገቢ ነው:: ሰሎሞን እንዳለው፣ ወጣቶች አስኪያረጁ ድረስ ከሚጠብቁ፣ በጉብዝናቸው ወራት እግዚአብሔርን ማገልገል አለባቸው:: (መክ. 12:1ን አንብብ::) እንደ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ወጣቶች ለእግዚአብሔር ክብር የሚሰጡትን ጉልበትና ፍላጎት መጠቀም አለብን:: እግዚአብሔር በመሪነት ችሎታቸው አድገው የነገውን የአመራር ኃላፊነት የሚረከቡትን ሰዎች የሚያስነሣው ከእነዚሁ ወጣቶች መካከል ነው:: «ሴቶች» በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከወንዶች በበለጠ በመሥዋዕትነት የሚያገለግሉ ታታሪ ሠራተኞች ናቸው:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሴቶችን የማገልገል ፍላጎት ለእግዚአብሔር ክብር መጠቀም አለባቸው:: በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሴቶች ከወንዶች በላይ ውጤታማ የሚሆኑባቸው ብዙ የአገልግሎት ዘርፎች አሉ:: ልጆችን ማስተማር፣ ለሴቶች መመስከር፣ ለወንጌላውያን ገንዘብ ማሰባሰብ፣ ጸሎት፣ ወዘተ. . . በሴቶች ቢሠራ የበለጠ ውጤታማ ይሆናል:: ሴቶቿ ስተለያዩ ፕሮግራሞች ምግብ ከማብሰል ያለፈ ሚና እንዳይጫወቱ የምትከላከል ቤተ ክርስቲያን ደካማ እንደ ሆነች ትኖራለች:: «አረጋውያን» ለአገልግሎት የሚሰጡት ጊዜና ልምድ አላቸው:: እነዚህ ሰዎች ጡረታ የወጡ ወይም በልጆቻቸው የሚጦሩ ሊሆኑ ይችላሉ:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች



የአረጋውያንን በቂ ጊዜና ተሞክሮ ለእግዚአብሔር ክብር ለማዋል መጣር አለባቸው:: አስተዋይ መሪ ሁልጊዜም ለሰዎች የአገልግሎት ዕድሎችን ለመስጠት የሚፈልግ ነው::

> 33ኛ ጥያቄ:- ባለፈው ሳምንት ለቤተ ክርስቲያን ያዘጋጀኸውን ዕቅድ እውጣ:: የቤተ ክርስቲያን መሪ ካልሆንክ፣ የቤተ ክርስቲያን የሽማግሌዎች ሰብሳቢ ነኝ ብለህ አስብ:: ከላይ የተጠቀሱትን ነጥቦች በመጠቀም፣ እንዴት ለሰዎች አገልግሎቶችን እንደምትወክል አብራራ:: ሀ) የትኞቹን የተግባር እርምጃዎች ትወስዳለህ? ያንን ተግባር የመረጥከው ለምንድን ነው? ለ) የትኞቹን ተግባራት ለሌሎች በውክልና ትሰጣለህ? ይህንን ሥራ ሌላ ሰው እንዲያከናውን የፈለግከው ለምንድን ነው? ሐ) ኃላፊነትንና ሥልጣንን እንዴት እንደምትወክል ግለጽ:: መ) ለሥራው ተጠያቂነትን የምትመሠርተው እንዴት ነው?

አምስተኛ ቀን:- የዚህን ሳምንት ትምህርት ክልስና ለሳምንታዊ ስብሰባ ተዘጋጅ::

## ሳምንታዊ ስብሰባ

የውይይት ጥያቄዎች:-

1. ሀ) አብዛኞቹ መሪዎች ከመጠን በላይ ሠርተው መዛላቸውን ይገነዘባሉ? የሚዝሉት ለምንድን ነው? ለ) ከአራቱ የውክልና አማራጮች አብዛኞቹ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሚጠቀሙት የትኛውን ነው? ሐ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ተጨማሪ የአመራር ኃላፊነቶችን ከመቀበላቸው በፊት፣ «እንፈጽመዋለን ብለን የተስማማንበትን የአመራር ኃላፊነት በሚገባ መወጣታችንን እግዚአብሔር በኃላፊነት ይጠይቀናል» የሚለውን እውነታ ማስታወሳቸው ጠቃሚ የሚሆነው ለምንድን ነው?

2. ሀ) ክህሎት ያለው ውክልና የሚያስገኛቸው ስድስት ጥቅሞች ምንድን ናቸው? ለ) መሪዎች የውክልናን ክህሎት ቢያውቁ በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ እንዴት መሻሻል ሊመጣ ይችላል?

3. ሀ) ዮቶር የእግዚአብሔርን ሕዝብ በቅርበት ለማስተዳደር ያስችላል በማለት ያቀረበውን መዋቅር አብራራ:: ለ) ምእመናንን ለመምራት ውጤታማ መዋቅር አስፈላጊ የሚሆነው ለምንድን ነው? ሐ) ግልጽ የሆነ መዋቅር አለመኖር ወይም ቢሮክራሲያዊ መሆን የእግዚአብሔርን ሥራ የሚያደናቅፈው እንዴት ነው? መ) ሁሉንም ምእመናን በእረኝነት ለማገልገል የሚያስችል ምን ዓይነት መዋቅር ለቤተ ክርስቲያናችሁ ልታዘጋጁ ትችላላችሁ?

4. ሀ) አገልግሎትን ለሌላ ሰው ስለ መወከል የተሰጠውን ትምህርት ከልሱ:: ለ) በቡድናችሁ ውስጥ ሁሉም ሰው የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ ነው እንበል:: የውጤታማ ውክልናን ዘዴዎች በመጠቀም፣ ለቤተ ክርስቲያናችሁ አዲስ መጋቢ ኃላፊነቶችን ለመወከል የምታደርጓቸውን ነገሮችና የምታብራሯቸውን አሳቦች ግለጹ:: ሐ) በዚህ መንገድ ውክልና መስጠቱ መጋቢውን እንዴት የሚረዳው ይመስላችኋል?

5. ሀ) ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ወንጌላዊ አብራችሁ «የሥራ ዝርዝር» አዘጋጁ:: ለ) የሥራ ዝርዝር መዘጋጀቱ ወንጌላዊው ሥራውን በተሻለ ሁኔታ እንዲያከናውን የሚረዳው እንዴት ነው?

# ትምህርት አሥራ ሁለት

## አንደኛ ቀን

ክፍሌ የቤተ ክርስቲያናቸው ሰብሳቢ ሆኖ ተመርጦ ነበር:: ክፍሌ ሰዎች እንደ መሪ ሊያከብሩት የሚችሉት በግል ካወቁትና ካከበሩት ብቻ እንደ ሆነ ያውቅ ነበር:: ስለዚህ ክፍሌ ምእመናንን በግል ደረጃ ለማወቅ ጥረት ማድረግ ጀመረ:: ወዲያውኑ እንደ ተመረጠ፣ የአባላትን ዝርዝር በመውሰድ የባሎችን፣ የሚስቶችንና የልጆችን ስም ማጥናት ጀመረ:: ከዚያም ከአምልኮ በኋላ በር ላይ



በመቆም እያንዳንዱን አባል ስሙን እየጠራ ሰላም ይል ጀመር:: ቢያንስ በሳምንት አንድ ጊዜ እያንዳንዱን ቤተሰብ በመጎብኘት ቤተ ክርስቲያንን እንዴት መምራት እንዳለበት አስተያየት እንዲሰጡት ይጠይቅ ነበር:: አንድ ሰው ከታመመ ወይም ችግር ከደረሰበት፣ ክፍሌ የመጀመሪያው ደራሽ ሆነ:: ሰዎች ክፍሌን ማመን ጀመሩ:: አንድ ነገር በሚወሰንበት ጊዜ፣ ለእኛው ጥቅም ነው ይህንን ያደረገው ብለው ስለሚያስቡ፣ ያለ ምንም ማንገራገር ውሳኔውን ይቀበላሉ:: አንድ ጊዜ አንድ አባላቸው በኃጢአት በመውደቁ ምክንያት ክፍሌ ቅጣት ሲጥልበት፣ የሰውዬው ዘመዶች ሳይቀሩ ክፍሌን ደግፈውታል:: ምክንያቱም ክፍሌ ነገሮችን በፍትሐዊነት እንደሚያከናውንና ለእግዚአብሔር ባለው ፍቅር ተነሣስቶ እርምጃዎችን እንደሚወስድ ያውቃሉ:: ለክፍሌ፣ አመራር በአንጻራዊ መልኩ ከወቀሳዎችና ከጦፉ ክርክሮች የጸዳ ነበር:: ለክፍሌ፣ አመራር ደስታ ነበር::

ወልዴ የሌላ ቤተ ክርስቲያን ሰብሳቢ ሆኖ ተመርጦ ነበር:: ሥራ ስለሚበዛበትና ተግባሬ ውሳኔዎችን መስጠትና ለምእመናን መመሪያዎችን መስጠት ነው ብሎ ስለሚያምን፣ ከምእመናን ጋር ጥሩ ግንኙነት ለመመሥረት ጥረት አላደረገም:: ወልዴ ከምእመናን ሩቅ ነበር:: ምእመናን ችግር በሚገጥማቸው ጊዜ ራሱ ከመሄድ ይልቅ መልእክተኛ ይልክ ነበር:: ምእመናን ወልዴን የሚያዩት አሉድ እሑድ ሽማግሌዎች የወሰኗቸውን ደንቦች ሲያነብ ወይም በትክክል ስላላደረጓቸው ነገሮች ሲገሥጻቸው ብቻ ነበር:: ሕዝቡ በጥርጣሬ ተሞልተው ሽማግሌዎች «ይህን ውሳኔ ያስተላለፉት ለምንድን ነው? ተጨማሪ ገንዘብ ከእኛ ስለሚፈልጉ ነው? ሥልጣናቸውን ለማስፋት እየፈለጉ ነው?» የሚሉ ጥያቄዎችን ማንሣት ጀመሩ:: አንድ ጊዜ አንደ ታዋቂ የቤተ ክርስቲያኒቱ አባል በኃጢአት ወደቀ:: ሽማግሌዎች ጥፋተኛውን ግለሰብ ለመቅጣት ሲሞክሩ፣ ዘመዶቹና አንዳንድ ወዳጆቹ ቅጣቱን ባለመቀበላቸው ክፍፍል ተፈጠረ:: ሕዝቡ ወልዴ ሊያደርግ የፈለገውን ነገር ሁሉ ይቃወም ጀመር:: ወዲያውም አመራርን በመጥላት በምእመናን ድርጊቶች ይናደድ ጀመር::

1ኛ ጥያቄ፡- ሀ) የክፍሌን አመራር ቀለል ያደረገውና የወልዴን ያከበደው ምንድን ነበር? ለ) መሪው ከምእመናን ጋር ያለው ግንኙነት ሕዝቡ ውሳኔዎቹን እንዲደግፍ ወይም እንዳይደግፍ የሚያደርገው እንዴት ነው? ሐ) ምእመናን የቤተ ክርስቲያን መሪውን ባለማወቃቸው ምክንያት ሲጠራጠሩት የተመለከትከበትን ሁኔታ አብራራ።

እስካሁን ራእይ ያለው መሪነት የሚካሄደው ሰዎች እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን የሰጠውን ራእይ ወደ መፈጸሙ አቅጣጫ ተከትለውት በሚሄዱበት ጊዜ መሆኑን ስናጠና ቆይተናል። ለዚህም ነው የመጀመሪያዎቹ ሦስት የመሪነት ክህሎቶች ሕዝቡን ወደ ራእዩ ፍጻሜ መምራትን ያካተቱት። አንድ መሪ ራእዩን የመወሰን፣ ራእዩን ለመፈጸም ዕቅዶችን የማውጣትና ሰዎችን የመወከል ተግባራትን እንደሚከታተል ተመልክተናል።

በዚህ ሳምንት አንድ መሪ ውጤታማ ለመሆን ከፈለገ፣ ሊማር የሚገባቸውን ሁለት ተጨማሪ ክህሎቶች እንማራለን። አንድ መሪ ግቦችንና ዕቅዶችን ምንም ያህል ጥሩ አድርጎ ቢያዘጋጅም፣ እነዚህን ሁለት ክህሎቶች ካልተማረ፣ ራእዩና ዕቅዶቹ እርባና ቢስ ይሆናሉ። እነዚህ ሁለት ክህሎቶች <u>ከሰዎች ጋር ጥሩ ግንኙነት የመመሥረት</u> እና <u>ጥሩ ውሳኔዎችን የመስጠት ክህሎቶች</u> ናቸው።

ከላይ በተመለከትናቸው ምሳሌዎች ውስጥ፣ ክፍሌ በዋናነት ውጤታማ ሲሆን የቻለው ከሰዎች ጋር ጥሩ ግንኙነት ለመመሥረት ጥረት በማድረጉ ነበር። ነገር ግን ወልዴ ከሰዎች ጋር ግንኙነት ለመመሥረት ጊዜ ስላልወሰደ፣ ሰዎች ይጠራጠሩት ጀመር። ከዚህም የተነሣ የሚወስዳቸውን እርምጃዎች ሁሉ በመቃወማቸው፣ አመራሩ በጭንቅ የተሞላ ሆነ። መሪዎች ውጤታማ ለመሆን ከፈለጉ፣ ከሚመሩት ሕዝብ ጋር ጥሩ ግንኙነት መመሥረት አለባቸው።

**አራተኛ ክህሎት፡- ከምእመናን እና ከሌሎች መሪዎች ጋር በመተማመንና በፍቅር ላይ የተመሠረተ ግንኙነት መመሥረት**

2ኛ ጥያቄ፡- 1ኛ ጴጥ. 4:8 አንብብ። ሀ) ጴጥሮስ በዚህ ጥቅስ ለማስተላለፍ የፈለገው መልእክት ምን ይመስልሃል? ለ) ሰዎች መሪው እንደሚወዳቸው ካወቁ ስሕተቶቹን ሲያልፉ የተመለከትከው እንዴት ነው?



**ከሰዎች ጋር ስምምነት የተሞላባቸው ግንኙነቶች የሚፈልቁት በመተማመን ላይ ከተመሠረቱ ግንኙነቶች ነው።**

አንድ መኪና ነዳጅና ጎማ ካለው ሊሄድ ይችላል። ነገር ግን በሞተር ውስጥ ዘይት ከሌለ፣ በጥሩ ሁኔታ ወይም ብዙ ርቀት ሊሄድ አይችልም። ሞተሩ በጣም ሳይሞቅ እንዲሠራ የሚያደርገው ዘይቱ ነው። ወደ አመራር ስንመጣ፣ መሪነታችን በጥሩ ሁኔታ እንዲካሄድ የሚያደርገው ከሰዎች ጋር ያለን ግንኙነት ነው። ጴጥሮስ እንዳስተማረው፣ በአማኞች መካከል ፍቅር በሚኖርበት ጊዜ አንዱ በሌላ ላይ ኃጢአት ቢሠራ እንኳን፣ ችግሩ በቀላሉ ይወገድና ግንኙነቱ ይቀጥላል። ሰላም ለመፍጠር ሲባል ችግሮች ተሸፋፍነው አይታለፉም። ነገር ግን ከልባቸው ስለሚዋደዱ፣ ሰዎች የሚፈጠሩትን ስሕተቶች ባለማጋነን ይቅርታ ይደራረጋሉ። በግንኙነቶች ውስጥ የምንጋፈጣቸው ብዙዎቹ ትግሎቹ የሚመነጩት ቀድሞውኑ የፍቅር መሠረት ካለመጣሉ ነው።

በክፍል አንድ መጽሐፋችን ውስጥ እንደተመለከተው፣ የቤተ ክርስቲያን መሪው ባሕርይ ለአመራሩ መሠረት ይጥላል። አንድ ሰው ጥሩ ግንኙነቶችን እንዲመሠርትና እንዲቀጥል የሚያስችለው መንፈሳዊ ባሕርይ ነው። እነዚህ ጥሩ ግንኙነቶች ደግሞ የአመራር ሥራችንን ቀላል ያደርጉልናል። ለጥሩ ግንኙነት መሠረት የሚጥሉ ሦስት ነገሮች አሉ።

<u>በመጀመሪያ</u>፣ ፍቅር መኖር አለበት። ፍቅር ከራስ ፍላጎት በላይ ለሌሎች በጎነት ማሰብ ነው። ፍቅር ሌላውን ለመጥቀም ሲባል ራስን አሳልፎ መስጠት ነው። ስለሆነም አንድ መሪ ምእመናንን ሲወድና ለእነርሱ ጥቅም ራሱን አሳልፎ ሲሰጥ፣ እንዲሁም ምእመናን ይህንን ሁኔታ በተሞክሮ ሲያረጋግጡ፣ አመራሩ ይበልጥ ሰላማዊ ይሆናል።

<u>ሁለተኛ</u>፣ መተማመን መኖር አለበት። የቤተ ክርስቲያን ምእመናንና መሪዎች፣ እንዲሁም መሪዎች እርስ በርሳቸው በሚተማመኑበት ጊዜ፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እምብዛም ዓበይት ችግሮች አይፈጠሩም። ነገር ግን በቤተ ክርስቲያን መሪዎችና

በምእመናን ወይም በራሳቸው በመሪዎች መካከል አለመተማመን ካለ፣ ቀላል ነገር ማከናወኑ ራሱ ከባድ ሆኖ ይገኛል።

<u>ሦስተኛ</u>፣ መከባበር መኖር አለበት። የቤተ ክርስቲያን ምእመናን መሪዎቻቸው መልካም የመንፈሳዊነት አርአያዎች እንደ ሆኑ በመረዳት ባሕርያቸውን በሚያከብሩበት ጊዜ፣ ሕዝቡ ስለ መሪ ዎቹና ስሚሰጡት ውሳኔ ጥሩ አስተሳሰብ ይኖረዋል።

ስለሆነም፣ አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ መማር ካለበት እጅግ አስፈላጊ ነገሮች አንዱ የምእመናንንና የሌሎች መሪዎችን ፍቅር፣ መተማመንና አክብሮት ማትረፍ ነው።

**በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብዙውን ጊዜ መተማመን የማይኖረው ለምንድን ነው?**

በመሪዎች መካከል፣ እንዲሁም በመሪዎችና በምእመናን መካከል የመተማመን አለመኖር የበርካታ አብያተ ክርስቲያናት መለያ ነው ማለት ይቻላል። ለዚህም አያሌ ምክንያቶች አሉ፦

1. በባህል ደረጃ፣ ብዙዎቻችን ሰዎችን ማመን እንደሌለብን ይነገረናል። ሰዎችን ካመንን፣ መጠቀሚያ እንደሚያደርጉን ማስጠንቀቂያ ይሰጠናል። «ምሥጢሮችህን ለማን እንደምትናገር መጠንቀቅ አለብህ። ምሥጢሮችህን ተጠቅመው ይጫወቱብሃል፣» የሚል ትምህርት ይሰጠናል። አንድ ቀን አንድ ሰባኪ፣ «ምሥጢርህን ለማንም፣ ለሚስትህም እንኳን መናገር የለብህም። ምሥጢርህን ለእግዚአብሔር ብቻ ንገረው፣» ሲል ሰምቻለሁ። ይህ በግንኙነቶች ውስጥ መተማመን አለመኖሩን ያሳያል። በአንዳንድ ባሕሎች ሰዎችን ማታለል መቻል እንደ ጀብዱ ይቆጠራል። በብዙ ታሪኮች ውስጥ ጀግናው ሌሎችን የሚያታልላቸው ወይም የሚሸውዳቸው ሰው እንደ ሆነ ይገለጻል። የተታለለው ሰውዬ ሞኝ በመሆኑ ጥፋተኛ ነው ብለን እናስባለን። ስለሆነም፣ ማታለሉ እንደ ጥፋት አይታይም። ጦጣ ሌሎችን እንስሳት ሁሉ ለማታለል በመቻ ሏ ጎበዝ ነች እንላለን። በኢትዮጵያ «ሰምና ወርቅ» የሚባል የሥነ-ጽሑፍ ዓይነት አለ። እንዲህ ዓይነት ጽሑፍ የሚጻፈው ሆን ብሎ ሰውን ለማታለል ነው። ላይ ላዩን ሲታይ ጥሩ የሚመስሉ ቃላት



ውስጠ- ወይራ ትርጉም ይይዛሉ። ከዚህ ባሕላዊ ውርስ ሳቢያ ሰ ዎችን ማመኑ ይከብደናል። ሰዎች ከሚናገሩት ነገር ሁልጊዜም ስውር ትርጉም እንፈልጋለን። ከመሪዎች ውሳኔዎችም ውስጥ ስውር ትርጉሞችን እንፈልጋለን። ሰዎች ለራሳቸው ጥቅም ሊያውሉት ስለሚችሉ ቃላችንን በጥንቃቄ እንመዝናለን።

ነገር ግን ይህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የግንኙነት መስመር ነው? በፍጹም አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች እንዲያደርጉላችሁ የምትወዱትን እናንተ ደግሞ አድርጉላቸው ይለናል (ማቴ. 7:12)። ማናችንም ብንሆን ልንታለል ወይም ሰዎች እንዲጠቀሙብን አንፈልግም። ስለሆነም፣ ሰዎችን ለማታለል ወይም መጠቀሚያ ለማድረግ መሞከር የለብንም። ክርስቶስ «አዎን» ስንል ከልባችን «አዎን» ልንል፣ «አይደለም» ስንልም እንዲሁ ከልባችን «አይደለም» እንድንል አስተምሮናል (ማቴ. 5:37)። ይህም ማለት በቃላችን ሰውን ለማታለል ምንም ዓይነት ዘዴ መጠቀም የለብንም ማለት ነው። ነግር ግን በፍጹም ግልጽነት ልንናገር ይገባል። በአንድ ነገር ከተስማማን፣ የማንስማማ ከመምሰል ይልቅ በቀጥታ መስማታችንን መግለጽ አለብን። የማንስማማ ከሆነ ደግሞ፣ ሰዎች ለመስማት የማይፈልጉትን አሳብ በልባችን ይዘን ዝም ብለን ከምናቅማማ፣ ሙሉውን መረጃ ልንሰጣቸው ይገባል። አሳባችንን በፍቅር መግለጽ አለብን። ነገር ግን ውጤታማ ተግባቦት እንዲኖር ሁሉም ሰው የሚያስበውን በግልጽ ማሳወቁ ወሳኝ ነው።

አንድን ሰው ለማታለል ወይም መጠቀሚያ ለማድረግ መሞከር «ውሸተኛ» መሆን ነው። አንድን ሰው መጠቀሚያ ለማድረግ ብለን እውነት በሆነው ነገር ላይ ስንጨምር ወይም ከእውነቱ የተ ወሰነውን ክፍል ስንደብቅ፣ እየዋሸነው ነው ማለት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ውሸትን እንደሚጠላ ይናገራል። እንዲያውም ውሸትን በጣም ከመጥላቱ የተነሣ የመዋሸት ልምድ ያላቸው ሰዎች ወደ መንግሥት ሰማያት እንደማይገቡ ይገልጻል (ራእይ 21:8)። ጳውሎስ አንዳችን ሌላውን ማታለል እንደሌለብን ገልጾአል። ይልቁንም፣ እውነትን በፍቅር እንድንናገር ያበረታታናል (ኤፌ. 4:14-15)።

የክርስቶስ ተከታዮች እንደ መሆናችን፣ እንዴት መምረጥ አለብን:: አለመተማመንን የሚፈጥረውን ባሕሳዊ ልማዳችንን እንከተላለን ወይስ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረንን የግንኙነት መስመር እናከብራለን? ሙሉውን እውነት በመደበቅ ሌላውን ሰው መጠቀሚያ ላለማድረግ ወይም በግንኙነቶቻችን ሙሉ በሙሉ ግልጽ ለመሆን እስካልወሰንን ድረስ፣ ምን ጊዜም በመካከላችን መተ ማመን ሊኖር አይችልም:: መተማመን ከሌለ ደግሞ፣ የእግዚአብሔ ርን ሕዝብ እርሱ ወደሚፈልገው ራእይ ልንመራ አንችልም:: ይህንን ሰይጣን የገነባውን ምሽግ ለመናድ ጊዜው አሁን አይደለምን?

| |
|---|
| 3ኛ ጥያቄ፡- ሀ) መሪዎች መረጃን በመደበቅ እርስ በርሳቸው ወይም ምእመናንን ለማታለል ሲሞክሩ ያየኸው እንዴት ነው? ለ) ከዚህ የተነሣ ባታለሉትና በተታለሉት መካከል የነበረው ግንኙነት ምን ሆነ? ሐ) ብዙውን ጊዜ እርስ በርሳችን የማንተማመንባቸውን ሁኔታዎች ግለጽ:: የማንተማመነው ለምንድን ነው? በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ መተ ማመን ይኖር ዘንድ ክርስቶስ ምን እንድናደርግ ወይም እንድንለውጥ የሚፈልግ ይመስልሃል? |

ሌላው ግልጽና ድክመታችንን ሳይቀር ለሰዎች እንዳናሳውቅ የሚያደርገን ሰዎች እውነትን አይቀበሉም የሚል ፍርሃት ሰላሰብን ነው:: ከሰዎች መረጃዎችን በምንደብቅበት ጊዜ ከምንሰጣቸው ማመኻኛዎች መካከል አንዳንዶቹ የሚከተለውን የሚመስሉ ናቸው: - «እንደ እኛ የተማሩ አይደሉም:: ነገሮችን ለምን በዚህ መንገድ እንደምናደርግ አይገባቸውም:: ምንም ነገር ስለማይገባቸው ለምን ይህንን ውሳኔ እንዳስተላለፈን ሊያውቁ አይችሉም፣ ማወቅም አያስፈልጋቸውም:: እኛ መሪዎች ስለሆንን ሊተማመኑን ይገባል::» ነገር ግን የዚህ አስተሳሰብ መሠረቱ ኩራት ነው:: እኛ ከሌሎች በላይ አስተዋዮችና ከሁሉም በላይ የሚሻለውን ነገር እናውቃለን ብለን እናስባለን:: የተማርነውና ለሌሎች የሚበጀውን የምናውቀው እኛው ነን:: «ውሳኔ መስጠት የእንድ መሪ ድርሻ ነው:: ሕዝቡ ውሳኔዎቹን መቀበል አለባቸው» እንላለን:: ይህ የውሸት አስተሳሰብ በመሪዎች ልብ ውስጥ ኩራትን የሚዘራ የሰይጣን መሣሪያ ነው:: ይህ ሰይጣን እንድ ልብና እንድ አሳብ (ፊልጵ. 2:2) እንዳይኖረን



ለመከላከል በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚያስፋፋው አስተሳሰብ ነው::»

| |
|---|
| 4ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ይህንን አመለካከት ከቤተ ክርስቲያን መሪዎች መካከል የታዘብክበትን ጊዜ ግለጽ:: ለ) ይህ በቤተ ክርስቲያን መሪዎችና በሕዝቡ መካከል ባለው ግንኙነት ላይ ያስከተለው ችግር ምን ነበር? |

3. ሌላው መተማመን የማይኖርበት ምክንያት ሁልጊዜም የግል ጥቅማችንን ለስምናስቀድም ነው:: ሁኔታዎችን ሁሉ ለግላችን፣ ለቤተሰባችን ወይም ለጎሳችን ጥቅም ለማዋል እንፈልጋለን:: ሁኔታ ዎችን ተጠቅመን ራሳችንን መጥቀም እንዳለብን እንማራለን:: ይህ ማለት የመሪነት ጊዜአችን ለአጭር ጊዜ ብቻ የሚቆይ በመሆኑ፣ የመሪነት አጋጣሚውን ተጠቅመን የተወሰነ ጥቅም ለማግኘት እንሞክራለን ማለት ነው:: ብዙውን ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ገንዘብ ማግኘቱ አስቸጋሪ ነው:: ነገር ግን ለራሳችን ትልቅ ክብር፣ ወይም ለቤተሰባችን ትልቅ ጥቅም (ኪየር ውስጥ እንዲገቡ ማድረግ ወይም በቤተ ክርስቲያን የሥራ መስኮች እንዲቀጠሩ ማገዝ፣ ወዘተ. . . ) ማድረግ ይቻላል:: ስለዚህም ሰዎች፣ «የቤተ ክርስቲያን መሪው ሥልጣኑን ተጠቅሞ ራሱን፣ ቤተሰቡንና ጎሳውን እየጠቀመ ያለው እንዴት ነው?» ሲሉ ይጠይቃሉ:: የሚያሳዝነው፣ መሪዎች ሥልጣናቸውን መከታ አድርገው ራሳቸውንና ቤተሰቦቻቸውን የሚጠቅሙበት ብዙ አጋጣሚ መኖሩ ነው:: ከዚህ አንጻር ሕዝቡ መሪዎችንና የሚናገሩትን ነገር አለማመኑ አስገራሚ አይሆንም:: እሁንም፣ ሰይጣን በአማኞች መካከል መተማመን እንዳይኖር ለማድረግ ተግቶ እየሠራ መሆኑን እንረዳለን:: ለራሳችንና ለቤተ ሰባችን ጥቅም በምንሯሯጥበት ጊዜ እግዚአብሔር ከራሳችን በላይ ሌሎችን እንድናከብር የሰጠውን ትእዛዝ እየጣስን ነው (ፊልጵ. 2:3-4):: የእግዚአብሔር ልጅ እንደ መሆኑ መጠን ሁኔታውን ተጠቅሞ ራሱን ከመጥቀም ይልቅ፣ እኛ የዘላለምን ሕይወት እናገኝ ዘንድ ጥቅሞቹን ወደ ጎን የተወውን የክርስቶስ ምሳሌነት ለመከተል አልፈለግንም ማለት ነው (ፊልጵ. 2:5-11):: እንዲሁም እንደ መሪ ዎች ማዳላት ከፍተኛ ጥፋት መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል (ያዕ. 2:1፣ 9)::

5ኛ ጥያቄ:- ሀ) በቤተ ክርስቲያናችሁ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የግል ጥቅማቸውን ሲያሳድዱ የተመለከትከበትን ሁኔታ ግለጽ። ለ) ይህ በቤተ ክርስቲያን መሪዎችና በምእመናን መካከል ባለው ግንኙነት ላይ ምን አስከተለ? ሐ) ክርስቶስ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለራሳቸው፣ ለቤተሰባቸው ወይም ለጎሳቸው ጥቅም ሲያገኙ በሚችሉባቸው ሁኔታዎች ላይ ምን ዓይነት እርምጃዎችን እንዲወስዱ የሚፈልግ ይመስልሃል?

4. አለመተማመን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዲሰፍን ያደረገው የመጨረሻው ምክንያት ከመረጃ አጠቃቀማችን ጋር የተያያዘ ነው። ብዙውን ጊዜ መረጃን የምንጠቀመው ሥልጣናችንንና ኃይላችንን የምናሳይበት መንገድ አድርገን ነው። አንዳንድ ጊዜ ለሰዎች አንድን ነገር የምንናገረው የሆነ ልዩ ኃይል እንዳለን አድርገው እንዲገምቱን በማሰብ ነው። ሌላ ጊዜ ደግሞ ልዩ ኃይል እንዳለን ለማሳየት ስንል ብቻ መረጃን እንደብቃለን። ከሽማግሌዎች ውሳኔዎች መካከል ምእመናን የሚያውቁት ምን ያህሉን ነው? እምብዛም የሚነገራቸው ነገር የለም። ለምን? ይህ የሚሆነው አብዛኛው ውሳኔ ምእመናንን ሊጎዳ የሚችል ስሜት ቀስቃሽ በመሆኑ ነው? አይመስልም። በብዙ አጋጣሚዎች፣ የቤተ ክርስቲያን ምእመናን የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሚወያዩባቸውንና የሚሰጧቸውን ውሳኔዎች ቢያውቁ እየሆነ ያለውን ነገር በሚገባ ይገነዘቡ ነበር። ነገር ግን የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሌሎች የማያውቁትን መረጃ በማወቃቸው የበለጠ ኃይል አለን የማለት ስሜት ይሰማቸዋል።

ይህም ሆኖ፣ መረጃው ከምእመናን ጆሮ ቢደርስ የሰዎችን ስም ሊያጠፋ የሚችልበት አጋጣሚ እንዳለም መዘንጋት የለብንም። ነገር ግን መሪዎች የሚነጋገሩባቸውን አብዛኞቹን ነገሮች ምእመናንን ቢያውቁ፣ ይጠቅም እንደ ሆነ እንጂ አይጎዳም። ሕዝቡ አንድን ነገር ሳያውቁ ሲቀሩ ወይም መረጃ ሲደበቅባቸው፣ ከእውነታው የከፋ ግምት ውስጥ ይገባሉ። አንድ ጊዜ የዚህ የጥናት መጽሐፍ ጸሐፊ አንድን ኢትዮጵያዊ ወደ አንድ የቦርድ ስብሰባ ጋበዘው። እንዲህ ዓይነት ነገር የተደረገው ለመጀመሪያ ጊዜ ነበር። ሰውየው የተነጋገርናቸውን ነገሮች በሙሉ ሰማ። ከዚያ በኋላ ሌሎች ኢትዮጵያውያን ሠራተኞችን ሰብስቦ ስለ ተነጋገርንባቸው ነገሮች



አጠር ያለ መግለጫ ሰጣቸው። መግለጫውን የሰሙትም፣ «እኛ እኮ እኛን እንዴት ከቁጥጥራቸው ሥር እንደሚያደርጉን የሚነጋገሩ ይመስለን ነበር። ስለ ራሳቸውና ወንጌሉን እንዴት ሊያስፋፉ እንደሚችሉ የሚነጋገሩ መሆናቸውን አናውቅም ነበር፣» አሉ። ለብዙ ዓመታት በቦርዱ ውስጥ የሚከናወነውን ነገር አለማወቃቸው በኢትዮጵያውያን ሠራተኞችና በሚሲዮናውያን መካከል አለመተማመንን ፈጥሮ ነበር። ሠራተኞቹ መረጃውን ካወቁ በኋላ፣ ወዲያውኑ ብዙ መተማመን ሊፈጠር ቻለ።

ኢየሱስ አንድ ጊዜ በምሥጢር የምንናገረው ነገር ወደ አደባባይ እንደሚወጣ ገልጾ ነበር (ሉቃስ 12:2-3)። ሁልጊዜም የምንወስነው ነገር ምሥጢር ሆኖ የሚቆይ ይመስለናል። ነገር ግን ብዙውን ጊዜ ምሥጢር ነው የተባለው ነገር ወደ ምእመናን ጆሮ ይደርስና የከፋ ችግር ያስከትላል። የሰዎችን አመኔታ በሚያስገኝ መንገድ መምራት ከፈለግን፣ መረጃን ማካፈል እንጂ መደበቅ አይገባንም።

6ኛ ጥያቄ:- ሀ) የመረጃ አስመናር አለመተማመንን ሲፈጥር የተመለከትከው እንዴት ነው? ለ) መሪዎች ለቤተ ክርስቲያን ምእመናን በነጻነት ሊያካፍሉ የሚገባቸውን አንዳንድ መረጃዎች ዘርዝር። ሐ) መሪዎች በጥንቃቄ በምሥጢር ሊይዙ የሚገባቸውን አንዳንድ መረጃዎች ዘርዝር። እንዲህ ዓይነቱ መረጃ በምሥጢር መያዝ ያስበት ለምንድን ነው? መ) ይህንን መረጃ በምሥጢር መያዙ የቤተ ክርስቲያን ምእመናንን አመኔታ ይጨምራል ወይስ ይቀንሳል? መልስህን አብራራ።

## አለመተማመን ቤተ ክርስቲያንን የሚጎዳው እንዴት ነው?

እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን መሪ አገልግሎት በመተማመን ላይ የተመሠረተ ነው። ይህ መተማመን ከሌለ፣ ምንም እንኳን ግለሰቡ የመሪነቱን ሥልጣን ቢይዝም፣ ሕዝቡን በጥሩ ሁኔታ ሊመራ አይችልም። ሰዎች የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ውሳኔና አመራር የሚቀበሉት ባላቸው አመኔታ ልክ ነው። ምእመናን የመሪውን ልባዊ ፍላጎት ከተጠራጠሩ፣ አይከተሉትም። አንድን ሰው እውነተኛ መሪ የሚያደርገው ደግሞ ሰዎች በፈቃደኝነት የሚከተሉት

መሆናቸው ነው:: ሰዎች መሪውን እንዲከተሉ የሚያደርገው ደግሞ መተማመን ነው:: በመሪዎች መካከል፣ እንዲሁም በቤተ ክርስቲያን መሪዎችና በምእመናን መካከል መተማመን ባለመኖሩ ምክንያት የሚከሰቱት ችግሮች ከዚህ በታች ተመልክተዋል::

1. በቤተ ክርስቲያን መሪዎች መካከል መተማመን በማይኖርበት ጊዜ፣ ሕዝቡ ለሚናገሩት ነገር ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው:: ሁላችንም ከሌሎች ጋር የግንኙነት ችግሮች ካሉባቸው ሰዎች ጋር ስብሰባ ተቀምጠን እናውቃለን:: በዚህ ጊዜ ቀላል ውሳኔ ዎችን ለማሳለፍ እንኳን ብዙ ጥረትን ይጠይቃል:: በቃላችን ሌሎችን ላለመጉዳት ወይም ትክክለኛ ውሳኔ ከማድረግ ይልቅ የተናገርነው ነገር ተተርጉሞ በሌላ መልክ እንዳይወሰድብን ጥንቃቄ እናደርጋለን:: ከዚህ የአለመተማመን ችግር የተነሣ በውይይቶች ብዙ ጊዜና ጉልበት ይባክናል::

2. ባለመተማመን ምክንያት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አብዛኞቹ ውሳኔዎች የሚገባቸውን ያህል ጥሩዎች አይሆኑም:: ብዙውን ጊዜ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ውሳኔ የሚሰጡት የሰዎችን ስሜት በሚጠብቅ መልኩ ይሆናል:: እያንዳንዱ ሰው ወደ ስብሰባው የሚመጣው የግል አጀንዳውን ይዞ ነው:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ይህንን ስለሚያውቁ፣ ለቤተ ክርስቲያንና ለእግዚአብሔር መንግሥት ከሁሉም የሚሻለውን ውሳኔ እንደ መስጠት፣ የተሳታፊዎችን ስሜት እምብዛም የማይጎዳ ውሳኔ ይሰጣሉ::

3. ካለመተማመን የተነሣ ሰዎች «ስውር» የቃላት ፍች ይፈልጋሉ:: አንድ ጊዜ ከቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጋር እስቺጋሪ ስብሰባ ስናካሂድ ነበር:: ምንም እንኳን ያየሁትን ችግር በግልጽነት ለመናገር ብሞክርም፣ አንደኛው የቤተ ክርስቲያን መሪ ለሌላው፣ «ተጠንቀቅ፣ እዚህ ጋ ድብቅ የልብ ፍላጎት አለ፣» ሲል አስጠንቀቀው:: መተማመን ከሌለ፣ ሰዎች ስውር የውስጥ ፍላጎት (ሞቲቭ) ይፈልጋሉ:: የተወሰረ ነገር ባይኖር እንኳን፣ ሰዎች መሪው ያለ አግባብ ራሱን ለመጥቀም ስውር ነገር እየተናገረ ነው ብለው ያስባሉ:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሰዎች የሚደብቋቸውን



ነገሮች እየገመቱ በመወያየት ብዙ ሰዓታት ያጠፋሉ:: ውሳኔዎችንም የሚሰጡት በእነዚህ ግምቶች ላይ ተመሥርተው ነው:: በአመዛኙ ግን፣ የተገመተው ነገር ስሕተት ሆኖ ይገኛል:: ጳውሎስ ፍቅር «ሁሉን ያምናል» ነበር ያለው (1ኛ ቆሮ. 13:4-7):: ይህም ማለት፣ ፍቅርና መተማመን ካለ፣ እያንዳንዱ ሰው ነገሮችን የሚያደርገው ከትክክለኛ የውስጥ ፍላጎት በመነሣት ነው ብለው ሰዎች ይገምታሉ ማለት ነው::

4. አለመተማመን ባለመኖሩ ምክንያት፣ የቤተ ክርስቲያን ምእመናን የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሚናገሩትን ነገር እንደ ማመን ልባዊ ፍላጎታቸውን ይጠራጠራሉ:: ወይም ደግሞ ምእመናን የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ያወጧቸው ደንቦች ትክክል አይደሉም ብለው ያስባሉ:: ስለሆነም፣ የተሰጠው ውሳኔ ቤተ ክርስቲያኒቱን ሊጠቅም የሚችል ቢሆንም እንኳን፣ የቤተ ክርስቲያን ምእመናን አሻፈረኝ ከማለት አይመለሱም:: ሕዝቡ ራእዩን ለመፈጸም እብሮ ይሠራ ዘንድ በመካከላቸው የመተማመን ግንኙነት እስካልተመሠረተ ድረስ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሕዝቡን አስተባብረው ወደተፈለገው ግብ ሊያደርሱ የሚችሉበት መንገድ ሊኖር አይችልም::

5. የማያቋርጡ ውስጣዊ ውጥረቶችና የኃይል ትግሎች ያለመተማመን ውጤቶች ናቸው:: በሽማግሌዎች ቦርድ ውስጥ ያሉት ሰዎች አንድ ቀን የስብሳቢነቱን ወንበር የሚቆናጠጡበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ይጣጣራሉ:: ወይም ደግሞ እሁን ያሉትን ወይም የበፊቶቹን መሪዎች ለማሳጣት ጥረት ያደርጋሉ:: የበፊት መሪዎች አሁን ያሉትን መሪዎች ለማሳጣት በማለብ መጥፎ ወሬዎችን ያስወሩባቸዋል:: የወጣቶች መሪዎች ሽማግሌዎችን ይነቅፋሉ:: የመሪው ቤተሰቦች ቤተ ክርስቲያኒቱን ለራሳቸው ክብር የሚያገኙባት የፖለቲካ መድረክ አድርገው ይቀይሯታል:: ወይም የተወሰኑ ጎሳዎች ጥቅም ለማግኘት ይሞክራሉ:: ሌሎች ጎሳዎች ውሳኔ የተሰጠው እንድን ጎሳ ለመጥቀም በማሰብ ነው ይላሉ፣

ወዘተ. . .:: መተማመን ከሌለ፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሰላምና ስምምነት ሊኖር አይችልም::

6. ሰዎች መተማመን በማይኖርበት ጊዜ አስራታቸውንና መባቸውን ለቤተ ክርስቲያን አይሰጡም:: ሰዎች የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ገንዘቡን በማስተዋል እንደማይጠቀሙ ወይም ለግል ጥቅማቸው እንደሚያውሉ ከተጠራጠሩ፣ መስጠታቸውን ያቆማሉ:: ገንዘብ ከሌለ ደግሞ፣ የእግዚአብሔርን ሥራ መሥራት አይችልም::

7. ባለመተማመን ምክንያት መሪነት በረከት መሆኑ ቀርቶ ሸክም ይሆናል:: እግዚአብሔር ምእመናን አመራርን ለሸማግሌዎች ከባድ ሥራ እንዳያደርጉባቸው አስጠንቅቋቸዋል፣ ይህ ሽማግሌዎቹን ይጎዳቸዋልና (ዕብ. 13:17):: የእግዚአብሔር ሕዝብ እርስ በርሳቸው በመተማመን የእግዚአብሔርን አሳብ ለማሳካት አብረው መሥራታቸው ምንኛ አስደሳች ነገር ነው! በሌላ በኩል የእግዚአብሔር ሕዝብ ባለመተማመን በሚሞሉበት ጊዜ የሚፈጠረው ሥቃይና ዝለት ምንኛ የከፋ ነው! በዚህ ጊዜ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችም ሆኑ ምእመናን ለብስጭት ስለሚጋለጡ፣ እምብዛም ፍሬ ያለው ሥራ ሊሠራ አይችልም::

> 7ኛ ጥያቄ:- ሀ) በአማኞች መካከል መተማመን ባለመኖሩ ምክንያት በቤተ ክርስቲያን ወስጥ ችግሮች ሲፈጠሩ የተመለከትክበትን ሁኔታ አብራራ:: ለ) ምእመናን በግንኙነቶቻቸው ውስጥ መተማመንን ለማጎልበትና አለመተማመንን ለመቅረፍ ምን ምን ነገሮችን ሊያደርጉ ይችላሉ? ሐ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በአመራራቸውና በምእመናን መካከል መተማመን እንዲሰፍን ምን ሊያደርጉ ይችላሉ?

## ሁለተኛ ቀን

## መተማመንን ለማጎልበት የሚያግዙ ጠቃሚ እውነቶች

1. የቤተ ክርስቲያን ምእመናን መሪው እንደሚወዳቸውና እንደሚያስብላቸው ሲያውቁ፣ በመሪያቸው ይተማመናሉ:: ሰዎች



መሪው እንደሚወዳቸው ካወቁ፣ ሊከተሉትና ሊታዘዙት ፈቃደኞች ናቸው:: በአመራር ውስጥ የፍቅር ኃይል ትልቁ ነገር ነው (2ኛ ጢሞ. 1:7):: ሰዎች መሪው ከልቡ እንደሚወዳቸው ካወቁ፣ እርሱን ለመከተል ደስተኞች ናቸው:: እንዲህ ዓይነቱ ፍቅር እሑድ እሑድ ከምስባክ ላይ ቆሞ፣ «እወዳችኋለሁ፣» ማለት ሳይሆን፣ በተግባር የሚገለጽ መሆን አለበት:: መሪዎች የምእመናንን ችግሮች ለመቅረፍ፣ ከእግዚአብሔር ጋር ባላቸው ግንኙነት እንዲያድጉ ለመርዳት፣ ወዘተ. . . ራሳቸውን አሳልፈው በሚሰጡበት ጊዜ፣ ምእመናን ሊሰሟቸውና ሊከተሏቸው ይፈቅዳሉ:: ዮሐንስ ከክርስቶስ ጋር ያለንን ግንኙነት አስመልክቶ፣ እርሱ አስቀድሞ ወዶናልና (ሞቶልናልና) እኛም እንወደዋለን (ልንታዘዘው እንፈቅዳለን) (1ኛ ዮሐ. 4:19) ብሏል:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የምእመናንን እመኔታ ለማግኘት ማድረግ ያለባቸው የመጀመሪያው ነገር እንደሚወዷቸው፣ ሊጠቅሟቸው በማሰብና ለእግዚአብሔር ክብር ብለው እንደሚያገለግሏቸው በግልጽ ማሳየት አለባቸው::

2. የቤተ ክርስቲያን ምእመናን መሪውን ሲያከብሩት፣ ለመከተል ፈቃደኞች ይሆናሉ:: እክብሮት የሚመነጨው ከመሪው ባሕርይ ነው:: የቤተ ክርስቲያን ምእመናን በሕይወታችን ውስጥ ግብዝነትን ከተመለከቱ፣ ሊተማመኑብን አይችሉም:: የማይተማመኑብን ከሆነ ደግሞ፣ የምናደርገውን ነገር ሁሉ ይቃወማሉ:: ነገር ግን ምእመናን በሙሉ ልባችን እግዚአብሔርን እንደምንወድ፣ እነርሱንም እንደምንወዳቸውና ልንረዳቸው እንደምንፈልግ ካወቁ፣ ወይም የማናዳላ፣ ግልጽና መንፈሳዊ፣ የመንፈስ ፍሬን የምናሳይ መሆናችንን ካወቁ፣ ይተማመኑብናል:: ይህም የመሪነቱን ሥራ ያቀልልናል:: ምእመናኝ የሚያዳምጡን መተማመንና አክብሮትን ካጎለበትን ብቻ ነው:: ይህ ካልሆነ፣ የውሳኔውን ጠቃሚነትና አስፈላጊነት ሺህ ጊዜ ብናብራራላቸውም፣ የምንናገረውን የመስማት ፍላጎት አይኖራቸውም:: በእያንዳንዱ የአመራር እርምጃችንም ላይ ተቃውሞአቸውን ያሳያሉ::

3. መሪዎች በመተማመን መንፈስ አብረው ሊሠሩ የሚችሉት በግል ደረጃ መንፈሳዊ ብስለት ሲኖራቸው ነው። የሚከተሉትን ባሕርያት እስካላሳዩ ድረስ፣ መሪዎች አብረው ሲሠሩ አይችሉም።

- ከውሳኔው አሳብ ጋር በማይስማሙበት ጊዜ እንኳን እግዚአብሔር ነገሮችን ሲቀይር እንደሚችል በልበ-ሙሉነት ማመን፣
- ሌሎች ውሳኔያችንን ላይወዱ ቢችሉም፣ እግዚአብሔር እንደሚወዳቸውና እንደሚቀበላቸው በልበ-ሙሉነት ማመን፣
- እግዚአብሔር የሰጣቸውን ልዩ መንፈሳዊ ስጦታዎች፣ ችሎታዎችና አመለካከቶች መገንዘብ፣
- ሁሉንም ነገር እንደማያውቁና ሊሳሳቱ እንደሚችሉ በመረዳት የትሕትናን መንፈስ መላበስ፣
- እምብዛም ወሳኝ ባልሆኑ ነገሮች ላይ ሌሎች የመረጡት ውሳኔ እንዲሳካ ፈቃደኛ መሆን፣ ምንም እንኳን የመረጡት ነገር ከሁሉም የተሻለ ላይሆን ቢችልም።

እነዚህ ባሕርያት ከሌሉ፣ መሪዎች ከአንድ ሁኔታ ለራሳቸው የተሻለውን ነገር ለማግኘት በመሻት፣ ለመስማት ባለመፈለግ፣ ወዘተ. . . እርስ በርሳቸው ሊቆላለሉ ይችላሉ። ነገር ግን በእግዚአብሔር ላይ ግላዊ ልበ-ሙሉነት ሊኖራቸውና የግል ስጦታቸውንና ችሎታቸውን ሲረዱ፣ እነዚህም ነገሮች ከትሕትናና በእግዚአብሔር ከመተማመን ጋር ሲዋሃዱ፣ መሪዎች ችሎታቸውን በሚገባ ተጠቅመው ሊያገለግሉ ይችላሉ።

መንፈሳዊ ብስለታችን ብዙውን ጊዜ በሽማግሌዎች ስብሰባ ላይ ይገለጻል። ውጤታማ ስብሰባዎችን ለማካሄድና በቤተ ክርስቲያን መሪዎች መካከል ጥሩ ግንኙነት ለመመሥረት በመንፈሳዊ ብስለት ላይ የተመሠረተ መተማመን ወሳኝ ነው። መሪዎች መንፈሳዊ ብስለት ከሌላቸው፣ ውሳኔዎችን ለራሳቸው ጥቅም ወደ መጠምዘዝ



ያዘነብላሉ። ሽማግሌዎች አመለካከታቸውን በግልጽ ለመናገርና ከሌሎች አሳብ ጋር በቸርነት ለመለየት ይፈራሉ፤ ከውሳኔው ጋር በማይስማሙበት ጊዜ የአብዛኞቹን አሳብ አልቀበልም ይላሉ።

ነገር ግን ግላዊና መንፈሳዊ ብስለት በሚኖርበት ጊዜ የሚከተሉት ነገሮች ይከናወናሉ፦

ሀ. ለቤተ ክርስቲያናቸው ወይም ለአገልግሎታቸው የተለየ ነገር ለማግኘት ሳይፎካከሩ፣ መሪዎች አብረው ሊሠሩ ይችላሉ። በዚህ ጊዜ መሪዎች የትምህርታቸውን ታላቅነት በማጉላት ወይም አሳቡን ያቀረብኩት እኔው ነኝ በማለት የግል ክብር ለማግኘት አይሞክሩም። ሥልጣናቸውንና የአመራር ደረጃቸውን ለማሳየት ወይም ከውሳኔው የሕዝብን ትኩረት ለመሳብ አይጥሩም። አንድ ሰው እንደተናገረው፣ «ክብሩን ማን እንደሚያገኝ ባንጨነቅ፣ ምን ያህል ሥራ ሊሠራ እንደሚችል መረዳቱ አስገራሚ ነው።»

ለ. መሪዎች በነጻነት፣ በእውነተኛነትና በግልጽነት በመወያየት የተሻሉ ውሳኔዎችን ሊሰጡ ይችላሉ። ጥሩ ውሳኔዎች ሊተላለፉ የሚችሉት ሰዎች በጉዳዩ ላይ ያላቸውን አመለካከት በነጻነት ሲያካፍሉ ብቻ ነው። ሰዎች በአንድ ጉዳይ ላይ የተለያዩ አመለካከቶች ስላሏቸው፣ በሳል ሰዎች የተለያዩ አሳቦችን ለማካፈልና ከራሳቸው የሚለዩ አመለካከቶች ያሏቸውን ግለሰቦች አሳቦች ምንም ዓይነት የመከፋት ስሜት ሳይሰማቸው ሊሰሙ ይችላሉ። ሰዎች በአሳብ ከእኛ ሊለዩና ነገር ግን እንደ ግለሰቦች ሊያከብሩን የሚችሉ የመሆኑን እውነት መረዳት አለብን። አንድ ሰው እኛ ያልነውን አሳብ አልተቀበለንም ማለት አይወደንም ማለት አይደለም። ሰዎች ከእኛ አሳብ ጋር በማይስማሙበት ጊዜ የመጎዳት ስሜት የሚደርስብን ከሆነ፣ ከሌሎች ጋር በመተማመን ላይ የተመሠረተ ውጤታማ ተግባር ልናከናውን አንችልም። ብዙ ጊዜ ሰዎች በስብሰባ ላይ ከአሳባቸው ጋር ሳይስማሙ ሲቀሩ ውጥረት ይነግሣል። ይህ በራሳቸውና በእግዚአብሔር ላይ እምነት በማጣታቸው ምክንያት የሚፈጠር ያለመብሰል ምልክት ነው።

ሐ. መሪዎች የተሻሉ ውሳኔዎችን ሊያደርጉ ይችላሉ:: ሽማግሌዎች ለእግዚአብሔር መንግሥት ከሁሉም የሚሻለውን ነገር ለማድረግ የሚጨነቁ ከሆነ (ማቴ. 6:33) እና ሰዎች አሳባቸውን መቀበላቸው ወይም አለመቀበላቸው የማያሳስባቸው ከሆነ፣ በጣም የተሻሉ ውሳኔዎችን ሊያስተላልፉ ይችላሉ:: «ከዚህ ምን ጥቅም አገኛለሁ?» ወይም «ቤተሰቤና ጎሳዬ ክዚህ ምን ጥቅም ያገኛል?» ብለው አያስቡም:: የማንም ሰው ስሜት እንዳይጎዳ በሚያስችል መልኩ እንዴት አሳባቸውን እንደሚያለሳልሉ መጨነቅ ሳያስፈልጋቸው፣ «ለእግዚአብሔር መንግሥት ክሁሉም በላይ የሚሻለው የትኛው ነው?» ብለው ያስባሉ:: አመለካከታቸውን በግልጽ ለማንጸባረቅ ስለሚችሉ ደግሞ፣ የውሳኔዎቹ ጠቃሚ ገጽታ ዎች ይፋ ይወጣሉ:: ይህም መሪዎች ውሳኔዎቹ ሊያስገኙ የሚችሏቸውን ውጤቶች እንዲገነዘቡ ያስችላቸዋል::

ስለሆነም መሪዎች ሁሉ ለእግዚአብሔር መንግሥት ከሁሉም የሚሻለው ምን እንደ ሆነ ለመወሰን በሚሞክሩበት ጊዜ፣ እያንዳንዱ ሰው ይስቁብኛል ወይም ድብቅ ፍላጎት አለው ብለው ያስባሉ የሚል ስጋት ሳይገባው፣ በልቡ ውስጥ ያለውን አሳብ በድፍረት ሊናገር ይችላል:: በነጻነትና በግልጽነት ሊናገሩ ይችላሉ:: አንድ ሰው ክአሳባቸው ጋር በማይስማማበት ጊዜም፣ ምንም ሳይከፋቸው የሚናገረውን ለመስማት ይችላሉ::

መንፈሳዊና ግላዊ ብስለት መንፈሳዊ የሆነና በመተማመን ላይ የተመሠረተ ግንኙነት ለመፍጠር ያስችላል:: በዚህ ጊዜ ምእመናን ይተማመኑብናል፣ አመራራችንንም ይቀበላሉ፤ ሌሎችም መሪዎች ከመቃወም ይልቅ አብረውን ይሠራሉ:: አመራር በሰዎች መተ ማመን ላይ የተመሠረተ ነው:: የቤተ ክርስቲያን አባላት አመራራችንንና ውሳኔያችንን ሊቀበሉ የሚችሉት ከተማመኑብን ብቻ ነው:: ሌሎች የቤተ ክርስቲያን መሪዎችም የእግዚአብሔርን ሕዝብ በመምራቱ ሥራ ላይ በቅርብ ክእኛ ጋር ሊሠሩ የሚችሉት መተማመን ሲኖር ብቻ ነው::



8ኛ ጥያቄ:- ሀ) ከሽማግሌዎች መንፈሳዊ ወይም ግላዊ ብስለት ጉድለት ሳቢያ በቤተ ክርስቲያን ምእመናንና በቤተ ክርስቲያን መሪዎች መካከል የነበረው የመተማመን ግንኙነት ሲናድ ያየህበትን ሁኔታ አብራራ:: ለ) ምእመናን የመሪዎችን መንፈሳዊ ብስለት በማክበራቸው ምክንያት አመራር ቀሰል ብሎ የታየበትን ሁኔታ ግለጽ:: ሐ) የቤተ ክርስቲያን መሪ ዎች እርስ በርሳቸው ያላቸው መተማመን፣ መንፈሳዊ ብስለትና እውነትን በፍቅር የመናገር ችሎታ፣ እንዲሁም አብሮ የመሥራት ብቃት በሚሰጡት ውሳኔ ላይ እንዴት ተጽዕኖ እንደሚያሳድር ግለጽ::

## መሪዎች የቤተ ክርስቲያን ምእመናንን አመኔታ እንዴት ሊያገኙና ሊጠብቁ እንደሚችሉ

የሕዝቡን አመኔታና አክብሮት ለማግኘት፣ ሁልጊዜም ለእኛ መልካም አሳብና ስሜት እንዲኖራቸው ማድረግ ይኖርብናል:: የቤተ ክርስቲያን ምእመናን አንድን የቤተ ክርስቲያን መሪ ወዲያውኑ ሳያምኑት ይችላሉ:: በአመዛኙ በአመራር ላይ ያለውን ማንኛውንም ሰው ይጠራጠራሉ:: አመኔታ በጥረት የምናገኘው ነገር ነው:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሆነን በመመረጣችን ብቻ ሰ ዎች ይተማመኑብናል ማለት አይቻልም:: ለመሆኑ አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ ሰዎችን በውጤታማ መንገድ ለመምራት የሚያስችለውን ይህን አመኔታ የሚያገኘው እንዴት ነው? የመተ ማመንን ግንኙነት ማሳደግ በባንክ ቤት ገንዘብ እንደ ማጠራቀም ነው:: አንድ ሺህ ብር ቢኖርህና ቤት ውስጥ አንድ ሰው ይሠርቀኛ ል ብለህ ብታስብ፣ ወደ ባንክ ቤት ሄደህ ታስቀምጠዋለህ:: ክዚያ በኋላ በ500 ብር ቴፕ ትገዛለህ:: የደመወዝ ቀን ይደርስና 300 ብር ባንክ ትጨምራለህ:: በመቀጠል በ300 ብር ጫማና ልብስ ትገዛለህ:: በ150 ብር ደግሞ ሰዓት:: በዚህ ዓይነት በባንክ ደብተርህ ውስጥ ገንዘብ ስትጨምርና ስትቀንስ ትኖራለህ:: ገንዘብ ማውጣት የምትችለው ባንክ ቤት ውስጥ ያስቀመጥከው ነገር ካለ ብቻ ነው:: ምንም የተረፈ ገንዘብ ባንክ ቤት ከሌለህ፣ አንድ ነገር ለመግዛት ገንዘብ ልታወጣ አትችልም::

የግንኙነቶችም ሁኔታ ክዚህ ጋር ተመሳሳይነት አለው:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከምእመናን ወይም ከሌሎች መሪዎች ጋር

ጥሩና በመተማመን ላይ የተመሠረተ ግንኙነት ለመፍጠር ከፈለጉ፣ ጥሩ አስተሳሰቦችን በሰዎች ልብ ውስጥ ማጠራቀም አለባቸው። ይህ «የስሜት ባንክ» ተብሎ ሊጠራ ይችላል። ሰዎች አመራራችንን ሊያከብሩ የሚችሉት በእኛ ላይ ያላቸው መልካም አስተሳሰብ ከመጥፎ አስተሳሰብ በላይ ሚዛን የደፋ እንደ ሆነ ነው። መሪዎች የቤተ ክርስቲያን ምእመናን ስለ እኛ መልካም ስሜትን እንዲጨምሩና አሉታዊ ስሜትን እንዲቀንሱ ልናደርግ የምንችለው እንዴት ነው?

- ስማቸውን በማጥናት።
- የፍቅር መግለጫ የሆኑትን ነገሮች ማድረግ፤ ለምሳሌ፣ ሲታመሙ በመጠየቅ።
- በሁሉም ነገር እውነተኞች ሆነን በመገኘት።
- የሰጠናቸውን ቃል በማክበር። እናደርጋለን ያልነውን ነገር ማድረግ፣ እንመጣለን ባልነው ሰዓት በመምጣት።

ስለሆነም፣ ሰዎች የሚያከብሩትን ነገር ባደረግን ጊዜ ሁሉ፣ በልባቸው ውስጥ ስለ እኛ መልካም ስሜት እንዲኖራቸው እናደርጋለን። ወይም ደግሞ አብረውን የሚያገለግሉ ሽማግሌዎች ከሆኑ፣ በጥንቃቄ አሳባቸውን ስንሰማ፣ ወይም የክብርን ስፍራ እንዲያገኙ ስናደርግ፣ ወይም ሥራቸውን በአግባቡ እንደሚወጡ ስናምን፣ በእኛ ላይ አመኔታ ይኖራቸውና አመራራችንን ይቀበላሉ።

ነገር ግን የማይገባ ነገር በምናደርግበት ጊዜ፣ ከስሜታዊው ባንክ ወጪ እያደረግን ነው ማለት ነው። የሚከተሉት ነገሮች በልባቸው ውስጥ ካስቀመጥነው መልካም ስሜት አመኔታቸውን የሚቀንሱብን ናቸው፦

- እሑድ ዕለት ሰላምታ ሳንሰጣቸው ስንቀር።
- ቀጠሮ ሳናከብር ስንቀር።
- ለችግራቸው ግድየለሽ ስንሆንና ሳንጎበኛቸው ስንቀር።
- የነገሩንን ምሥጢር ስናባክን።



- ሥልጣናችንን ተጠቅመን እኛ ልናደርግ የማንፈልገውን ነገር እንዲያደርጉ ስናዝዛቸው።
- የሌሎች መሪዎችን አሳብ ባለመስማት የእኛን አሳብ ብቻ እንዲከተሉ ስንጠይቅ።
- ሰዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተለያዩ ተግባራትን እንዲያከናውኑ ሳናምናቸው ስንቀርና ውሳኔዎችን ሁሉ ራሳችን ስንሰጥ።
- ስለ እነርሱ ለሌሎች መሪዎች ስናማ።

ሰዎች በልባቸው ለእኛ ጥሩ ስሜት እስካላቸው ድረስ ያከብሩናል፣ አመኔታም ይኖራቸዋል። ይህም አመራራችን ቀለል ባለ መንገድ በጥሩ ሁኔታ እንዲቀጥል ያደርገዋል። ብንሳሳት ወይም የማይረባ ውሳኔ ብንሰጥ፣ ይቅር ይሉናል። የመረጃ ልውውጡ በጥሩ ሁኔታ ሳይካሄድ ቢቀር፣ ጥሩ ምክንያት ቢኖራቸው ነው ብለው ያስባሉ። ለምሳሌ፣ ሥራ በዝቶባቸው ይሆናል ብለው ያልፋሉ። ልናታልላቸው ወይም ልንጠቀምባቸው እንደምንፈልግ አያስቡም። ምን እያሰቡ ይሆን? ብለን ሳንጨናነቅ በነጻነትና በግልጽ ልናወያያቸው እንችላለን።

ነገር ግን ለእኛ ያላቸው መልካም አመለካከት አነስተኛ ከሆነ፣ ሰዎች ይጠረጥሩናል። ለእኛ ጥሩ ስሜት ከሌላቸው፣ ምእመናን በሁሉም ውሳኔዎች ውስጥ ልባዊ ፍላጎታችንን ይጠራጠራሉ። ብንሳሳት ወይም የማይወዱትን ወሳኔ ብናስተላልፍ፣ አንዳንድ ምእመናን ወዲያው የቃላት ጦርነት ይከፍቱብናል። ውሳኔውን በአግባቡ ሳናሳውቃቸው ብንቀር፣ ልናታልላቸው የምንፈልግ ይመስላቸዋል። ከሌሎች መሪዎች ጋር በምንገናኝበት ጊዜ ሁሉ፣ ንግግራችን በሌላ መልኩ እንዳይተረጎም እንጠነቀቃለን። ሰዎች የማይወዱትን ወይም ትልቅ ተጽዕኖ ሊያመጣ የሚችል ውሳኔ ማድረግ ቢኖርብን፣ ለእኛ መልካም ስሜትና አመኔታ ከሌላቸው፣ ክፍፍል ሊፈጠር ይችላል። በሰዎች ላይ ተጽዕኖ ልናሳድር የምንችለው ለእኛ መልካም ስሜትና አመኔታ ያላቸው እንደ ሆነ ብቻ ነው።

ከሰዎች ጋር የቅርብ ግንኙነት በሚኖረን ጊዜ፣ በስሜት ባንኩ ውስጥ ጥሩ ነገሮች ማጠራቀማችንን መቀጠል አለብን:: በየእሑዱ የምናገለግላቸው ምእመናን እና አብረውን የሚያገለግሉት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ስለ እኛ መልካም አመለካከት እንዲኖራቸው መጣራችንን መቀጠል አለብን:: የቅርባችን ለሆኑት ሰዎች (ለምሳሌ፣ የትዳር ጓደኞችን፣ ልጆቻችን፣ አብረውን የሚሠሩና የሚያገለግሉ) የስሜት ባንክ መጨመርና መቀነስ በፍጥነት ይከናወናል:: የሚያስደስቷቸውን ነገሮች (ለምሳሌ፣ በሰዓቱ ቀጠሮ ቦታ መገኘት፣ ለቤተሰብ ፍቅርን ማሳየት፣ ወዘተ. . .) በምናደርግላቸው ጊዜ የስሜታዊው ባንኩ ክምችት በፍጥነት ይጨምራል:: ጥሩ ያልሆኑ ነገሮች (ለምሳሌ፣ ሰላምታ አለመስጠት፣ ታጋሽ አለመሆን፣ ሐሜት፣ ቁጣ፣ ወዘተ. . .) በፍጥነት መልካም ስሜቶችን ከባንኩ ይቀንሳሉ:: ብዙውን ጊዜ የቅርብ ግንኙነቶቻችንን ቸል የምንል ይመስላል:: ለምሳሌ፣ ብዙ ባሎች ሚስቶቻችንን እንደ ዋዛ በመመልከት መልካም ነገሮችን ሳናደርግላቸው እንቀራለን:: ይህም ግንኙነቶቻችንን በማበላሸት ጸብን ይፈጥራል::

ነገር ግን ሁልጊዜ በማናገኛቸው ሰዎች ስሜታዊ ባንክ ውስጥ ባለማቋረጥ መልካም ነገሮችን ማጠራቀም ላያስፈልገን ይችላል:: ነገር ግን በምናገኛቸው ጊዜ ሁሉ መከባበርን በሚጨምር መንገድ ግንኙነታችንን መቀጠል አለብን:: ስለ እኛ ጥሩ አመለካከት እንዲኖራቸው ካደረግን፣ በሚቀጥለው ጊዜ እስኪያገኙን ድረስ ስሜታቸው ጥሩ ሆኖ ሊቆይ ይችላል:: ስለሆነም፣ አንድ እንግዳ ሰው ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲመጣ ፍቅር ብንሰጠውና መልካም አቀባበል ብናደርግለት፣ አመለካከቱን የሚቀይር መጥፎ ነገር እስክናደርግበት ድረስ ወዳጆቹ አድርጎ ሲያየን ይኖራል:: ነገር ግን ያ የመጀመሪያው ቀን ጉብኝቱ መልካም ሆኖ ካልተገኘ፣ ሁል ጊዜም የወዳጅነት ስሜት ያለን ቤተ ክርስቲያን አለመሆናችንን ሲያስብ ይኖራል:: ወይም ደግሞ የዋናውን ጽ/ቤት መሪ ከስንት ቀን አንድ ጊዜ ብናገኘው፣ ስለ እኛ ያለው ግንዛቤ የሚመሠረተው በዚያው ግንኙነት ላይ ነው:: ስሜታዊ ባንኩ በየጊዜው እንዲሞላ ማድረግ አያስፈልገንም:: (ማስታወሻ:- ይህም ማለት ስልክ



እንድንደውልላቸው፣ ደብዳቤዎችን እንድንጽፍላቸው ወይም ሪፖርት እንድንልክላቸው አይጠብቁም ማለት ነው:: ሰዎች እነዚህን ነገሮች የሚጠብቁ ከሆነ፣ እነዚህን ነገሮች አለማድረጉ ከስሜታዊ ባንካቸው መልካም ነገሮችን እንዲቀንሱ ያደርጋል::)

ስለሆነም የመልካም ፈቃድና የእመኔታ ስሜታቸውን ለማጠናከር የሚያስችሉትን ነገሮች ባለማቋረጥ ማድረግ ያለብን ከቅርባችን ላሉት ሰዎች መሆን አለበት::

| |
|---|
| 9ኛ ጥያቄ:- ሀ) በየጊዜው የምታገኛቸውን ሰዎች ስም ዘርዝር:: ለ) በልባቸው ውስጥ ያለህ የስሜታዊ ባንክ መጠን ምን ያህል ይመስልሃል? ሐ) ሰዎች ከአንተ ጋር ጥሩ ግንኙነት የሌላቸው በመሆኑ ምክንያት የፈጸምከው ትንሽ ስሕተት የግንዛቤ መዛባትን በመፍጠር የስሜት መጎዳት ያስከተለበትን ሁኔታ ግለጽ:: መ) ከአርሱ ጋር ካለህ መልካም ግንኙነት የተነሣ በጥሩ ሁኔታ ላላከናወንከው ተግባር ቅያሜ ያልተፈጠረበትን ሌላ አጋጣሚ ጥቀስ:: ሠ) በቅርብ የምታገኛቸውን ሰዎች የመልካም ስሜት ደረጃ ከፍ ለማድረግ በዚህ ሳምንት ልታደርግ የምትችላቸውን ነገሮች ዘርዝር:: በዚህ ሳምንት ብቻ ሳይሆን በሚቀጥሉት ወራትና ዓመታትም እነዚህን ነገሮች በማድረግ ግንኙነትህን ለማሳደግ ሞክር:: |

## ከሌሎች የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና ምእመናን ጋር ያለንን ግንኙነት ለማሳደግ የሚያግዙ ስድስት መንገዶች

1. ሰውን እንደ ግለሰብ ቀረብ ብለህ እወቅ:: የሚወደውንና የሚጠላውን ነገር እወቅ:: የሚወዳቸውን/የምትወዳቸውን ነገሮች አድርግ:: የማይወደውን/የማትወደውን ነገር ላለማድረግ ተጠንቀቅ:: ለምሳሌ፣ ግለሰቡ ሰብሰባ ላይ አርፍዶ መገኘትን የሚጠላ ከሆነ፣ በስዓቱ ለመድረስ ጥረት አድርግ:: እንግልጋይ መሆን ማለት ሌላውን ሰው ለማስደሰት ስትል ነገሮችን ታስተካክላለህ ማለት ነው (1ኛ ቆሮ. 9:19-23):: ለራስ ወዳድነት ምክንያቶች ብለህ ከሰዎች ጋር ግንኙነት መመሥረት የለብህም:: «ይህንን ሰውዬ/ይህቺን ሴትዮ እራት ብጋብዝ፣ ገንዘብ እንዲያበድረኝ/እንድታበድረኝ ለመጠየቅ እችላለሁ:: እራቱ/ቷን በልቶ/ታ መቼም እይሆንም ለማለት መቸገሩ የማይቀር ነው፣» የሚል አመለካከት ካለህ ምን ጊዜም በፍቅርና

በመተማመን ላይ የተመሠረተ ግንኙነት ልትመሠርት አትችልም። ሰዎች የራስ ወዳድነት ምክንያቶቻችንን ማወቃቸው ስለማይቀር፣ እንዲህ ዓይነት ነገሮች ብዙም ትርጉም አይሰጧቸውም።

የራስ ወዳድነት ድርጊቶች ጥሩ ስሜቶችን እያዳብሩም። ሰዎች እኛ የምንወዳቸውን እና የሚያስደስቱንን፣ እንዲሁም ለእኛ የሚያስፈልጉንን ነገሮች እንዲያደርጉልን እንደምንፈልግ፣ እኛም ለሰዎች እንዲሁ ማድረግ ያስፈልገናል (ማቴ. 7:12)። ይህ ማለት ንግግራችን ስለ ሰዎቹ እንጂ ስለ ራሳችን ሊሆን አይገባም። ይህም ማለት ስለ ቤተሰቦቻቸው ልናውቅና ከልብ በመነጨ ስሜት ልንጠይቃቸው ይገባል ማለት ነው። ወይም ደግሞ እነርሱ ስለሚያደርጓቸውና ብዙ ትርጉም ስለሚሰጧቸው ለየት ያሉ ነገሮች እንጠይቃቸዋለን። ለሰዎች ሕይወት እውነተኛ ፍላጎት በምናሳይበት ጊዜ፣ ፍቅራችንን እና አክብሮታችንን ማንጸባረቃችን ነው። አንድ ሰው ስለ እኛ ግድ እንደሚሰው ስናውቅ፣ እኛም በተራችን እናምናቸዋለን፣ እንዲሁም ስለ እነርሱም ግድ ይለናል።

**10ኛ ጥያቄ፡- አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ ለአንድ ምእመን በግል እንደሚያስብለት ለማሳየት ሊያደርግ የሚችላቸውን አምስት ነገሮች ዘርዝር።**

**11ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ለአንድ ሰው የግል ቀረቤታ ማሳየት ግለሰቡ እንዴት በበለጠ እንዲያከብርህ እንዳደረገ ከራስህ ተሞክሮ ምሳሌ ስጥ። ለ) ሥራ የሚበዛባቸው የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለምእመናን የግል ቀረቤታ ለማሳየት ሊያደርጉ የሚችሏቸውን ነገሮች ዘርዝር። ሐ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ብዙውን ጊዜ የሚያደርጓቸውና ግላዊ ቀረቤታ ለመፍጠር ባለመቻላቸው ምእመናን እንዳይተማመኑባቸው ወይም ጥሩ ስሜት እንዳይኖራቸው የሚያደርጉትን ነገሮች ዘርዝር።**

2. <u>ግንኙነቶችን እስደሳች የሚያደርጉትን ትናንሽ ነገሮች ማስታወስ</u>። ብዙውን ጊዜ የገንዘብ ስጦታ፣ ምሳ ወይም እራት መጋበዝ ወይም ገጸ በረከት የመሳሰሉትን ትልልቅ ነገሮች እናስባለን። ነገር ግን ጥሩ ግንኙነቶችን ለመፍጠር ቀላል የሚመስሉና ለሰዎች ትርጉም የሚሰጡ ነገሮችን ማድረጉ አስፈላጊ ነው። ለምሳሌ ያህል፣ እንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ የአንድን



ምእመን ስም፣ የሚስቱን ወይም የልጆቹን ስም ማወቁ ትንሽ ነገር ሊመስል ይችላል። ለምእመኑ ግን ብዙ መልእክቶችን ያስተላልፋል። «ይህ የቤተ ክርስቲያናችን ሽማግሌ ስሜን ማወቁና የልጆቼን ጤንነት መጠየቁ አስገራሚ ነገር ነው። ስለ እኔ ምንም ግድ የሌለው ነበር የሚመስለኝ፣» ሊል ይችላል። ይህ ከቤተ ክርስቲያን አየወጡ ሳለ ስሙን ጠርቶ ሰላምታ ስለ ሰጠው ብቻ በአእምሮው ውስጥ የሚቀር መልካም እስተሳሰብ ነው። ከቤተ ክርስቲያን ሲወጡ ሰላምታ መስጠት ወይም፣ «ቤተ ክርስቲያኑን ስታጸዳው እይቻለሁ። ለጥሩ ሥራህ አመሰግናለሁ» ማለቱ፣ ለሰዎች እንደምታስብ በሚገባ ያሳያል። ነገር ግን ሰላም የማትላቸው ከሆነ፣ ስሜታቸው ይጎዳና በልባቸው ውስጥ ስለ አንተ የነበራቸው መልካም አስተሳሰብ ይቀንሳል። አብዛኞቹ ሰዎች ስሜታዊነት ስለሚያጠቃቸው፣ በቀላሉ ሊጎዱ ይችላሉ።

3. <u>ለሰዎች የገባኸውን ቃል ፈጽም</u>። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሕዝቡን መልካም ስሜት ከሚቀንሱባቸው ዓበይት መንገዶች አንዱ ሕዝቡ ቃል ኪዳን ነው ብለው የሚያስቡትን ነገር መናገርና ሳይፈጽሙ መቅረት ነው። ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች የተገባው ቃል ብዙም እርባና ያለው ላይመስል ይችላል። ለምሳሌ፣ እንድ አባል ወደ ትልቅ ከተማ እንደምንሄድ ሰምቶ እስክሪብቶ እንድንገዛለት ቢጠይቅና እሺ ብለን ከሄድን በኋላ ረስተን ባንገዛ፣ የግለሰቡ ስሜት ስለሚጎዳ፣ ለእኛ የነበረው አክብሮት ይቀንሳል። ወይም ቀጠሮ ይዘን ብንቀር ወይም በሰዓቱ ባንደርስ፣ በጣም ሊጎዱ ይችላሉ። በመሆኑም፣ ልንፈጽም የማንችለውን ቃል መግባት የለብንም። ለአንድ ሰው አንድ ቃል ከገባን በኋላ እንዳንፈጽም የሚያደርግ ችግር ቢከሰት፣ የተከሰተውን ነገር ቃል ከማፍረሉ ውጤት ጋር ማመዛዘን አለብን። የሚበልጠው የትኛው ነው? ሻይ ከጋበዘን ወዳጃችን ጋር መጫወት ነው ወይስ ለቤተ ክርስቲያን አባል የሰጠነውን ቀጠሮ ማክበር? ጓደኞችን ቀደም ተብሎ የተያዘ ቀጠሮ እንዳለብን ብንነግረው ሊረዳንና ሌላ ቀን ለመገናኘት ፈቃደኛ ሊሆን ይችላል። እባሉ ግን በቀጠሮው ቀን ብንቀር፣ ስሜቱ ሊጎዳና ከእንግዲህ ቃላችንን ለማመን ሊቸገር ይችላል። በቤተ ክርስቲያን ላይ ከሚያስከትሉት ተጽዕኖ አንጻር ቃላችንን በአግባቡ መጠበቅ

አለብን:: (ማስታወሻ:- በተጨማሪም ቃል ከገባን በኋላ ቃላችንን ለመጠበቅ የምንችለውን ጥረት ሁሉ ማድረግ እንዳለብን መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረንን ማስታወስ አለብን::) ቀጠሮአችንን መሰረዝ ያለብን ለእግዚአብሔር ሥራ የበለጠ ጠቀሜታ የሚኖረው ጉዳይ ከገጠመን ብቻ ነው:: (ለምሳሌ፣ የቤተሰባችን አባል የሆነ ሰው ቢታመምና ወደ ሆስፒታል መወሰድ ካለበት::) እንዲህ ዓይነት ሁኔታ ከገጠመን ደግሞ፣ በተቻለ ፍጥነት ለቀረንበት ግለሰብ ሁኔታውን ማሳወቅና ይቅርታ መጠየቅ አለብን:: ሰዎች ቃላችንን ሲያከብሩ ምክራችንን ይሰማሉ:: አመኔታቸውም ከአንድ ሁኔታ ወደ ጠቅላላው አመራራችን እያደገ ይሄዳል::

| |
|---|
| 12ኛ ጥያቄ:- ሀ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለማኅበረ ምእመናቸው ብዙውን ጊዜ የሚገቧቸውን ቃሎች ዘርዝር:: ለ) መሪዎች እንዳንድ ጊዜ እነዚህን ቃሎች የሚያፈርሱባቸውን ሁኔታዎች ግለጽ:: ሐ) የቃሎቹ መፍረስ በምእመናን ላይ የሚያስከትለው ተጽዕኖ ምንድን ነው? |

4. የምንጠብቃቸውን ነገሮች ግልጽ ማድረግ:: አለመተማመንና የስሜት መጎዳት እንዲከሰት ከሚያደርጉት ነገሮች አንዱ በአንድ ሁኔታ ውስጥ ሁለት ሰዎች የተለያዩ ነገሮችን የሚጠብቁ መሆናቸው ነው:: ለምሳሌ፣ አንድ ሰው በወርሐዊ ስብሰባችን ላይ እየተገኘ ሪፖርት እንዲያቀርብ እንጠይቀዋለን:: ግለሰቡ በስብሰባው ላይ ለሠላሳ ደቂቃ እናገራለሁ ብሎ ቢያስብና እኛ ግን አምስት ደቂቃ ብቻ ብንሰጠው፣ ስሜቱ ሊጎዳ ይችላል:: ለሥራው ብዙም ትኩረት እንዳልተሰጠው ያስባል:: ነገር ግን መጀመሪያውኑ አምስት ደቂቃ ብቻ እንደሚሰጠው ቢያውቅ፣ የሰብሰባው ሰዓት የተጣበበ መሆኑን ስለሚረዳ፣ ስሜቱ አይጎዳም:: በቤተ ክርስቲያን አምልኮም ሁኔታው ተመሳሳይ ነው:: የፕሮግራም መሪው ጥቂት መዝሙሮችን (ለ20 ደቂቃዎች ያህል) ብቻ ያዘምራል ብለን ብናስብና እርሱ ግን «መንፈስ እስከ መራኝ ድረስ እቀጥላለሁ» ቢል፣ በእርሱና በቤተ ክርስቲያን መሪዎቹ መካከል ችግር ሊፈጠር ይችላል:: ወይም አንድ ኮሚቴ በአንድ ጉዳይ (የወንጌል ስርጭት) ላይ ብቻ ለመሥራት ቢያስብና የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ግን ኮሚቴው በሁሉም መንፈሳዊ አገልግሎቶች ላይ መሳተፍ እንዳለበት ቢጠብቁ፣ ሰይጣን ይህንን የአሳብ ልዩነት ተጠቅሞ ውጥረትን



ሊያነግሥ ይችላል:: ባለፈው ሳምንት እንደተመለከትነው፣ ውክልና በሚሰጥበት ጊዜ አንድ ሰው የሚያከናውነው ተግባር በግልጽ መብራራት፣ ግንዛቤ ማግኘትና ስምምነትን ማግኘት አለበት:: ከሌሎች መሪዎች ጋር ባለን ግንኙነት፣ ይህ የጋራ ግንዛቤ ከተጓደለ፣ ብዙም ሳይቆይ ውጥረቶች ይጎለብታሉ:: ሽማግሌዎች መጋቢው የእኛ ኃላፊነት ነው የሚሉትን ሥራ ብቻውን እያከናወነ ነው ብለው የሚያስቡ ከሆነ፣ የግንኙነቶች መሻከር ይፈጠራል:: ይህ ደግሞ አንድን አሳብ በተለያዩ መንገዶች መረዳትን፣ አለመተማመንንና አለመተባበርን ያስከትላል::

| |
|---|
| 13ኛ ጥያቄ:- ሀ) በሰዎች መካከል የተለያዩ ነገሮችን መጠበቅ ውጥረትንና አለመተማመንን ሲፈጥር የተመለከትክባቸውን ሁኔታዎች በምሳሌነት ዘርዝር:: እነዚህ ሁኔታዎች ምን እንዳስከተሉ ግለጽ:: ለ) የሚጠበቀውን ነገር ሁሉም ሰው በግልጽ እንዲያውቅ ሁኔታውን እንዴት ማስተካከል ይቻል የነበረ ይመስልሃል? ሐ) ሁለቱም ወገኖች ከመጀመሪያው የሚጠብቁትን ነገር በትክክል ቢያውቁ ኖሮ ውጤቱ እንዴት ይለወጥ ነበር? |

5. የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ግላዊ እውነተኛነትን በማሳየት አመኔታን ይመሠርታሉ:: ሰዎች ሌሎች በማይደግፉን ጊዜ እንኳን መሪዎች አቋማቸውን ይዘው ሲዘልቁ በሚመለከቱ ጊዜ፣ ለመሪዎቹ ያላቸው አክብሮት ይጨምራል:: በአሳባችን ሳይስማሙ ቢችሉም፣ ቃላችንን የምንጠብቅ ሰዎች መሆናችንንና ቃላችንን ለመቀየር የማንፈልግባቸው መመዘኛዎች እንዳሉን ይረዳሉ:: ለማማት ወይም ስለ ሌላ መሪ ክፉ ነገር ለመናገር ሳንፈልግ ስንቀር፣ ሰዎች ያከብሩናል:: ስለ እነርሱም ቢሆን ሊሰሙን በማይችሉ ጊዜ ክፉ ነገር እንደማንናገር ያውቃሉ:: ነገር ግን ስለ ሌላ መሪ ክፉ ቃል ከተናገርን፣ በእኛ ላይ አመኔታ አይኖራቸውም:: ስለ እኔም በሌላ ቦታ ክፉ ነገር ይናገር ይሆን? የሚል ስጋት ያድርባቸዋል:: ነገር ግን በግልጽ ትክክል አለመሆኑ ያልተረጋገጠበትን ሌላ መሪ ጥብቅና በመቆም አሳባቸውን እንደገና እንዲያጤኑ በምናደርግበት ጊዜ፣ ሰዎችን ከማቁሰል ይልቅ ሕይወታቸውን ለመገንባት እንደምንፈልግ ይገነዘባሉ:: ለአንድ ሰው «ምሥጢር» ነው የሚባል ነገር ብትነግረው፣ መጀመሪያ

ስላመንከው ደስ ይለዋል። በኋላ ግን፣ የአኔንም ምሥጢር ለሌላ ሰው እየተናገረ ይሆን? ብለው መስጋታቸው አይቀርም። እውነተኛነት ማለት ሁሉንም ሰው በእኩል መንገድ ማስተናገድ ነው። ለእንደኛው ሠራተኛ ልዩ ችሮታ አድርገን ለሌላው እንነፈገውም ማለት ነው። አንደ መሪ ሰዎችን (ማን ይሁን ማን) ለፈጸሙት ጥፋት በእግዚአብሔር ላይ ተመሥርተህ በፍቅር ስታጋፍጥ፣ ሰዎች ስለ አንተ ያላቸው አክብሮት ይጨምራል። ይህ መጀመሪያ ሊጎዳ የሚችል ቢሆንም፣ በፍቅር ልትረዳቸው አንደምትፈልግ ይገነዘባሉ። ነገሮችን ሁሉ ፊት ለፊት እንደምትናገር እንጂ በሌላ በታ እንደማትተቻቸው ያውቃሉ። እንዲሁም፣ እውነተኛነት ማለት የትኛውንም ዓይነት የማታለያ ንግግር እናስወግዳለን ማለት ነው። ሰዎች አታላዮች መሆናችንን በሚያውቁበት ጊዜ፣ ከእነርሱ ጋር ያለን የእሳብ ልውውጥ እውነተኛ ነው ብለው አያምኑም። ሁልጊዜም ሊሸውደኝ እየሞከረ ይሆን? ብለው ያስባሉ።

> 14ኛ ጥያ:- ሀ) አንድ መሪ እውነተኛ ባሕርይ ሊያሳይ የሚችልባቸውን ሁኔታዎች ዘርዝር። ለ) በዚያ ሁኔታ ውስጥ እውነተኛ ባሕርይ ማሳየት እንዴት የሰዎችን ከበሬታ እንዲያገኝ እንደሚያስችለው ግለጽ። ሐ) ብዙውን ጊዜ አንድ መሪ እውነተኛነትን የማያሳይባቸውን መንገዶች ጥቀስ። መ) ይህ ሰዎች በእርሱ ላይ ባላቸው ከበሬታና አመኔታ ላይ የሚያስከትለውን ለውጥ ግለጽ።

6. የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሰውን ስሜት የጎዱበትና ይህም ከበሬታቸውን የቀነሰበት ሁኔታ በሚፈጠርበት ጊዜ፣ ይቅርታ በመጠየቅ ሊከበሩ ይችላሉ። ብዙውን ጊዜ ይቅርታ ከጠየቅን፣ ወይም ድክመታችንን ካሳየን፣ ሰዎች እምብዛም አያከብሩንም ብለን እናስባለን። እውነቱ ግን ተገላቢጦሹ ነው። አንድ መሪ መሳሳቱን አውቆ በራሱ አነሣሽነት ወደ ተበዳዩ በመሄድ፣ «ተሳስቻለሁና ይቅርታ አድርግልኝ» ቢል፣ ሰዎች ለእርሱ ያላቸው እክብሮት በጣም ይጨምራል። ይህ አመኔታቸውን ያሳድገዋል።

ነገር ግን መሪዎች ይቅርታ ከጠየቁ በኋላ ማመካኛ መጨመር የለባቸውም። ብዙውን ጊዜ፣ «ይቅርታ አድርግልኝ ለተናገርኩት እውነተኛ ያልሆነ ነገር። ይህ የሆነው ግን በዚህ ምክንያት ነው»



ወደ ማለቱ እናዘነብላለን። በይቅርታው ላይ ማመካኛ በምንጨምርበት ጊዜ፣ ለተፈጸመው ጥፋት ኃላፊነት አንወስድም ማለት ነው። የተናገርነው ውሸት የእኛ ጥፋት ሳይሆን፣ የሁኔታዎች ጥፋት ነው እያልን ነው። ነገር ግን በምንዋሽበት ጊዜ ሁሉ ጥፋቱ የራሳችን እንጂ የሌላ ሰው ወይም የሁኔታዎች አለመሆኑን መረዳት አለብን። ማመካኛ በምንጨምርበት ጊዜ፣ ሰዎች ይቅርታችን ልባዊ እንዳልሆነ ያስባሉ። በኃጢአታችን ላይ ማመካኛ በመጨመራችን፣ ግለሰቡ ለእኛ ባለው እክብሮት የሚያድግበትን ዕድል እናጠብበዋለን። ለፈጸምነው ጥፋት ኃላፊነት በማንወስድበት ጊዜ፣ እውነተኞች አይደለንም ማለት ነው። እንዲሁም ደግሞ ሰዎችን የሚጎዳ ነገር ማድረጋችንን እየቀጠልን በተደጋጋሚ ይቅርታ የምንጠይቅ ከሆነ፣ ትርጉም የለውም። ሁልጊዜም የምናረፍድ ወይም ሰው ቀጥረን የምንቀር ከሆነ፣ ይቅርታ መጠየቁ ዋጋ የለውም። ለመለወጥ ጥረት የማናደርግ ከሆነ፣ ሰዎች ይቅርታችን ልባዊ እንዳልሆነ ያውቃሉ። ለምናደርጋቸው ነገሮች ከልባችን ይቅርታ አለመጠየቃችንን (ወይም አለማዘናችንን) ያውቁና ጭራሽ ይንቁናል። ከእግዚአብሔር የሆነ ኀዘን ሁልጊዜም ወደ ይቅርታና ለውጥ ይመራል። (2ኛ ቆሮ. 7:8-11 አንብብ።)

ሰዎች የልብ ፍላጎታችን መልካም ሆኖ ሳለ ስሕተት መፈጸማችንን በግልጽ በምንገልጽላቸው ጊዜ ይቅርታ ለማድረግ ፈቃደኞች ይሆናሉ። ነገር ግን የስሕተቶቹ ምንጭ አንድን ሰው እንደ መጉዳት፣ ወይም የራስን ስሕተት እንደ መሸፈን ያለ ክፉ ልብ መሆኑን በሚገነዘቡበት ጊዜ ይቅር ለማለት ይቸገራሉ።

ጳውሎስ በቁጣችሁ ላይ ፀሐይ አይግባ ሲል ያስጠነቅቀናል (ኤፌ. 4:26)። ይህን ሲል የፈጠርነውን የስሜት መጎዳት በፍጥነት መጠገን አለብን ማለቱ ነው። ይቅርታ ሳንጠይቅ በምንቆይበት ጊዜ፣ ንዴቱና የስሜት ጉዳቱ እየጠለቀ ይሄዳል። ጥልቅ ንዴትና የስሜት መጎዳት ካለ ደግሞ፣ ግንኙነትን መልሶ ማደሱ ከባድ ይሆናል። ነገር ግን አንድን ሰው እንደ ጎዳን ባወቅን ጊዜ፣ ወዲያውኑ ይቅርታ ብንጠይቅ፣ ግንኙነቱንና ግለሰቡ ለእኛ ያለውን አመኔታ መልሶ መጠገኑ ይቀላል። አንደ ቤተ ክርስቲያን መሪ

ዎች፣ የስሜት መጎዳት በሚኖርበት ጊዜ (አንድን ሰው ከጎዳኝ ወይም እነርሱ ከጎዱን)፣ በተቻለ ፍጥነት ችግሩን ለማስወገድ ብንሞክር፣ ግንኙነቱን መፈወስና ጉዳቱን መቀነስ እንደሚቀል መ ረዳት አለብን።

> 15ኛ ጥያቄ፦ ሀ) ለመሪዎች ለፈጠሩት ስሕተት ይቅርታ መጠየቅ ከባድ የሚሆንባቸው ለምንድን ነው? ብዙውን ጊዜ ስስሕተታችን ማመካኛ የምንፈልገው ለምንድን ነው? ለ) መሪው ይቅርታ ባለመጠየቁ ምክንያት አለመተማመን እያደገ የመጣበትን ሁኔታ ግለጽ። ሐ) አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ ከልቡ ይቅርታ በመጠየቁ ሰዎች ቀደም ሲል የነበራቸውን አክብሮት እንዴት መስጠታቸውን እንደ ቀጠሉ ግለጽ። መ) መሪዎች ይቅርታ ለመጠየቅ ፈቃደኞች መሆን አለባቸው የምትልባቸውን ሁኔታ ዎች ግለጽ።

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከሌሎች ጋር ያላቸውን ግንኙነት ለመገንባት የሚያግዙ ሌሎች እውነቶች፦

*1.* በሰዎች መካከል መተማመን ለመገንባት ትልቁ ነገር በሁኔታዎች ላይ ያልተመሠረተ ፍቅር ነው። ሰዎች በማይሳካላቸው ጊዜ ሳይቀር እንደምንወዳቸውና እንደምንቀበላቸው በሚያውቁበት ጊዜ፣ ከእኛ ጋር ያላቸው ግንኙነት አስተማማኝ ይሆናል። ለእኛ ጠቃሚ ሰዎች መሆናቸውን ከተረዱ፣ ለዕድገትና ለውጥ የሚያግዛቸውን ነገር እንድናደርግላቸው ፈቃደኞች ይሆናሉ - ምንም እንኳን ይህ ተግሣጽንም የሚጨምር ቢሆንም እንኳን። ነገር ግን ከራሳችን ጓደኞች፣ ቤተሰቦች ወይም የኀላ አባላት ጋር ብቻ የምንዛመድ መሆናችንን ካወቁ፣ እንዲሁም ፍቅራችን ነገሮችን ጥሩ አድርገው በማከናወናቸው ላይ የሚመሠረት ከሆነ፣ ለእኛ ብዙም አክብሮት አይኖራቸውም፣ አይሰሙንምም።

ስለሆነም፣ እውነተኛ ፍቅር ምን እንደ ሆነ መረዳቱ ጠቃሚ ነው።

*ሀ.* ፍቅር ማለት ለግለሰቡ ከሁሉም የሚሻለውን ነገር መፈለግ ማለት ነው። ፍቅር ማለት ግለሰቡ የሚፈልገውን ብቻ ማድረግ አይደለም። ወላጅ ልጁን ስለሚወደው ጥያቄዎቹን የማይቀበልበት ጊዜ ይኖራል። እንደ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች፣ ለሰ



ዎች ፍቅር የምንገልጸው፣ ለእነርሱ ከሁሉም የሚሻለውን ነገር በሚያስገኝ መልኩ እንጂ፣ አንድን ነገር ስለ ፈለጉ ወይም ስለ ጠየቁን ያንኑ በማድረግ ላይ ያተኮረ መሆን የለበትም።

ለ. ፍቅር ማለት ሰዎች የሚያደርጉትን ሁሉ ትክክል ነው ብለን እናጸድቃለን ማለት አይደለም። ከዚህ ይልቅ፣ ፍቅር ሰዎችን ለኃጢአታቸው ወይም ለፈጸሙት የተሳሳተ ነገር እንድናጋፍጣቸው ያነሣሣናል (ገላ. 6:1)። ይሁንና፣ ይህንን የምናደርገው እንዲያድጉ ከመፈለግ እንጂ፣ ልንቀጣቸው በማሰብ አይደለም። ሰዎች ምንም እንኳን ድርጊታቸውን ባንደግፍና የቤተ ክርስቲያን ቅጣት ብንሰጣቸውም፣ የምንወዳቸውና እንዲያድጉ የምንረዳቸው መሆኑን ካወቁ፣ ያከብሩናል። ነገር ግን ለእነርሱ ያለንን ፍቅር ካላወቁ፣ እንዲታዘዙን ለማድረግ ኃይላችንን ለመጠቀም የምንፈልግ መሆናችንን ከተረዱ፣ ወይም ለግል ሕይወታቸው ግድየለሾች መስለን ከታየናቸው፣ ለምንሰጣቸው ቅጣት የሚኖራቸው ምላሽ አሉታዊ ይሆናል። እንዴት ሥራቸውን እንደሚያሻሽሉ፣ እንዴት እግዚአብሔርን በሚያስከብር መንገድ ሊኖሩ እንደሚችሉ ወይም አንዳንድ ጊዜ ለሚያነሷቸው ጥያቄዎች የምንሰጣቸውን አሳብ አይቀበሉም። ይህ በተለይ፣ ሚስቶቻችንን፣ ልጆቻችንንና አብረውን የሚያገለግሉትን ሽማግሌዎች ጨምሮ የቅርባችን ለሆኑት ሰዎች እውነት ነው። ከእንግዶች ይልቅ እጅግ የሚቀርቡንን ሰዎች ለመጋፈጥ ወይም ይቅርታ ለመጠየቅ ትልቅ ድፍረትንና ብርታትን ይጠይቃል።

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የግንኙነት ችግሮች በብዛት የሚከሰቱት እርስ በርሳቸው በሚጣሉ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች መካከል ነው። ለምእመናን ፍቅራችንን ለማሳየት ጥረት እንደምናደርግ ሁሉ፣ ለሌሎች የቤተ ክርስቲያን መሪዎችም እንዲሁ ፍቅራችንን ማሳየት አለብን። ለሕይወታቸውና ለመንፈሳዊ ዕድገታቸው የምናስብ መሆናችንን ማወቃቸው ሌሎች መሪዎች ለእኛ አክብሮት እንዲኖራቸው ያስችላቸዋል። እንዲሁም ደግሞ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚነሡትን ችግሮች በፍርሐት ከማስተናገድ ይልቅ ቁርጥ ውሳኔዎችን ብናደርግ፣ በሌሎች የቤተ

ክርስቲያን መሪዎች እንከበራለን:: ችግሮች እልባት ሳያገኙ ተንጠልጥለው እንዲኖሩ ከማድረግ ይልቅ መፍትሔዎችን ስንፈልግና የተበላሸውን ነገር ስናስተካክል ለእኛ ያላቸው አክብሮት ይጨምራል::

2. የግንኙነት ችግሮችን የሚያስከትሉ ችግሮች በሚኖሩበት ጊዜ ግንኙነቶች ወደ ጥልቅ ደረጃ የሚደርሱት እነዚህን ችግሮች በመንፈሳዊ መንገድ በመያዝ ነው:: ሁለት መሪዎች የቤተ ክርስቲያንን ራእይ በሚመለከት ጉዳይ የተለያዩ አቋሞችን ይዘው በሚወዛገቡበት ጊዜ እርስ በርሳቸው ለመዋደድና ልዩነቶቻቸውን ለማሻሻል ከወሰኑ፣ ወደፊት እጅግ የጠነከረ ግንኙነት ሊመሠርቱ ይችላሉ:: እግዚአብሔር ያለብንን ማንኛውንም ችግር፣ አለመስማማት ወይም የስሜት መጎዳት በመጠቀም ዕድገትን ሊያመጣ ይችላል:: ሁሉም ነገር የሚወሰነው በአያያዛችን ላይ ነው:: ሰይጣን ችግሮችን፣ አለመስማማቶችንና የስሜት መጎዳትን ተጠቅሞ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ትልቅ ሽለቆ ሊፈጥር ይችላል:: ነገር ግን እነዚህን ነገሮች በትሕትና፣ እግዚአብሔርን ለመታዘዝ በመሻትና በአንድ አሳብ ለማገልገል በመፈለግ (ፊልጵ. 2:3) ከያዝናቸው፣ እግዚአብሔርን ብንጠይቅና ይቅር ብንል (ማቴ. 5:23-24፤ 6:12-15)፣ እግዚአብሔር ጥልቅና ጠንካራ ግንኙነቶችን ለማምጣት ይጠቀምባቸዋል::

16ኛ ጥያቄ:- ሀ) ማጠናከር የሚያስፈልግህ ግንኙነት የትኛው ነው? በመካከላችሁ አመኔታና መከባበር እንዲኖር ግንኙነቱን ለማጠናከር ምን ልታደርግ እንደምትችል ዕቅድ አውጣ:: ለ) እግዚአብሔር የሚፈልጋቸውን ዓይነት ያልሆኑ ምን ዓይነት ግንኙነቶች አሉህ? እነዚህ ግንኙነቶች በመከባበርና አመኔታ እንዳያድግ የሚያደርገው ምንድን ነው? ግንኙነቱ በፍቅር፣ በይቅርታና በጋራ መከባበር ላይ የተመሠረተ ይሆን ዘንድ መለወጥ ያለበት ነገር ምንድን ነው? አሁኑኑ ጊዜ ውሰድና እግዚአብሔርን ግንኙነቶቹን ለመለወጥ እንዲረዳህ ጠይቅ::

## ሦስተኛ ቀን

አመራር በሰዎች ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩና የቤተ ክርስቲያንን ችግሮች የሚቀርፉ ውሳኔዎች በመስጠት ላይ የተመሠረተ ነው::



ስለሆነም፣ መሪዎች ምርጥ ውሳኔዎችን መስጠት አለባቸው:: ይህ ካልሆነ፣ ሰዎች በአመራራቸው ላይ እመኔታ ስለማይኖራቸው፣ አይከተሏቸውም:: በየቀኑ አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ ሊያደርጋቸው የሚገባቸው ውሳኔዎች አሉ:: እነዚህም ውሳኔዎች ውስብስብ አስከትሎቶችን ሊመዘ የሚችሉ ናቸው:: እነዚያ ውሳኔ ዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ፈውስና አንድነት ሊያመጡ ይችላሉ:: ወይም ደግሞ ተጨማሪ ክፍፍሎችን ሊያስከትሉ ይችላሉ:: አስቸጋሪና ሰዎች የማይወዷቸውን ውሳኔዎች ለማስተ ላለፍ የሚፈራ ወይም ውሳኔዎችን በወቅቱ ለመስጠት የማይችል የትኛውም የቤተ ክርስቲያን መሪ፣ የእግዚአብሔርን ቤተሰብ በጥሩ ሁኔታ ሊመራ አይችልም:: ምንም እንኳን ሰዎች እንደሚወዳቸው በማወቃቸው ምክንያት አንድን መሪ ሊወዱት ቢችሉም፣ ውሳኔ ለመስጠት ካልቻሰ ወይም ይህንኑ ወቅቱን በጠበቀ ሁኔታ ካላከናወነ፣ እዝነው እርሱን ላለመከተል ሊወስኑ ይችላሉ:: ስለሆነም፣ ቀጥለን የምንመለከተው ክህሎት አንድ መሪ እንዴት ጥሩ ውሳኔዎችን ሊሰጥ እንደሚችል የሚያሳይ ይሆናል::

17ኛ ጥያቄ:- ሀ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ያስተላለፉት ጥሩ ውሳኔ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንድነትን ሲፈጥር የተመለከትከው እንዴት ነው? ለ) ጥሩ ያልሆነ ወይም በጊዜው ያልተሰጠ ውሳኔ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የነበሩትን ችግሮች ሲያባብስ የተመለከትክበትን ሁኔታ ግለጽ:: ሐ) ብዙ መሪዎች አስቸጋሪ ውሳኔዎችን ለመስጠት የሚፈሩት ለምን ይመስልሃል?

## አምስተኛ ክህሎት:- ጥሩ ውሳኔዎችን መስጠትና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ላሉት ችግሮች መፍትሔ መስጠት::

ውጤታማ አመራር ጥሩ ውሳኔዎች መስጠትን ይጠይቃል:: ውሳኔዎቹ የሚሰጡት የቤተ ክርስቲያኒቱ ራእይ ምን መሆን እንዳለበትና ይህንኑ ራእይ ክፍጻሜ ለማድረስ ምን ዓይነት ዕቅዶችን ማውጣት እንደሚያስፈልግ ሊሆን ይችላል:: ስለ ገንዘብ አጠቃቀም ወይም ቤተ ክርስቲያንን ስለ ገጠማት አንድ ችግር ሊሆን ይችላል::

18ኛ ጥያቄ፡- ዘጸአ. 32:1-6 አንብብ። ሀ) አሮን የገጠመው ችግር ምን ነበር? ለ) ምን ለማድረግ መረጠ? ለምን? ሐ) ዛሬ አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ እንዴት ተመሳሳይ ችግር ሊገጥመው እንደሚችል ግለጽ። መ) ብዙውን ጊዜ የአብዛኛውን ሕዝብ ፍላጎት የሚጻረር ውሳኔ መስጠት አስቸጋሪ የሚሆነው ለምንድን ነው? ሠ) ሰዎች የሚፈልጉትን ነገር መምረጥ ሰዎቹን ከእግዚአብሔር እንደምናስበልጣቸው የሚያሳየው እንዴት ነው?

***መንፈሳዊ መሪ ለመሆን፣ አንድ ሰው እንዴት አስቸጋሪ ውሳኔዎችን መስጠት፣ አደጋን መጋፈጥና ለችግሮች መፍትሔ መስጠትን መማር አለበት።***

1. ምንም እንኳን አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ በአንጻራዊ መልኩ ቀላል የሚባሉትን ውሳኔዎች በየቀኑ ቢያስተላልፍም፣ ከከባባድ ውሳኔዎችም ጋር የሚጋፈጥባቸው ጊዜያት አሉ። መሪው የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዳልሆኑ የሚያውቃቸው የግብረ-ገብ ጉዳዮች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሊኖሩ ይችላሉ። ይህንን ሁኔታ ለማስተካከል ካልሞከረ፣ ሕዝቡ እግዚአብሔር ለእነርሱ ካዘጋጀው መንገድ ይበልጥ እየራቁ ይሄዳሉ። ነገር ግን ለችግሮች መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ መፍትሔ ከሰጣቸው፣ የግንኙነት ችግሮች ሊስከቱ ይችሉ ይሆናል። ወይም እነዚህን ችግሮች ወደ ሽማግሌዎች በሚያመጣበት ጊዜ፣ ብዙውን ጊዜ ችግሩን በመጽሐፍ ቅዱሳዊ መንገድ ለመፍታት ሊፈሩ ይችላሉ። ይህ በሚሆንበት ጊዜ የቤተ ክርስቲያን መሪው እግዚአብሔር የሚፈልገውና ሰዎች የሚፈልጉት ነገር የሚለያይበትን ችግር ለመፍታት ይገደዳል።

አሮን እንዲህ ዓይነት ችግር ገጥሞት ነበር። ይህ የሆነው ሙሴ በተራራ ላይ ከእግዚአብሔር ጋር እየተገናኘ ሳለ ነበር። ሙሴ ተራራ ላይ በመቆየቱ ምክንያት ሕዝቡ ትዕግሥት አጥተው አሮን የወርቅ ጥጃ እንዲሠራላቸው ጠየቁት። በዚህ ጊዜ አሮን ምንም ዓይነት የተቀረጸ ምስል እንዳያመልኩ እግዚአብሔር የሰጠውን ትእዛዝ በመጠበቁ (ዘጸአ. 20:4-6) እና ሕዝቡ የጠየቁትን የወርቅ ጥጃ በመሥራቱ አሳብ ተወጠረ። በመጨረሻም፣ አሮን ሕዝቡ የሚፈልጉትን ነገር ለማድረግ በመምረጥ የወርቁን ጥጃ



ሠራላቸው። አሮን በዚህ ውሳኔው እግዚአብሔርን ለመታዘዝ ባለመፈለጉ የእግዚአብሔር ፍርድ በሕዝቡና በእርሱ ላይ ደረሰ።

ዛሬም እንደ አሮን፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አብዛኛው ሕዝብና ምናልባትም አብዛኞቹ ሽማግሌዎች፣ የተሳሳተ ነገር በሚመርጡበት ሁኔታ ውስጥ ራሳቸውን ያገኛሉ። በዚህ ጊዜ መሪው አንድም እግዚአብሔርን መታዘዝ ወይም ሕዝቡ የሚፈልጉትን ነገር ማድረግ ይኖርበታል። መሪው እግዚአብሔርን ከመታዘዝ ይልቅ ሕዝቡን ለማስደሰት የሚፈልግ ከሆነ፣ እግዚአብሔር በታላቅ መንገድ ሊጠቀምበት አይችልም። አመራር ብዙውን ጊዜ የብቸኝነት አገልግሎት ነው። ይህም የሚሆነው አንዳንድ ጊዜ ሰዎች የማይወዱትን ወይም ባህላዊ ተቀባይነት የሌላቸውን ውሳኔዎች መስጠትን የግድ ስለሚል ነው።

19ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ሕዝቡ ከሚሰጠው ምላሽ የተነሣ ውሳኔ ለመስጠት አስቸጋሪ ሊሆኑ የሚችሉትን ሦስት ሁኔታዎች ዘርዝር። ለ) መሪው የአብዛኛውን ሕዝብ ፍላጎት የሚከተል ከሆነ፣ ውሳኔው ምን እንደሚሆን ግለጽ። በዚህ ጊዜ የሕዝቡ መንፈሳዊ ሕይወት ምን ይሆናል? ሐ) መሪዎቹ እግዚአብሔር የሚፈልገውን ነገር ለማድረግ ቢመርጡ፣ ውሳኔው ምን ይሆናል? ይህ በሕዝቡ አመለካከት ላይ የሚያስከትለው የአጭር ጊዜ ለውጥ ምን ይሆናል? በቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ሕይወት ላይ የሚያስከትለው የረዥም ጊዜ ለውጥስ? መ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ውሳኔ ለመስጠት መፍራታቸው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ችግርን ሲፈጥር የተመለከትክበትን ሁኔታ ግለጽ።

2. አመራር አደጋን መጋፈጥንም ያካትታል። በአመራር ውስጥ፣ «አደጋ» የሚባለው አዲስና መሳካት አለመሳካቱ ያልተረጋገጠለት ማንኛውም ዕቅድ ነው። ይህ ከዚህ በፊት ያልተሞከረ በመሆኑ፣ መከረጅ ወይም ውጤቱ ምን ሊሆን እንደሚችል ማወቅ አይቻልም። ምናልባትም እግዚአብሔር ከችሎታችን በላይ የሚመስል አንድ ነገር እንድናደርግ እየጠየቀን ይሆናል። በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር የሚፈልገውን ነገር እንደሚፈጽም በማመን ሥራውን እንጀምራለን።

ለምሳሌ፣ ምንም እንኳን ከዚህ በፊት ዝናብ ባይዘንብም፣ እግዚአብሔር ኖኅ መርከብ እንዲሠራለት አዘዘው። ኖኅ ሕዝብ ሁሉ ከሚያስብበት መሥመር በመውጣት መርከብ መሥራትና ለእግዚአብሔር የታዛዥነት ምላሽ መስጠት ነበረበት። ምንም ዓይነት መንገድ ሳይኖር፣ ሙሴ እግዚአብሔርን በመታዘዝ ሕዝቡን እየመራ ቀይ ባህር ውስጥ መግባት የመሰለውን አደጋ ተጋፈጠ። ጌዴዎን ከግዙፍ ሠራዊት ጋር ለመግጠም በሄደ ጊዜ 300 ወታደሮችን ብቻ አስቀርቶ ሌሎች ተዋጊዎችን ሁሉ በማሰናበት አደጋን ተጋፈጠ። ፊልጶስ ከዚህ በፊት ማንም ያላደረገውን ለሰማርያውያን ወንጌል የመስበክ አደጋ ተጋፈጠ። ጳውሎስ ወንጌልን ለአሕዛብ በመውሰድና የአይሁድን ልማድና ሕግጋት እንዳይከተሉ በማድረግ አይሁዶችን አሳዘነ።

እግዚአብሔር ሁልጊዜም ሕዝቡ በእምነት እንዲጓዝ ይፈልጋል። ይህ ማለት ደግሞ በእግዚአብሔር ስለምንታመንና ልንታዘዘው ስለምንፈልግ፣ ያልተለመደ ወይም አዲስ ነገር ማድረግ አለብን ማለት ነው። ብዙውን ጊዜ ይህ እግዚአብሔር አዳዲስ ነገሮችን ለመሥራት በሚመርጣቸው መሪዎች ሕይወት ውስጥ የሚፈጸም ነው። አብያተ ክርስቲያኖቻችን እንዲያድጉና እንዲለወጡ ከፈለግን፣ ከዚህ በፊት ያላደረግናቸው ነገሮች ማድረግ ይኖርብናል። ጥናቶች እንዳሳዩት፣ በማኅበረሰቦች ውስጥ አዳዲስ ነገሮችን የመሞከር ድፍረት ያላቸው ሰዎች ጥቂቶች ብቻ ናቸው። ብዙውን ጊዜ ሰዎች እነዚህን አዳዲስ ነገሮች በሚሞክሩት ሰዎች ላይ ይሳለቃሉ። አብዛኛው ሕዝብ አመለካከቱን የሚቀይረው የተሞከረው ነገር ውጤታማ መሆኑን ከተመለከተ በኋላ ብቻ ነው።

በአብዛኛው አንድ መሪ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ታላቅ ለውጥ የሚያመጣ ውሳኔ ሲሰጥ ውጤቱ ጥሩ ይሁን መጥፎ በርግጠኝነት ሳያውቅ ለመሞከር ይደፍራል። መሪው እግዚአብሔር የሚፈልገውን ነገር ለማወቅ ከሞከረ በኋላ ውሳኔው የሚያስከትላቸውን ነገሮች ሙሉ በሙሉ ሳያውቅ ይወስናል። መሪው ጥሩ ውጤት ላያመጣ የሚችለውን አስቸጋሪ ውሳኔ ለመስጠት ካልደፈረ፣ ምን ጊዜም ሕዝቡን እግዚአብሔር ወደሚፈልገው መንገድ ሊመራ አይችልም። ወይም ደግሞ መሪው ሁኔታው ከዚህ በፊት እንደ ነበረው ብቻ እንዲቀጥል የሚያደርግ ከሆነ፣ መንፈሳዊ ዕድገት ሊመጣ አይችልም። እግዚአብሔር ሁልጊዜም ሕዝቡ እምነት እንዲኖረው ይፈልጋል። በመሆኑም፣ ከአስቸጋሪ ወይም ለእኛ የማይመቹ ከሚመስሉ ነገሮች ጋር በምንጋፈጥበት ጊዜ ያለን የልብ እምነት ብቻ ይሆናል።

20ኛ ጥያቄ፡- ሀ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለቤተ ክርስቲያናቸው ሊሰጡ የሚችሏቸውን ሦስት «አደገኛ» ውሳኔዎች ዘርዝር። ለ) ብዙ መሪዎች ከእንዲህ ዓይነቱ አደጋ ለመራቅ የሚሞክሩት ለምንድን ነው? ሐ) እግዚአብሔር ብዙውን ጊዜ እርሱን በመተማመን አዲስን ነገር እንድናደርግና «አደጋውን» እንድንጋፈጥ የሚፈልገው ለምንድን ነው? መ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አደጋን ለመጋፈጥ መፍራታቸው እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ሊሠራ ያሰበውን ነገር ሲገድብ የተመለከትክበትን ሁኔታ ግለጽ።

3. አመራር ቀላል መፍትሔ የማይገኝላቸውን ከባባድ ችግሮችንም ያካትታል። በቤተ ክርስቲያን ምእመናን መካከል አለመግባባት ይፈጠርና ወደ መሪው ዘንድ ለውሳኔ ይመጣሉ። መሪው ችግሩን በአግባቡ ካልፈታ፣ ችግሩ ሊባባስ ይችላል። መሪው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉትን ችግሮች ለመፍታት የሚፈራ ከሆነ፣ ወይም በመጽሐፍ ቅዱሳዊ መንገድ ለችግሮች መፍትሔዎችን የማይፈልግ ከሆነ፣ እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንድነትንና ንጽሕናን ለማምጣት ሊጠቀምበት አይችልም።

ለምሳሌ፣ ሐዋርያት አሕዛብ ለመዳን የአይሁዶችን የብሉይ ኪዳን ሕጎች መጠበቅ አለባቸው የሰባቸውም የሚል ከባድ ችግር ገጥሟቸው ነበር (የሐዋ. 15)። በአንድ መንገድ ውሳኔውን ቢሰጡ፣ አሕዛብ በክርስቶስ አምነው የሚድኑበትን መንገድ ይገድቡ ነበር። በሌላ በኩል ቢወስኑ ደግሞ፣ ብዙ አይሁዳውያን ክርስቲያኖች ያዝኑባቸው ነበር። ጭራሽ ውሳኔ አለመስጠቱ ደግሞ፣ ሁለት አብያተ ክርስቲያናትን፣ ማለትም የአይሁዶች እና የአሕዛብ አብያተ ክርስቲያናትን መፈጠር ያስከትል ነበር። ስለዚህ፣ ሐዋርያት አሕዛብ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት የሚያገኙበትን መንገድ በተመለከተ ብዙ አይሁዶች የማይፈልጉትን ውሳኔ ለመስጠት ተገድደዋል።

21ኛ ጥያቄ፡- ሀ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለአንድ ችግር በፍጥነት ወይም በአግባቡ እልባት አለመስጠታቸው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የባሱ ችግሮችን ሲያስከትል የተመለከትክበትን ሁኔታ ግለጽ፡፡

## ውሳኔ በምንሰጥበት ጊዜ ልብ ልንላቸው የሚገቡ መሠረታዊ መርሖዎች፡-

1. ማንኛውም መሪ ወደ መሪነት ከመምጣቱ በፊት ውሳኔ ዎችን የመስጠት ግዴታ እንደሚኖርበትና ከእነዚህም ውሳኔዎች አብዛኞቹ አስቸጋሪዎችና ሥቃይን የሚፈጥሩ መሆናቸውን መገንዘብ አለበት፡፡ አንዳንዶቹ ውሳኔዎች በሰዎች ዘንድ ተወዳጅነት አይኖራቸውም፡፡ ሌሎች ብዙ ሰዎች የማይደፍሯቸው ከባድ ውሳኔ ዎች ይሆናሉ፡፡ አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ እንደ ተናገረው፣ ለቤተ ክርስቲያን ዕድገት አጅግ ከፍተኛው መሰናክል «ከዚህ በፊት እንዲህ ዓይነት ነገር አድርገን አናውቅም፣» የሚለው አስተሳሰብ ነው፡፡ ማንም ሰው ቀላል ነገሮችን በመጠበቅና ከባባድ ውሳኔዎች የማድረግ ግዴታ እንደሚኖርበት ሳያውቅ ወደ መሪነት መምጣት የለበትም፡፡

2. የቤተ ክርስቲያን መሪ ተግባሩ ቤተ ክርስቲያንን እግዚአብሔ ር በሚፈልገው መሥመር መምራት እንደ ሆነ ሁልጊዜም ማስታወስ አለበት፡፡ ያ መሥመር ሁልጊዜም ለአደጋ የሚያጋልጡ ሁኔታዎችን ያካተተ መሆኑ የማይቀር ነው፡፡ ለዚህም ምክንያቱ እግዚአብሔር ሁልጊዜም የሕዝቡን እምነት ለማስፋት ስለሚፈልግ ነው፡፡ ሁልጊዜ አንድ ዓይነት ነገሮችን የምናደርግ ከሆነ፣ እምነታችን ሊያድግ አይችልም፡፡ አዳዲስና የማይቻሉ የሚመስሉትን ነገሮች ማድረግ አለብን፡፡ ነገሮችን በራሳችን ብርታት የምናከናውን ከሆነ፣ እምነት ለምን ያስፈልጋል? ብዙውን ጊዜ እግዚአብሔር የሚጠይቀን ነገር ከባሕላችን ስለሚወጣ፣ ርዳታ መጠየቃችን የግድ ይሆናል፡፡ አንደ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች የባሕላችን ባሪያዎች መሆን የለብንም፡፡ መሆን ያለብን የእግዚአብሔ ር ባሪያዎች ነው፡፡ ሁልጊዜም የእርሱ መንገድ ትክክለኛና ከሁሉም የተሻለ ነው - ምንም እንኳን ባህላችን በዚህ አሳብ ላይስማማ



ቢችልም፡፡ ስለሆነም አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ እግዚአብሔርን በመስማት እርሱ የሚፈልገውን የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡ የአንድ መሪ ፍላጎት በቀዳሚነት ሰዎች የሚፈልጉትን ማድረግ መሆን የለበትም፡፡ በገላትያ 1:10፣ እግዚአብሔርን ለማስደሰት ብንፈልግ፣ የእግዚአብሔር ባሪያዎች እንደ ሆነን፤ ነገር ግን ሰዎችን ለማስደሰት የምንፈልግ ከሆነ፣ የሰዎች ባሪያዎች እንደ ሆንን የሚናገረውን ቃል አስቡ፡፡ የማን ባሪያ መሆን ትፈልጋላችሁ? ሰ ዎችን ለማስደሰት ብትፈልጉ፣ የሰዎች ባሪያች ናችሁ፡፡ መጀመሪያ እግዚአብሔርን ለማስደሰት ራስን መስጠቱ ምንኛ የተሻለ ነገር ነው፡፡ ከዚያ በኋላ በነጻነት ስሜት ሕዝቡን ለመምራት ትችላላችሁ፡፡ የምትሰጧቸው ውሳኔዎችም ምንም እንኳን በራስ-ወዳድነት የሚፈልጓቸው ባይሆኑም፣ የኋላ ኋላ ለሕዝቡ የሚጠቅሙ ይሆናሉ፡፡

22ኛ ጥያቄ፡- ሰዎችን ስማስደሰት በመፈለግ እግዚአብሔርን የማያስደስት ነገር ስማድረግ የተገደድክበትን ሁኔታ የሚያሳይ ግላዊ ገጠመኝ ተናገር፡፡ ለ) ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች ይህን ሰዎችን የማስደሰት ተፈጥሯዊ ፍላጎት ማሸነፍና እግዚአብሔርን በማስደሰት ላይ ትኩረት ማድረግ አስፈላጊ የሚሆነው ለምንድን ነው?

3. አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ ውሳኔዎችን በሚሰጥበት ጊዜ ልባዊ ፍላጎቱ «እግዚአብሔር ምን እንድናደርግ ይፈልጋል?» የሚል መሆን አለበት፡፡ የቤተ ክርስቲያን መሪው የቤተ ክርስቲያን ራስ አይደለም፡፡ የቤተ ክርስቲያን ራስ ክርስቶስ ነው፡፡ ስለዚህ እርሱን መስማትና መታዘዝ አለብን፡፡ ክርስቶስ ለግል ሕይወታችንም ሆነ ለቤተ ክርስቲያናችን ትልቁ ፍላጎታችን የእግዚአብሔርን መንግሥትና ጽድቅ መፈለግ ሊሆን እንደሚገባ ተናግሯል (ማቴ. 6:33)፡፡ ስለሆነም መሪዎች ራእዮችን፣ ዕቅዶችንና ውሳኔዎችን በሚሰጡበት ጊዜ፣ ሁሉንም ነገር አውቃለሁ ከማለት ይልቅ፣ በእያንዳንዱ ሁኔታ ውስጥ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ መጣር አለባቸው፡፡ ይህ ማለት እግዚአብሔር ፈቃዱን እንዲገልጥልን ልንጸልይና በሚያጋጥመን ሁኔታ ውስጥ ሁሉ እንዲመራን መጸለይ አለብን ማለት ነው፡፡

ይህ ሁሉም ሽማግሌዎች ሊማሩት የሚገባው ጠቃሚ እውነት ነው። ብዙውን ጊዜ በሽማግሌዎች ወይም በክልላዊ የቦርድ ስብሰባ ዎች ላይ ትልቁ ችግር እያንዳንዱ ሰው ራሱ፣ ቤተሰቡ፣ ጎሳው፣ ወይም የአካባቢው ቤተ ክርስቲያን የሚጠቀምበትን መንገድ የሚፈልግ መሆኑ ነው። መሪው ውሳኔ ለመስጠት በሚፈልግበት ጊዜ፣ «ለቤተሰቤ ወይም ለጎሳዬ ከሁሉም የሚሻለው የትኛው ነው?» ሊል ይጠይቃል። ወይም የቤተ ክርስቲያንና የቀጣና ተ ወካዮች ሆነን የቦርድ ስብሰባ ላይ በምንገኝበት ጊዜ ዋንኛው ጥያቄያችን፣ «ይህን ውሳኔ ለቤተ ክርስቲያኔ በሚጠቅም መንገድ እንዴት ልቀይረው እችላለሁ? ሰዎች ወደ እኛ አካባቢ ወንጌላዊ እንዲልኩ ማድረግ እችላለሁ? በአካባቢያችን የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት እንዲገነባ ላደርግ የምችለው እንዴት ነው?» የሚል ይሆናል። እንደ ሰዎች ሁሉ አብያተ ክርስቲያናትም ስለ ሌላው ሰው ከማሰባቸው በፊት የራሳቸውን ጉዳይ ያስቀድማሉ። ስለ ሆነም፣ ብዙ አብያተ ክርስቲያናት የራሳቸውን ምእመናን ለማሳደግ አስተዋጽኦ ለማያደርጉ ወንጌላውያን ገንዘብ ለማዋጣት አይፈልጉም። ምላሻቸውን የሚሰጡት ቤተ ክርስቲያኖቻቸው እንዲያድጉ፣ የቆርቆሮ ቤተ ሊሠሩ፣ አዲስ የድምፅ ማጉያ፣ ወዘተ. . . ሊያገኙ በሚችሉበት መንገድ ነው። ችግሩ ብዙ ሰዎች ያልዳኑባቸው አካባቢዎች የሚገኙት ትላልቅ አብያተ ክርስቲያናት ባሉባቸው ቦታዎች አይደለም። እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ ወደ ስብሰባው የሚመጣው የራስ-ወዳድነት ዕቅዱን ለራሱ ወይም ለቤተ ክርስቲያኑ በመወጠን ስለ ሆነ፣ ሁለት ችግሮች ይከሰታሉ:-

ሀ. ስብሰባው ውስጥ ውጥረት ይነግሣል። መሪዎች ውሳኔ ዎችን ለራሳቸው ጥቅም ለማዋል ጥረት በማድረጋቸው ምክንያት የኃይል ፍትጊያ ይካሄዳል። ትላልቅ ቀጣናዎች በድምጽ ብልጫው ያሸንፉና ትናንሽ ቀጣናዎች በኀዘን ከስብሰባው በታ ይሰናበታሉ። ይህም የሚሆነው ለአነስተኛ ቀጣናዎች የሚገባውን ሀብት ትላልቆቹ ቀጣናዎች ባላቸው የድምጽ ብዛት አሸንፈው ወስደዋል የሚል እምነት ስላላቸው ነው። መሪዎችና ተወካዮች ውሳኔዎች



የራሳቸውን ቤተ ክርስቲያን እንዲጠቅሙ የሚፈልጉ ከሆነ፣ ምን ጊዜም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንድነት ሊኖር አይችልም።

ለ. የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በሆነ መንገድ ሁሉንም መሪ ዎች የሚያስደስቱ ውሳኔዎችን ለመስጠት ስለሚፈልጉ፣ አብዛኞቹ ውሳኔዎች ከ«ማመቻመች» አያልፉም። ይህን ያህል ጥሩ ውሳኔ ዎች ሊተላለፉ አይችሉም። እንዲህ ዓይነት ውሳኔዎች ሁሉም ለእግዚአብሔር መንግሥት በማሰብ የሚሰጠውን ያህል ውጤታማ ሊሆኑ አይችሉም።

ራስ ወዳድነት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ውሳኔዎችን በማመቻ መች አንዱ ሌላውን ለማስደሰትና ሰላምን ለመፍጠር እንዲጥር እያደረገ ነው። ይህን ያህልም፣ «ለእግዚአብሔር መንግሥት ከሁሉም የሚበልጠው የትኛው ነው? ክርስቶስ ምን እንድናደርግ ይፈልጋል?» የሚለውን ጥያቄ በሚመልስ መልኩ ውሳኔዎች አይሰጡም። እግዚአብሔር እንደሚፈልገው ለመምራት ከፈለግን፣ እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን መሪ ወደ ስብሰባው ስፍራ እንደ ዓይነት ፍላጎት ይዞ መምጣት አለበት። «እግዚአብሔር ሆይ፣ አንተ የምትፈልገውን ውሳኔ እንድንሰጥ እርዳን። ጌታ ሆይ፣ ለራሴና ለቤተ ክርስቲያኔ ጥቅም በማሰብ ውሳኔዎችን እንዳልሰጥ እርዳኝ፣» የሚል አሳብ በሁሉም ልብ ውስጥ መገኘት አለበት። የኋላ የኋላ፣ የእግዚአብሔር ውሳኔዎች ለቤተ ክርስቲያናችን ከሁሉም የሚሻሉ ናቸው። ይህ ማለት ግን ወንጌላዊ፣ የወንጌላዊ ደመወዝ መክፈያ ገንዘብ፣ አዲስ የቆርቆሮ ቤት፣ ወይም የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ማግኘት ላይሆን ይችላል። ነገር ግን፣ እግዚአብሔር የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ከዚህ በበለጠ መንገድ መንግሥቱን የሚያስፋ ውሳኔ እንዲሰጡ ሊረዳቸው ይችላል። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በራስ-ወዳድነት አሳብ ውሳኔዎችን ቢሰጡ፣ ወንጌሉን ሊሰሙ የማይችሉ ሰዎች እግዚአብሔርን በሚያስከብረው ውሳኔ ወንጌሉን የመስማት ዕድል ሊኖራቸው ይችላል። በተጨማሪም፣ እግዚአብሔር ከራስ-ወዳድነት ፍላጎት ወጥተው እግዚአብሔር የሚፈልገውን ነገር ስለሚያደርጉ ሰዎች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ያድጋሉ።

**23ኛ ጥያቄ፡-** ሀ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከእግዚአብሔር መንግሥት ይልቅ ለራሳቸው ቤተ ክርስቲያን የሚጠቅም ውሳኔ ሲሰጡ ያየሀበትን ሰብሰባ በተመለከተ ማብራሪያ ስጥ። ለ) ይህ አመለካከት ከላይ የተመለከቱትን የራስ-ወዳድነት ውሳኔ ሁለት አስከፊ ውጤቶች ያስከተለው እንዴት ነው? ሐ) መሪዎች ለየራሳቸው አብያተ ክርስቲያናት ከሚጠቅሙ ነገሮች ይልቅ ለእግዚአብሔር የሚጠቅም ውሳኔ መስጠታቸው በውሳኔያቸው ላይ ለውጥ የሚያመጣው እንዴት ነው? መ) የቤተ ክርስቲያን መሪ ከሆንክ፣ ቀደም ሲል የሰጠሃቸውን ውሳኔዎች ሁሉ አሰብ። የቤተ ክርስቲያን መሪ ካልሆንክ፣ የምታውቃቸውን የመሪዎች ውሳኔዎች አስታውስ። 1) ከውሳኔዎቹ አንድን መሪ ወይም ቤተ ክርስቲያን ለመጥቀም ሲባል የተሰጡት የትኞቹ ናቸው? 2) የክርስቶስን መንግሥት በተቻለን አቅም ሁሉ ለማስፋፋት በሚያስችል መንገድ የተሰጡት ውሳኔዎች የትኞቹ ነበሩ? 3) ውሳኔዎቹ ሁሉ የተሰጡት የእግዚአብሔርን መንግሥት ለማስፋት በሚያስችል መልክ ቢሆን ኖሮ፣ ምን ዓይነት ለውጥ ይኖር ነበር? ሠ) አንድ ነገር የእኛ ግላዊ ፍላጎት ብቻ ሳይሆን፣ የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን የምናውቀው እንዴት ነው?

4. የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ውሳኔ በሚሰጥበት ጊዜ ሁሉ ውጤታማ ያለመሆን አደጋ መኖሩን መረዳት አለባቸው። አንድን ውሳኔ በምንሰጥበት ጊዜ ውጤቱን ሙሉ በሙሉ ልናውቅ አንችልም። በተለይም እግዚአብሔር እንድንፈልግ የሚያደርገው ነው ብለን ድፍረት የተሞላበት የእምነት እርምጃ በምንወስድበት ጊዜ፣ ውጤቱን ማወቁ አስቸጋሪ ነው። የውድቀቱ መዘዝ ከፍተኛ በሚሆንበት ጊዜ (ለምሳሌ፣ ውሳኔው ብዙ ገንዘብ የሚያካትት ከሆነ፣ ወይም ቀደም ሲል ሲሠራበት ከነበረው ጭራሽ የተለየ መንገድ የምንከተል ከሆነ)፣ የውሳኔው ውጤታማ አለመሆን የሚያስከትለው አደጋ ከፍተኛ ይሆናል። ነገር ግን የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አንድ ነገር የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው ብለው ካመኑ፣ አደጋ ለመጋፈጥ ፈቃደኞች መሆን አለባቸው። ውድቀትን የምንፈራ ከሆነ፣ ለቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ ለውጥ የሚያመጣ የእምነት ውሳኔ ልንሰጥ አንችልም። የድፍረት ውሳኔ ባለመስጠት ለእግዚአብሔር ትንሽ ውጤት ብቻ ከማስመዝገብ ይልቅ፣ ከውሳኔ ዎቻችን 51 በመቶውን ትክክል በማድረግ ለእግዚአብሔር መንግሥት አንድ ነገር ማድረጉ የተሻለ ነው።



አደጋውን ለመቀነስ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የመንፈስ ቅዱስን ምሪት መከተል አለባቸው። እንዲሁም በተቻለ መጠን ውሳኔውን በተመለከተ በቂ መረጃ ሊኖረን ይገባል። ነገር ግን ውሳኔው ከተሳለፈ በኋላ እሳባችንን ሳንቀይር ጸንተን መቆም አለብን። እንዲሁም ሥራው እየተካሄደ ሳለ፣ በቅርብ ልንከታተለውና አሳሳፈላጊ አደጋዎችን ለመቀነስ የምንችለውን ጥረት ሁሉ ማድረግ አለብን። አንድ ጊዜ በቆራጥነት ውሳኔ ከሰጣችሁ፣ ወደ ፊት ጥሩ ውሳኔዎችን የመስጠት ልምድ ይኖራችኋል።

5. እንደ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ውጤታማነታችን የሚወሰነው ትክክለኛ ውሳኔዎችን በትክክለኛ ጊዜ ለማድረግ በመቻላችን ላይ ነው። እግዚአብሔር እንድናደርግ የሚፈልገውን ነገር ካወቅን በኋላ፣ ውሳኔው ተግባራዊ የሚሆንበትን ጊዜ በጸሎት መወሰን አለብን። ችኩለን ከጀመርን፣ ምናልባት እግዚአብሔር ለክብሩ ለማከናወን ለሚፈልገው ነገር የሕዝቡን ልብ ገና አላዘጋጀም ይሆናል። ወይም ደግሞ ጥሩ ውሳኔ ወይም ዕቅድ ለማውጣት ሁኔታው ገና ግልጽ አልሆነም ይሆናል። በጣም ከቆየን ደግሞ፣ ለእግዚአብሔር አንድ ነገር የምናደርግበት አጋጣሚ ሊያመልጠን ይችላል። ለአጭር ጊዜ ብቻ ልንጠቀም የምንችላቸው ዕድሎች አሉ። (ለምሳሌ፣ አንድ ቦታ ላይ ቤቶች ከመሠራታቸው በፊት በመሬቱ ላይ የቤተ ክርስቲያን ሕንጻ መሥራት።) ወይም ደግሞ ብዙ በቆየን መጠን፣ ምእመናን በጉዳዩ ላይ የተለያዩ አቋሞች እየያዙ ይመጡና ሊወሳሰብብን ይችላል። (ለምሳሌ፣ አንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ለሁለት ትከፈል ወይ?) የሕዝቡ ስሜት ከተጎዳና ጥልቅ ቁስሎች ከተፈጠሩ፣ ለጉዳዩ እልባት መስጠቱ አስቸጋሪ ነው። ችግሩን ለመፍታት ብዙ አማራጮች ላይኖሩን ስለሚችሉ፣ የሰዎችን የጉዳትና የቁጣ ስሜት ለማስዘብ ከመጣር የበለጠ ሊወሰድ የሚችል እርምጃ ላይኖር ይችላል።

6. ጥሩ ውሳኔ በጥሩ አፈጻጸም ላይም ይደገፋል። ውሳኔ በምንሰጥበት ጊዜ፣ ውሳኔው ተግባራዊ የሚሆንባቸውን ዕቅዶች በማሰብም በቂ ጊዜ ማሳለፍ አለብን። ውሳኔው ተግባራዊ የሚሆንበት መንገድ በሚገባ ካልታቀደ፣ ውሳኔው መፍትሔ ለማግ

ኙት አያስችልም:: በአብዛኛው በጥሩ ሁኔታ የተከናወነ ደካማ ውሳኔ፣ በሚገባ ሊከናወን ካልቻለ ጥሩ ውሳኔ የተሻለ ነው::

7. መሪዎች በጸሎትና በጥንቃቄ ውሳኔውን ከሰጡ በኋላ፣ ጸንተው መቆም አለባቸው:: መሪው ጥሩ ውሳኔ አድርጌአለሁ አላደርግኩም እያለ መጨነቅ የለበትም:: ሰዎች እየመጡ የተለያዩ አመለካከቶችን ሲነግሩት ውሳኔውን መቀየር የለበትም:: እግዚአብሔር ውሳኔው መቀየር እንዳለበት በግልጽ ካላሳየው፣ መሪው ችሎታውን ሁሉ ተጠቅሞ የሰጠውን ውሳኔ መጠበቅ አለበት::

መሪው ውሳኔውን ከሰጠ በኋላ፣ ኃላፊነቱ የእርሱ እንደ ሆነ መረዳት አለበት:: ቢሳካ ወይም ባይሳካ፣ ሰዎች ቢወዱት ወይም ባይወዱት፣ ኃላፊነቱ የእርሱ ስለ ሆነ፣ ማመካኛዎችን ማቅረብ የለበትም:: መሪው ሰው ነውና የወደ ፊቱን ለማየት አይችልም:: ስለ ሆነም፣ የተወሰነው ነገር ውጤታማ ሳይሆን ቢቀር፣ ራሱን ዝቅ አድርጎ ጥሩ ውሳኔ አለመሆኑን ይቀበላል:: ነገር ግን ተስፋ ከመቁረጥ ይልቅ ስሕተቱን የዕድገት መማሪያ አድርጎ መጠቀም አለበት::

24ኛ ጥያቄ:- ከላይ የተጠቀሱት ሰባት ነገሮች አስፈላጊ የሚሆኑት ለምንድን ነው?

**የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለውሳኔያቸው የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንዴት እንደሚያውቁ መማር አለባቸው::**

አንድ ነገር የእግዚአብሔር ፈቃድ ይሁን ወይም የራሳችን ፈቃድ እንዴት እናውቃለን? አንዳንድ ሰዎች ቸኩለው፣ «እግዚአብሔር እንድናደርግ የሚፈልገው ይህንን ነው» ይላሉ:: ነገር ግን ይህንን እንዴት እናውቃለን? ከሰማይ ራእይ እንጠብቃለን? ተግባራዊ የሚመስል ነገር አይተን መሥራት እንቀጥላለን? በሁሉም ሁኔታዎች ውስጥ በመሪዎች ፊት የሚጋረጡ ሁለት ምርጫዎች አሉ:: በመጀመሪያ፣ የራሳችንን ጥበብና ሀብት ተጠቅመን ነገሮችን በራሳችን መንገድ ለማከናወን እንፈልጋለን:: በቀዳሚነት የዓለምን መስፈርት በመከተልና የነገሮችን ጠቃሚና ጎጂ ጎኖች በማመዛዘን ወይም ለእኛ



የሚሰጡትን ጥቅሞች በማሰብ ምርጫ ካካሄድን፣ በእግዚአብሔር ፈቃድ ላይ የተመሠረተ ውሳኔ ልናደርግ አንችልም:: ይህ ዓለማውያን ውሳኔዎችን ከሚሰጡበት መንገድ የተለየ አይደለም:: ሁለተኛ፣ በእግዚአብሔር መንገድ ውሳኔ የመስጠትም ምርጫ አለ:: ይህ በእግዚአብሔርና በምሪቱ ላይ በመመሥረት፣ ሀብቱን ተጠቅመን የምንወስነው ውሳኔ ይሆናል:: ለእግዚአብሔር ክብርን የሚያመጣው ውሳኔ ይህ ነው:: እግዚአብሔርም ሊረዳን ቃል የገባው በራሳችን ሳይሆን፣ በእርሱ ዕቅዶች ላይ ስንሠራ ነው::

ከዚህ በታች የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ውሳኔያቸው የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑንና የራሳቸውን ፍላጎት ሳይሆን፣ የእግዚአብሔርን አሳብ እያገለገሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ሊጠቀሙ የሚችሉባቸው ነጥቦች ቀርበዋል::

1. ማንኛውንም ውሳኔ ከመስጠታቸው በፊት፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እግዚአብሔርን ለመታዘዝ ራሳቸውን አሳልፈው መስጠት አለባቸው:: ነገሩ አመቺ ቢሆን ወይም ባይሆን፣ ከባሕላቸው ጋር ባይስማማ ወይም ቀደም ሲል ይሠራ ከነበረው መንገድ ጋር ባይመሳሰል፣ እግዚአብሔር ያለው ነገር መከናወን አለበት:: እግዚአብሔር ፈቃዱን የሚገልጠው ተግባራዊ ለማድረግ ለሚፈቅዱ ሰዎች ብቻ ነው:: ለራሳችን፣ ለቤተሰባችን፣ ለጎሳችን፣ ወይም ለባህላችን ብቻ የሚጠቅም ተግባር ለማከናወን ከወሰንን፣ እግዚአብሔር ለምን ብሎ ፈቃዱን ይገልጥልናል? የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ የሚጀምረው ፈቃዱን ለመፈጸም ካለን ቁርጠኝነት ነው::

2. የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የጸሎት ሰዎች ሊሆኑና ውሳኔዎችን ሁሉ በጸሎት ማሳለፍ አለባቸው:: ጸሎት እግዚአብሔር እንዲመራን በእርሱ ላይ መደገፋችንን የምንገልጽበት አንደኛው መንገድ ነው:: ከልቡ እግዚአብሔርን ለማስከበር የሚፈልግ ጸሎት ትኩረታችንን በእግዚአብሔር ፈቃድ ላይ እንድናሳርፍ ይረዳናል:: ጸሎታችን እውነተኛ ከሆነ፣ መንፈስ ቅዱስ ራስ-ወዳድነታችንን ለመቀነስ ይጠቀምበታል:: ብዙውን ጊዜ የእግዚአብሔር መንፈስ የሚንቀሳቀሰው በጸሎት ጊዜ ነው:: (በሐዋ. 1:15-26 መንፈስ

ቅዱስ ሐዋርያት በጸሎት ይሁዳን የሚተካ ሐዋርያ እንዲመርጡ መርጧቸዋል።) ብዙውን ጊዜ ሽክሞችን በሰዎች ልብ ላይ የሚያስቀምጠው በጸሎት ጊዜ ነው።

እግዚአብሔር አንድን ነገር እንዲያደርግልን የምንፈልገው አስቀድመን ዕቅድ ካወጣን በኋላ ከሆነ፣ እግዚአብሔር የእኛን ዕቅድ እንዲባርክ እየጠቅነው ነው ማለት ነው። ብዙውን ጊዜ የምናደርገውም ይህንኑ ነው። «ጌታ ሆይ፣ የቆርቆሮ ቤት ለመሥራት እንፈልጋለን። ምክንያቱም በከተማይቱ ውስጥ የእኛ ቤተ ክርስቲያን ታላቋ ቤተ ክርስቲያን እንድትሆን እንፈልጋለን። ስለዚህ፣ እባክህን ባርክን» ስንል እግዚአብሔር የራስ-ወዳድነት ዕቅዳችንን እንዲባርክ እንጠይቀዋለን። ነገር ግን፣ ምንም ዕቅድ ከማውጣታችን በፊት ወደ እግዚአብሔር በመምጣት ዕቅዶቹን እንዲገልጥልን ልንጠይቀው ይገባል። እግዚአብሔርን ምን እንድናደርግ እንደሚፈልግ የምናውቀውና ሥራውን ለማከናወን የሚያስችል ህብት የምናገኘው በዚህ ጊዜ ብቻ ነው። ጸሎት በራሳችን ራስ-ወዳድነት ያልተወሰኑትን አስተዋይና መንፈሳዊ ውሳኔዎች ለመስጠት መሠረታዊ ነገር ነው። ከምሳሌ 3:5-6 እና 16:3 እንደምንረዳው፣ መንገዳችንን ለእግዚአብሔር አሳልፈን ብንሰጥና በራሳችን ማስተዋል ባንደገፍ፣ እግዚአብሔር ይመራናል። ምንም እንኳን እግዚአብሔር በአንድ ሁኔታ ውስጥ የሚፈልገውን ነገር በትክክል ባናውቅም፣ እግዚአብሔር ፈቃዱ ያልሆነውን ነገር እንዳናደርግ እንዲያስቆመን በመጠየቅ በእርሱ ላይ መደገፉችንን እናሳያለን። ጳውሎስ ወደ መቄዶንያ እስኪሻገር ድረስ (የሐዋ. 16:6-10) የጳውሎስን በሮች ሊዘጋ እንደ ነበረ ሁሉ፣ እኛም መንግሥቱን ለማስፋፋት የማያግዝ ተግባር እንዳንፈጽም ሊያስቆመን ይችላል።

ነገር ግን አንድ ነገር እንዲከሰት መጸለይና ተስፋ ማድረግ ብቻ በቂ አይደለም። እግዚአብሔር ጸሎታችንን ያከብራል። ነገር ግን እርሱ የሰጠንን ጥበብ ተጠቅመን ዕቅድ ማውጣታችንም ያስደስተዋል። ነህምያ ሲጸልይና ሲያቅድ እንደ ነበረ ሁሉ (ነህ. 1-2)፣ እኛም መጸለይና ዕቅድ ማውጣት አለብን። ይህንን የምናደርገው ግን



ሁልጊዜም እግዚአብሔር የሚፈልገውን ብቻ ለማድረግ በመፈለግ ሊሆን ይገባል።

25ኛ ጥያቄ:- ሀ) አንተ ወይም የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ዕቅድ ካወጣችሁ በኋላ እግዚአብሔር እንዲባርክላችሁ የምትጠይቁበትን ሁኔታ ግለጽ። ለ) እግዚአብሔር ዕቅዱን እንዲሰጠን መጠየቅ ዕቅዳችንን ለእርሱ ከመስጠት የሚሻለው እንዴት ነው?

3. አእምሯችንን በእግዚአብሔር ቃል መሙላት አለብን። የእግዚአብሔር ቃል እርሱ በአጠቃላይ ምን እንድናደርግ እንደሚፈልግ የሚያሳውቁንን ብዙ ትእዛዛት ወይም መርሖዎች የያዘ ነው። ለምሳሌ፣ መጽሐፍ ቅዱስ በአድልዎ የተፈጸመ ማንኛውም ነገር ትክክል አለመሆኑን ይነግረናል (ያዕ. 2:1፣ 9)። ስለዚህ፣ ውሳኔያችን በሰዎች መካከል አድልዎ የሚያደርግ መሆኑን ከተገነዘብን፣ ይህ ውሳኔ ከእግዚአብሔር ሊሆን እንደማይችል ግልጽ ይሆንልናል። እንዲሁም እግዚአብሔር «ለጠፉት በጎች» እንደሚገደው እናውቃለን። ሄደን እንድንፈልጋቸው ይፈልጋል። በመሆኑም፣ ዕቅዶቻችን ሁሉ በቤተ ክርስቲያናችን ላይ ያተኮሩና ላልዳኑት ሰዎች ግድ የሌላቸው ከሆኑ፣ ምናልባትም የእግዚአብሔርን ዕቅዶች እየፈጸምን ላይሆን ይችላል። በተጨማሪም፣ እግዚአብሔር ልጆቹ በመንፈሳዊ ብስለት እንዲያድጉ ይፈልጋል። ስለሆነም ዕቅዶቻችን በምድራዊ በረከቶች ላይ ትኩረት የሚያደርጉ ከሆነ፣ ምናልባትም የእግዚአብሔርን ዕቅዶች እየፈጸምን ላንሆን እንችላለን። ከዚህም በላይ፣ እግዚአብሔር ክብሬን ለሌላ አልሰጥም ይላል (ኢሳ. 42:8)። እኛም ለቤተ ክርስቲያናችን ክብርን ለማስገኘት አንድን ተግባር የምናከናውን ከሆነ፣ ከእግዚአብሔር ሊሆን አይችልም።

ማንኛውም የቤተ ክርስቲያን መሪ ልቡንና አእምሮውን በእግዚአብሔር እውነቶች እስካልሞላ ድረስ፣ አንድ ነገር ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር መስማማት አለመስማማቱን በትክክል ሊያውቅ አይችልም። ጥልቅና ሰፊ የእግዚአብሔር ቃል እውቀት እንደ ጥልቅ የዛፍ ሥር ነው። ምንም እንኳን የአሳብ ነፋስ

ቢመጣም፣ የቃሉ ሥር አግዚአብሔር ወደሚፈልገን ስፍራ እንድንመለስ ያደርገናል።

> 26ኛ ጥያቄ፡- የእግዚአብሔርን ቃል የሚያወቁና የማያውቁ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በሚሰጧቸው ውሳኔዎች ውስጥ የታዘብካቸውን ልዩነቶች ግለጽ።

4. እግዚአብሔር ፈቃዱን እንድናውቅ ሰማድረግ ወይም የክርስቶስ አሳብ እንዳለን ለማረጋገጥ የሌሎች አማኞችን መንፈሳዊ ጥበብ ይጠቀማል (ምሳሌ 15:22)። አንድ ሰው እንደ ተናገረው፣ የቤተ ክርስቲያን መሪ ውሳኔ ሰመስጠት የራሱን ጥበብ ብቻ የሚጠቀም ከሆነና ራሱን ብቻ የሚያዳምጥ ከሆነ፣ ሞኝ አማካሪ አለው ማለት ነው። አንድ መሪ ብቻውን የሚያስተላልፈው ትልቅ ውሳኔ እምብዛም ውጤታማ አይሆንም። ይህ በግለሰቡ ብቁ ያልሆነ ተሞክሮ፣ ፍጹምነት የጎደለው አመለካከትና ከፊል አውቀት የተገደበ ነው። አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ ወይም የመሪዎች ቡድን የአግዚአብሔርን ፈቃድ በአውነት ሰማወቅ ከፈለጉ፣ የሌሎችን ሰዎች ምክር መስማት አለባቸው። ይህም ማለት በስብሰባ ላይ ሰዎች ያለምንም መቀያየም አሳባቸውንና አመለካከታቸውን በግልጽና በእውነተኛነት የማካፈል ነጻነት ሊኖራቸው ይገባል ማለት ነው።

አንድ መሪ በአንድ ሁኔታ ውስጥ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ሰማወቅ እግዚአብሔር በዙሪያው ያስቀመጣቸውን መንፈሳዊ ሰዎች ምክር መስማትን መማር አለበት። እነዚህ መንፈሳዊ ሰዎች ከመሪው ጋርና እርስ በርሳቸው በአሳብ ሊለያዩና እውነትን ሊናገሩ እንደሚችሉ ማወቅ አለባቸው። አውነትን በፍቅር ሲናገሩ ይገባል (ኤፌ. 4:15)። አሳባቸውን በድፍረት የሚገልጹና ከመሪው የተለየ አሳብ ለማንጸባረቅ የሚችሉ ጥሩ አማካሪዎች በጣም ያስፈልጉናል። ጥሩ ውሳኔዎች ሊተሳሰፉ የሚችሉት የአሳብ ልዩነት ሲኖር ወይም ሰሎሞን እንዳለው «ብረት ብረትን ሊስል» ነው (ምሳሌ 27:17)። የቤተ ክርስቲያን መሪም አማካሪዎች ከእርሱ የተለየ አሳብ በሚያቀርቡበት ጊዜ ጭምር ሰመስማት ፈቃደኛ መሆን አለበት። ዳዊት በትዕቢት ኃጢአት የወደቀውና በአግዚአብሔር ሕዝብ ላይ



ፍርድን ያመጣው የአማካሪዎቹን ምክር ለመስማት ባለመፈለጉ ነበር። (2ኛ ሳሙ. 24:1-4 አንብብ።) መሪዎች የሆንን ሁሉ ለስሕተት የተጋለጥን ሰዎች መሆናችንን በመረዳት ሌሎችን ልንሰማና ከአነርሱም ልንማር ይገባል። ልናድግ የምንችለው ሰዎችን ሰመስማት ፈቃደኞች ስንሆን ብቻ ነው። ሰዎች አሳባችንን በሚገዳደሩበት ጊዜ ሰራሳችን ጥብቅና የምንቆም ከሆነ፣ በግንዛቤአችን ልናድግ አንችልም። ይህም ራሳችንንና የአግዚአብሔርን ሕዝብ ወደ ተሳሳተ አቅጣጫ እንድንመራ የሚያደርግ አደገኛ ነገር ነው።

ይሁንና፣ አነዚህ የቤተ ክርስቲያን መሪው ወይም የቤተ ክርስቲያን አማካሪዎች በማስተዋል መመረጥ አለባቸው።

<u>አንደኛ</u>፣ አነዚህ ሰዎች በመንፈሳዊ ብስለታቸውና ጥበባቸው ምክንያት መመረጥ አለባቸው። መሪው የራሱ ጓደኞች ወይም ብዙውን ጊዜ አርሱ የሚለውን የሚደግፉ በመሆናቸው ብቻ ሰዎችን መምረጥ የለበትም። ወይም እንደ ትምህርትና ሥልጠና ያለውን ውጫዊ የብቃት መመዘኛ በመያዛቸው ብቻ ሊመረጡ አይገባም። የቤተ ክርስቲያን ሥራ መንፈሳዊ አንደ መሆኑ መጠን፣ ከእግዚአብሔር መንፈስ ጋር የማይስማማ ሰው ክፍፍልን ሊፈጥር ወይም ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር የሚቃረን ምክር ሊሰጥ ይችላል።

<u>ሁለተኛ</u>፣ መሪው ሌሎችን ሳይፈሩ እውነትን ሰመናገር የሚችሉትን ደፋር ሰዎች መምረጥ አለበት። አማካሪዎች ፈርተው አርስ በርሳቸው ወይም ከመሪው ጋር የሚስማሙ ከሆነ፣ አርባና ሊኖራቸው አይችልም። አንድ አማካሪ ጠቃሚ ሊሆን የሚችለው መሪው የማያውቀውን ነገር ሊነግረው ፈቃደኛ ከሆነ ብቻ ነው።

<u>ሦስተኛ</u>፣ አነዚህ አማካሪዎች የተለያዩ ባሕርያት፣ ሥረ-መሠረቶች፣ አገልግሎቶች፣ ነሳዎች፣ ወዘተ. . . ሊኖራቸው ይገባል። ሚዛናዊና የአስተዋይነት ውሳኔዎችን ሰማድረግ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የተለያዩ አመለካከቶች ያሏቸውን ሰዎች መጠቀም አለባቸው። ጉዳዩን ከተግባራዊ የአስተዳደር እይታ አንጻር

ስመመልከት ነገሮችን የማደራጀትና የማስተዳደር ብቃት ያላቸው ሰዎች መሳተፍ አለባቸው፡፡ ውሳኔዎችን ከረዥም የዕድገት አይታ አንጻር የሚመለከቱ ራእይ ያላቸው አማካሪዎችም መኖራቸው ጠቃሚ ነው፡፡ ስለ ገንዘብና አሰተዋይነት የተሞላበት የገንዘብ አጠቃቀም በቂ እውቀት ያላቸው አማካሪዎችም አስፈላጊዎች ናቸው፡፡ የእረኛ ልብ ያላቸውና ውሳኔዎች እንዴት በግል ደረጃ በሰዎች ላይ ተጽዕኖ እንደሚያሳድሩ የሚገነዘቡ፣ እንዲሁም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለረዥም ጊዜ የቆዩና ለውሳኔው ታሪካዊ አይታ የሚያሰጨብጡ ሰዎች መሳተፋቸው በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ በወንጌል ስርጭት ላይ ትኩረት የሚሰጡ አማካሪዎች መካተታቸው ደግሞ ቤተ ክርስቲያን በዚህ አስፈሳጊ አገልግሎት ላይ አጽንኦት እንድታደርግ ያስችላታል፡፡ በተጨማሪም፣ አማኞች እንዲያድጉ ስመርዳት የሚፈልጉ መጋቢዎች፣ ሴቶች በጉዳዩ ሳይ ያላቸውን አመለካከት የሚያሳዩ ሴቶች፣ ውሳኔው በወጣቶች ሳይ ስለሚያሳድረው ተጽዕኖ የሚያስረዱ ወጣቶች፣ የተማሩና ያልተማሩ፣ ሀብታሞችና ድሆች ሁሉ በውሳኔው ውስጥ መካተት አለባቸው፡፡ እንዲሁም ደግሞ የተሰያዩ ጎሳዎች፣ በተለይም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉት አናሳ ጎሳዎች መሳተፍ አለባቸው፡፡ ይህ ካልሆነ፣ ሰይጣን የጎሳ ውጥረትን ለመፍጠር ውሳኔውን ሊጠቀምበት ይችላል፡፡ እነዚህ አማካሪዎች ሁሉ ከሥረ-መሠረታቸው የየራሳቸውን እሳብ ሲያከሉና መንፈስ ቅዱስ ውይይታቸውንና እስተሳሰባቸውን ሲመራ፣ ጥሩ ውሳኔዎች ሲሰጡ ይችላሉ፡፡ መሪው የእነዚህን አማካሪዎች ውይይት በሚሰማበት ጊዜ፣ አሳባቸውን ሁሉ በአንድነት ለመጠቅለል አይፈልግም፡፡ ይልቁንም፣ እሳባቸውን በመመርመር ምርጥ ውሳኔ ለመስጠት ይሞክራል፡፡

2ኛ ጥያቄ፡- ሀ) በቤተ ክርስቲያናችሁ ወደ ፊት የወንጌል ሰርጭት ስለሚጫወተው ሚና አንድ ትልቅ ውሳኔ መስጠት ቢኖርብህ፣ ከምእመናን መካከል የማንን ምክር ትጠይቃለህ? ለምን ያንን ሰው መረጥክ? ለ) ብቻህን ከምትሰጠው የተሻለና ሚዛናዊ ውሳኔ እንድትሰጥ የሚያስችል ምክር እንዲሰጡህ አግዚአብሔር ሊጠቀምባቸው ይችላል ብለህ የምታስባቸውን መንፈሳዊ ወንዶችና ሴቶች ስም ዘርዝር፡፡



እንዳንድ እብያተ ክርስቲያናት እስቸኳይ ጉዳይ ካልገጠማቸው በስተቀር የሽማግሌዎቹን ሙሉ ድጋፍ ያሳገኘ ውሳኔ አያስተላልፉም፡፡ መንፈስ ቅዱስ ሁሉንም ሽማግሌዎች በግል እየመራቸው ከሆነ፣ እሳባቸውንና ፈቃዳቸውን ወደ ስምምነት ያመጣል ብለው ያምናሉ፡፡ እንድነት ከሌለ፣ መንፈስ ቅዱስ የሰዎቹን አሳብ አንድ እስኪያደርግ ድረስ ውሳኔውን ያዘገዩታል፡፡ ውሳኔውን ተግባራዊ ማድረጉ ብዙውን ጊዜ በቦርዱ አሳባቸው ውድቅ የተደረገባቸውን ሰዎች ስሜት ይጎዳል፡፡ በውሳኔው ላይ እሳባቸው ውድቅ የተደረገባቸው ሰዎች ብዙውን ጊዜ ውሳኔውን ተግባራዊ ለማድረግ የጸሎትና የሥራ ድጋፍ አያደርጉም፡፡

5. እግዚአብሔር በሁኔታዎች ውስጥ እየተንቀሳቀሰ እንደ ሆነ ተመልከት፡፡ ሁልጊዜም ማለት ይቻላል፣ እግዚአብሔር በሚንቀሳቀስበት ጊዜ፣ ነፋሱ ሳይታይ የዛፎች ውዝዋዜ እንደሚታይ ሁሉ፣ ግልጽ የሆኑ ምልክቶች ይታያሉ፡፡ ስለዚህ፣ እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሰዎች በሆነ አገልግሎት ውስጥ እንዲሳተፉ ሸክም ሰጥቷቸው እንደ ሆነ እንመለከታለን፡፡ ወይስ ሰዎች ማመን መጀመራቸውን የሚያሳዩ ምልክቶች አሉ ወይ? ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል ለማጥናት ይፈልጉ ይሆናል፡፡ ለዎች ብዙ ለዎች ለአምልኮ ይሰባሰቡ ዘንድ ትልቅ የቤተ ክርስቲያን ሕንጻ መሠራት እንዳለበት ወይም ሌላ ቤተ ክርስቲያን መከፈት እንዳለበት እየተናገሩ ነው? እነዚህ ነገሮች ብዙውን ጊዜ እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንን ወደ የት አቅጣጫ ለመውሰድ እንደሚፈልግ ያመላክታሉ፡፡

6. ቀደም ሲል እግዚአብሔር ምን ሲያደርግ እንደ ነበረ ተመልከት፡፡ እግዚአብሔር ብዙውን ጊዜ ፍጹም አዲስ ነገር በድንገት አይጀምርም፡፡ ይልቁንም፣ እግዚአብሔር ሕዝቡን የሚመራውና የሚንቀሳቀሰው ቀስ በቀስ በጊዜ ሂደት ነው፡፡ ስለሆነም፣ ወደ ኋላ መለስ ብለን ከአንድ፣ አምስትና አሥር ዓመታት በፊት የነበሩትን ሁኔታዎች በማጤን እግዚአብሔር መሪዎችንና ሕዝቡን ወዴት ይመራ እንደ ነበረ ልንረዳ እንችላለን፡፡ እግዚአብሔር ሕዝቡን በሆነ መንገድ ሲመራ እንደ ነበረ መረዳታችን ያ ዕድገት እንዲቀጥል

እንዴት አስተዋጽኦ ማድረግ እንዳለብን ያሳየናል። ስለዚህ፣ ዕቅዶቻችን እግዚአብሔር ሊሠራ ከነበረበት ቦታ ይጀምሩና ወደ በለጠ ዕድገት ለመምራት የሚያስችሉን መሆን አለባቸው። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ፍጹም አዲስ ነገር በመጀመር ታላቅ መሪዎች መሆናቸውን ለማሳየት የሚገዳደራቸውን ፈተና ማሸነፍ አለባቸው። ታላቅነታችንን በዚህ መንገድ ለማሳየት የምንፈልግ ከሆነ፣ ይህ የሚሆነው አንድም በራሳችን ስለማንተማመን (ሕዝቡ ምን እንደሚል ስለምንፈራ)፣ ወይም ትዕቢተኞች ስለ ሆንን (ከሌሎች በላይ መሆናችንን ለማስረገጥ) ነው ማለት ነው። ሁለቱም ኃጢአት በመሆናቸው፣ እንዲህ ዓይነት አስተሳሰብ ያለው መሪ ንስሐ ሊገባ ይገባል። እግዚአብሔር እያንዳንዱ መሪ በተመረጠ ቁጥር አሳቡንና ዕቅዶቹን ሲቀያይር አይኖርም።

7. የልባችን ፍላጎት ትክክል ለመሆኑ እርግጠኞች ከሆንን፣ ለቤተ ክርስቲያናችን እግዚአብሔር ፈቃዱን እንዲያሳውቅ በእውነተኛነት የምንሻ ከሆንን፣ እግዚአብሔር በልባችን ውስጥ ሸክም አኑሮ እንደ ሆነ መመልከት አለብን። እግዚእብሔር ብዙውን ጊዜ አንድን ነገር እንድናደርግ በማነሣሣት ፈቃዱን ይገልጥልናል (ፊልጵ. 2:13፤ መዝ. 37:4)። የእግዚእብሔርን ፈቃድ ለማድረግ ከልባችን የምንሻ ከሆነ፣ ወደ ራሳችን በመመልከት ምን ማድረግ እንደምንፈልግ መረዳት አለብን።

8. ውሳኔውን በምናደርግበት ጊዜ በልባችን ውስጥ ሰላም አለ? ውሳኔው ሰላም የሚነሳን ከሆነ፣ ይህ መንፈስ ቅዱስ በልባችን ውስጥ ውሳኔውን እንዳላጸደቀ የሚያሳይ ስለሆነ፣ እንጠብቃለን። እዚህ ላይ ግን ውሳኔው የሚጠይቀው እምነት ሊኖረን ባለመቻሉ ውሳኔውን እየተጠራጠርን አለመሆናችንን ማረጋገጥ አለብን። እግዚአብሔር ሕዝቡ በእርሱ ላይ በመደገፍ የማይቻል የሚመስለውን ነገር እንኳን እንዲያደርግ ይፈልጋል። እግዚአብሔር አንድን ነገር እንድናደርግ እንደ ጠየቀን እርግጠኞች ከሆንን፣ ሥራው ከአቅማችን በላይ ቢሆን እንኳን በውሳኔያችን መጽናት አለብን። እግዚአብሔር አንድን ነገር እንድናደርግ ከጠየቀን በኋላ ሥራውን ለማከናወን የሚያስፈልጉንን ነገሮች በፍጹም



አይነፍገንም። ምንም እንኳን የሚያስፈልጉትን ነገሮች እኛ በምንፈልግበት ጊዜ ላይሰጠን ቢችልም፣ በራሱ ጊዜ የሕዝቡን እምነትና ታዛዥነት ያከብራል። ይህ የሚሆነው ግን ጉዳዩ የራሳችን የራስ-ወዳድነት ዕቅድ ሳይሆን፣ የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን ስናውቅ ነው።

| |
|---|
| 28ኛ ጥያቄ:- ሀ) ከላይ የተጠቀሰውን መስፈርት በመጠቀም በአሁኑ ጊዜ ቤተ ክርስቲያናችሁ የተጋፈጠችውን ውሳኔ ግለጽ። ቤተ ክርስቲያናችሁ ከእግዚአብሔር የሚመጣውን የአስተዋይነት ውሳኔ እንድታደርግ እነዚህ 8 ነጥቦች እንዴት ሊረዷት ይችላሉ? ለ) መሪዎች ቤተ ክርስቲያን የምትጋፈጣቸውን ጉዳዮች በተመሰከተ አስተዋይነት የታከለባቸውን ውሳኔዎች ለመስጠት እንዲችሉ ከተለመደው የውሳኔ አሰጣጣቸው ውስጥ መለወጥ ያለባቸው ነገር ምንድን ነው? |

## ጥሩ ውሳኔ እንዳንሰጥ የሚያደርጉ የተለመዱ ወጥመዶችን ልብ በሉ።

በአብዛኛው የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የአስተሳሰብ መንገድ ጥሩ ውሳኔዎች የማድረግ ችሎታቸውን ይገድበዋል። ከዚህ በታች መሪዎች ጥንቃቄ ሊያደርጉ የሚገባቸው አንዳንድ አሳቦች ቀርበዋል።

1. «ብዙ ጊዜ ወስጄ ብጠብቅ፣ ችግሩ የራሱን መፍትሔ ያመጣል።» የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ውሳኔ ባይሰጡ ችግሩ በራሱ ጊዜ እንደሚቀረፍ በማሰብ አስቸጋሪ ውሳኔዎችን ለማዘግየት ማሰብ የለባቸውም። ሰዎችን የሚጎዳና እንዲጣሏቸው የሚያደርግ ውሳኔ ላለመስጠት ሲሉ፣ ብዙ መሪዎች፣ ችግሩ በራሱ ጊዜ ይቀረፋል ብለው በማሰብ፣ ውሳኔ ከመስጠት ይቆጠባሉ። ይህ ግን እምብዛም የሚሆን ነገር አይደለም። አብዛኞቹ አስቸጋሪ ውሳኔዎች ውስብስብ ናቸው። ለምን ቢባል፣ የትኛውም ውሳኔ ቢሰጥ፣ የሆነ ሰው መጎዳቱ አይቀርምና።

ውሳኔውን ማዘግየት ብዙውን ጊዜ ችግሩን ያባብሰዋል።

በመጀመሪያ፣ አንድ ሰው ውሳኔውን ተቀብሎ ወደ ፊት የሚጓዝበትን ጊዜ በማራዘም ችግሩን የከፋ ያደርገዋል። በአመዛኙ

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሚፈልጉት ነገር የማይቻል መሆኑን ለሰዎች አይናገሩም። ስለዚህ፣ «ከአንድ ወር በኋላ ተመለስ። ምናልባትም ያን ጊዜ መልስ ይገኝ ይሆናል፣» ይላሉ። የተጠየቀው ነገር የማይቻል መሆኑን ግለሰቡ ከእነርሱ እንዲሰማ አይፈልጉም። ይህ ለጊዜው ያልተፈለገውን ዜና የማዘግየት ዘዴ ውሳኔው እንደ ተላለፈ በትሕትና የሚሰጥ ግልጽ ምላሽ ሊያስከትል ከሚችለው የበለጠ የስሜት መጎዳትን ያስከትላል። ይህ የምንወደው ሰው በጣም በሚታመምበት ጊዜ ከሚሆን ሁኔታ ጋር ተመሳሳይ ነው። ታማሚው እንደሚሞት ብናውቅም፣ ጊዜው እየቆየ ሲሄድ ሥቃያችንም በዚያው ልክ ያይላል። የበሽታውና የሞቱ ጊዜ ፈጣን በሚሆንበት ጊዜ ግን ሥቃያችን ይቀንሳል። ወዲያውኑ ሥቃዩን ተጋፍጠን ከችግሩ ጋር ራሳችንን ለማስተካከል እንችላለን። በተመሳሳይ ሁኔታ፣ ምንም እንኳን ውሳኔው ግለሰቡን የሚጎዳ ቢሆንም፣ በፍጥነት ውጤቱን ካወቀ፣ ቀጣይ እርምጃዎችን ለመውሰድ ያስችለዋል።

<u>ሁለተኛ</u>፣ ምላሽ እስካልተሰጠ ድረስ፣ ግለሰቡ አንድ ቀን ውሳኔው እኔ በምፈልገው መንገድ ይወሰንልኛል በማለት በተስፋ ይጠባበቃል። ተስፋው እየተገነባ ከሄደ በኋላ፣ እንደማይቻል ማወቁ ግን የበለጠ ይጎዳዋል።

> **29ኛ** ጥያቄ፡- ሀ) ብዙውን ጊዜ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለሰዎች ጥያቄያቸው ተቀባይነት አለማግኘቱን ለመናገር የማይፈልጉት ለምንድን ነው? ለ) አስደሳች ያልሆነውን ምላሽ በፍጥነት መስጠቱ ይሻላል ወይስ ችግሩ የራሱን መፍትሔ እስኪያመጣ ድረስ መቆየት? መልስህን አብራራ። ሐ) ውሳኔውን ማዘግየት በኋላ አይሆንም የሚል ምላሽ ለቀለጠው ለው ችግሩን ያባባሰበትን ሁኔታ ግለጽ።

**2.** «ተጨማሪ መረጃ ባገኝ፣ በቀላሉ ውሳኔ መስጠት እችል ነበር።» የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ውሳኔ ከመስጠታቸው በፊት የተቻላቸውን ያህል መረጃ ማግኘታቸው አስፈላጊ ነገር ነው። ነገር ግን መረጃ እያሰባሰብን በጣም ከቆየን፣ ብዙውን ጊዜ ችግሩ እየከፋ ይሄዳል። ውሳኔው በቀላሉ በሚሰጥበት ጊዜ ብዙ ሁኔታዎች ቀለል ባለ መንገድ ሊፈቱ ይችላሉ። ለምሳሌ ያህል፣ ሁለት ሰዎች ወይም



ሁለት የቤተ ክርስቲያን ቀጣናዎች አለመግባባት ከፈጠሩ፣ ከመሪዎች የሚመጣው መፍትሔ እየቆየ በሚሄድበት ጊዜ፣ በመካከላቸው ያለውም ጸብ እየጨመረ ይሄዳል። መጥፎ የቃላት ልውውጦች ይፈጠሩና ለዎች የከፉ ሁኔታዎችን ማሰብ ይጀምራሉ። ሁኔታዎች ጠንከር በሚሉበት ጊዜ፣ ጥሩ መፍትሔ ማግኘቱ አስቸጋሪ ይሆናል። ስለሆነም፣ የምንፈልጋቸው መረጃዎች ሁሉ ባይሟሉልንም እንኳን፣ በአብዛኛው በፍጥነት ውሳኔ መስጠቱ አስፈላጊ ነው። እንደ እውነቱ ከሆነ፣ የመረጃ ስብሰባውም ማለቂያ የሌለው ተግባር ነው። በመሆኑም፣ የተቻለንን ያህል መረጃ በፍጥነት ሰብስበን ውሳኔ መስጠት አለብን። ብዙም መረጃ ሰበሰብን ወይም ጥቂት፣ በመጨረሻው ላይ አስቸጋሪ ውሳኔዎች አስቸጋሪ መሆናቸው የማይቀር ነው። በሰዎች መካከል ንዴት በሚኖርበት ጊዜ፣ ውሳኔዎችን ማስተናገዱ ከባድ ነው። ምንም ያህል ሰዎች በሂደቱ ውስጥ ለጊዜው ቢጎዱም፣ አብዛኞቹ ከባባድ ውሳኔዎች በዋናነት የቤተ ክርስቲያን መሪው ከሁሉም የተሻለውን መንገድ መርጦ ተግባራዊ እንዲያደርግ የሚጠይቁ ናቸው።

3. «ይህ ከባድ ውሳኔ ስለሆነ፣ ለበላይ ኃላፊ አስተላልፋለሁ። አስቸጋሪ ውሳኔዎችን የሚሰጠው ሁልጊዜም ዋናው ኃላፊ ነው። እርሱ ሁሉንም ነገር የበለጠ ስለሚያውቅ፣ የተሻለ ውሳኔ መስጠት ይችላል።» በርግጥ፣ ሁሉም የአመራር እርከን ውሳኔ የመስጠት ዳርቻውን ማወቅ አለበት። አስቸጋሪ ውሳኔዎችን ከመስጠት አስቀድሞ የበላይ አመራርን ማነጋገሩም ጠቃሚ ነው። ነገር ግን ለዚያ የአመራር ደረጃ ውሳኔ መስጠት ያንተ ኃላፊነት ከሆነ፣ ውሳኔ መስጠት ይኖርብሃል። አብዛኞቹ ውሳኔዎች በተቻለ መጠን ለሁኔታው በቀረበ መንገድ መስጠት አለባቸው። የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ስለ ቤተ ክርስቲያናቸው ውሳኔ መስጠት አለባቸው። የቀጣና ወይም የዞን መሪዎች ውሳኔ እንዲሰጡላቸው መጠበቅ የለባቸውም። አብዛኞቹን መረጃዎች የሚያውቁት ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸው ሰዎች ናቸው። ሰዎችን በሚገባ ያውቋቸዋል። ውሳኔው ምን እንደሚያስከትልም በደንብ ያውቃሉ። ስለሆነም፣ እንድ መሪ አስቸጋሪ ውሳኔ የሚጠይቁትን ነገሮች ለበላይ ኃላፊዎች ከማስተላለፉ በፊት የሚችለውን ያህል ጥረት ማድረግ አለበት።

ከባባድ ውሳኔዎችን የበላይ ኃላፊዎች እንዲሰጡ የሚጠይቁት ፈሪ መሪዎች ናቸው። ራሱ ኃላፊነትን እንደ መውሰድ፣ የበላይ ኃላፊዎች የሕዝቡን ቁጣ እንዲጋፈጡ ማድረግ ነው። ይህ የራሱን የአመራር ችግሮች በመጋፈጥ ላይ ላሰው የበላይ ኃላፊ ፍቅር አለማሳየትም ነው።

ጉዳዩ ለበላይ ኃላፊዎች በሚተላለፍበት ጊዜ፣ ወዲያውኑ ከእውነታው የበለጠ ክብደት ይሰጠዋል። ሰዎች ለአመለካከታቸው ማሸነፍ ተግተው ለመታገል ይቆርጣሉ። ውሳኔውን ወደሚፈልጉት አቅጣጫ ለመውሰድ ሲሉ የውሸት መረጃዎችን ይሰጣሉ። በዚህ ከፍተኛ የአመራር ደረጃ የተሰጠው ውሳኔ በተሸናፊዎቹ ላይ የሚያስከትለው ኀፍረትም የዋዛ አይሆንም። የበላይ አመራር በአስቸጋሪ ውሳኔ ውስጥ መሳተፍ ያለበት የበታች የቤተ ክርስቲያን አመራር የሚችለውን ውሳኔ ከሰጠ በኋላ እልባት ካላገኘ መሆን አለበት።

የበላይ አመራሮች ከበታች አመራሮች ጋር በሚሠሩበት ጊዜ፣ የበታች አመራሮችን ሥልጣን ላለመጫን ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው። ይህ ካልሆነ፣ የቤተ ክርስቲያን ምእመናን ሁሉንም ውሳኔ ወደ ዋናው መሪ ለመውሰድ መፈለጋቸው የማይቀር ነው። ይህ ደግሞ ብዙ ከባባድ ጉዳዮችን በትንሽ መረጃ ላይ ተመሥርቶ እንዲወሰን ያስገድደዋል። ጉዳዩ እልባት ሳያገኝ ቀርቶ ከበላይ ኃላፊዎች ዘንድ ከተላለፈ፣ የበላይ አመራሮች የታች አመራሮች ፍትሐዊ ውሳኔ ለመስጠት ጥረት ማድረጋቸውን ማረጋገጥ አለባቸው። ውሳኔያቸው ፍትሐዊና በጣም ጥሩ ከሆነ፣ የበላይ ኃላፊዎች የበታች አመራሮችን ውሳኔ ማጽደቅ አለባቸው።

ብዙ የበላይ ኃላፊዎች የበታች አመራሮችን ውሳኔዎች የመሻርን ስሕተት ይፈጽማሉ። ይህ ብዙ ችግሮችን ያስከትላል። በመጀመሪያ፣ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች በቤተ ክርስቲያናቸው ፊት ለኀፍረት ስለሚጋለጡ፣ ከዚያ በኋላ የአመራር ሥራ የበለጠ ከባድ ይሆንባቸዋል። ሁለተኛ፣ በሚቀጥለው ጊዜ ከባድ ውሳኔ የሚጠይቅ ጉዳይ ሲገጥማቸው፣ እነዚህ የበታች መሪዎች በቀጥታ ለበላይ ኃላፊዎች ማስተላለፋቸው አይቀርም። በዚህ



ጊዜ የበላይ ኃላፊዎች ከራሳቸው ዋና ዋና ሥራዎች በተጨማሪ የበታች መሪዎችንም ውሳኔዎች ጭምር የመስጠት ኃላፊነት ይኖርባቸዋል። ሦስተኛ፣ የትኛውንም ከባድ ውሳኔ ለመስጠት ባላመፈለጋቸው ምክንያት፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በአመራር ችሎታቸው ማደጋቸውን ያቆማሉ። አንድን ሁኔታ ገምግሞ ምርጥ ውሳኔ የመስጠትን ብቃት ሊማሩ አይችሉም። ራሳቸው ከመወሰን ይልቅ አስቸጋሪ ጉዳዮች በገጠሟቸው ቁጥር ለበላይ ኃላፊዎች የማስተላለፍን ልማድ ያዳብራሉ። አራተኛ፣ የበታች ኃላፊዎች በበላይ ኃላፊዎች ላይ ምሬት ስለሚኖርባቸው፣ የበላይ ኃላፊዎችን ውሳኔዎች አይሰሙም።

> 30ኛ ጥያቄ፡- ሀ) የቤተ ክርስቲያን የበታች አመራሮች ራሳቸው ሊወስኑ የሚገባቸውን ጉዳዮች ለበላይ ኃላፊዎች ሊያስተላልፉ የተመለከትክበትን ሁኔታ ግለጽ። ይህ በጉዳዩና በመሪዎች ላይ ያስከተለው ውጤት ምንድን ነው? ለ) የበላይ ኃላፊዎች በአንድ ሁኔታ ውስጥ ጣልቃ በመግባት የበታች ኃላፊዎችን ሥልጣን የተጫኑበትን ሁኔታ ግለጽ። ይህ በሁኔታውና በመሪዎች ላይ ያስከተለው ውጤት ምንድን ነው?

4. «ችግሩ ገና አሳሳቢ ስላልሆነ፣ በጣም አሳሳቢ እስኪሆን ድረስ እንጠብቅና ከዚያ በኋላ እንፈታዋለን።» ብዙውን ጊዜ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አንድ ችግር መከሰቱን ባወቁ ጊዜ ወዲያውኑ መፍትሔ ስለማይፈልጉለት ከቀውስ ወደ ቀውስ ይሄዳሉ። ከማሳችን ላይ አንድን ተክል ለማስወገድ ከፈለግን፣ ጥሩው ጊዜ ገና ትንሽ እያለ እንጂ አድጎ ሥር ከሰደደ በኋላ አይደለም። በተመሳሳይ ሁኔታ፣ አንድን ችግር ለመፍታት የሚቀልለው ገና ትንሽ ሳለ እንጂ አድጎ ከተስፋፋ በኋላ አይደለም። ችግሩ ወደ ቀውስነት በሚሸጋገርበት ጊዜ፣ ብዙ ነገሮች ይፈጠሩና የበለጠ ያወሳስቡታል።

ሀ. የሰዎች ስሜት በይበልጥ እየተጋጋለ ይሄዳል። ሰዎች ስለ አንድ ነገር ስሜታዊ በሚሆኑበት ጊዜ፣ በትክክልና በፍትሐዊነት ለማሰብ ይቸገራሉ። ንዴታቸውና ትዕቢታቸው የሌላውን ግለሰብ አመለካከት እንዳያጤኑ ይከለክላቸዋል። እነርሱ የማይፈልጉትን ማንኛውንም ውሳኔ ይቃወማሉ።

ለ. የስሜት መጎዳቱ ለረዥም ጊዜ በሚቀጥልበት ወቅት ጥልቀቱ እየባሰ ይሄዳል። ይህም የፈውሱን ጊዜ የበለጠ ረዥም ያደርገዋል። ይህ በሰውነታችን ላይ የደረሰውን ትንሽ ቁስል በመፈወስና ሰፍቶ ትልቅ እስኪሆን ድረስ በመጠበቅ መካከል ያለውን ልዩነት የሚመስል ነገር ነው። ቁስሉ በሚያድግበት ጊዜ ወደ ሐኪም ቤት በመሄድ ለዶክተሩ ብዙ ገንዘብ መክፈልና የተፈለገውን ፈውስ ለማግኘት ብዙ ጊዜ መጠበቅ የግድ ይሆናል።

ሐ. ቀውስ በሚፈጠርበት ጊዜ የምንሰጠው ውሳኔ ቀደም ብለን በማስተዋል ከምንሰጠው ውሳኔ የከፋ ነው። ቀደም ተብሎ የሚሰጠው ውሳኔ ቀውስ እንዳይፈጠር ሊከላከል ወይም ችግሩ እንዳይባባስ የሚያደርግ ሊሆን ይችላል። እንደ መሪዎች ልናደርግ የምንችለው ነገር ቢኖር ስለ ጉዳዩ በቂ ዝርዝር መረጃዎችን ማሰባሰብ፣ በጉዳዩ ውስጥ የተካተቱትን ነገሮችና መርሖዎች፣ ብሎም እነዚሁ ነገሮችና መርሖዎች በችኮላ ሳይሆን ጊዜ ኖሮን በጥንቃቄ ውሳኔ ብንሰጥ ምን ዓይነት የረዥም ጊዜ አስከትሎቶችን ሊያመጡ እንደሚችሉ መመርመር ነው። ነገር ግን አንድ ነገር ወደ ቀውስነት ከተቀየረ በኋላ በችኮላ ውሳኔ ለመስጠት ስለምንገደድ፣ ብዙውን ጊዜ የችግሩን ምንጭ የሚያደርቅ ሳይሆን፣ የሰዎችን ቁጣ የሚያበርድ ውሳኔ ለመስጠት እንገደዳለን። የችግሩን ምንጭ ስለማናደርቅም፣ ችግሩ ተመልሶ ስለሚመጣ፣ ጊዜያችንን እባክነን ዳግም ለማስተናገድ እንገደዳለን።

መ. ብዙውን ጊዜ ችግሮች በፍጥነት ውሳኔ በሚያገኙበት ጊዜ ችግሩን ለመፍታት የሚያስችሉ ብዙ አማራጮች ይኖሩናል። ነገር ግን ችግሩ እየከፋ በሚመጣበት ጊዜ፣ ችግሩን ለመፍታት የሚያስችሉ አማራጮች እየቀነሱ ይሄዳሉ። ውሳኔው በማመቻመች ላይ በሚመሠረትበት ጊዜ፣ ሁለቱንም ወገኖች ደስ ለማሰኘት ጥረት ስለሚያደርግ ለእግዚአብሔር መንግሥት ከሁሉም የተሻለው ውሳኔ ሳይሆን ይቀራል።

5. «የሰጠሁትን ውሳኔ በተመለከተ አሳቤን የምቀይር ይመስለኛል። ምናልባትም ይህ ነገሮች የተሻለ ገጽታ እንዲኖራቸው ያደርግ ይሆናል።» መሪዎች ብዙ ጸሎት አድርገው አንድን አስቸጋሪ ጉዳይ



ከወሰኑ በኋላ በእመዛኙ ያደረግኩት ውሳኔ ከሁሉም የሚያሻል ይሆን? ብሎ መጨነቁ የተለመደ ነው። ሰዎች እየመጡ የተለያዩ አሳቦችን ሲሰጡ ወይም ቅሬታዎችን ሲያቀርቡ፣ አሳባችንን በመቀየር ሌላ ውሳኔ ለመስጠት እንፈተናለን። ነገር ግን መሪው ጉዳዮችን በመመርመር መጀመሪያውኑ ፍትሐዊ ውሳኔ ሰጥቶ ከነበረ፣ ቀደም ሲል ያላወቀው አዲስ መረጃ እስካልተገኘ ድረስ በውሳኔው መጽናት አለበት። መሪዎች አሳባቸውንና ውሳኔያቸውን በተደጋጋሚ በሚለዋውጡበት ጊዜ፣ ይህ ድርጊታቸው በምእመናን ላይ ብዙ ግራ የመጋባት ሁኔታዎችን ይፈጥራል። ሕዝቡ ለመሪያቸው የነበራቸው አክብሮት ይቀንስና ያነጋገረውን ሰው ሁሉ ለማስደሰት ሲል አሳቡን በተደጋጋሚ የሚቀይር ደካማ ሰው እንደ ሆነ ያስባሉ።

6. «ወደ ፊት ስለሚሆነው ነገር አልጨነቅም። አሁን ችግሩን በመፍታት ሰዎችን ማስደሰት አለብኝ።» የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ብዙውን ጊዜ ለጊዜው ችግሩን የሚያቃልልና ወደ ፊት የባሉ ችግሮች የሚፈጥሩትን ውሳኔዎች ይሰጣሉ። እንበልና አንድ የቤተ ክርስቲያን ሠራተኛ የደመወዝ ጭማሪ ይፈልጋል። ከቤተሰቡ ጋር ወደ ቤተ ክርስቲያን መሪ ይመጣና ደመወዙ ካልተጨመረ ሥራውን የሚለቅ መሆኑን ይገልጻል። የቤተ ክርስቲያን መሪዎቹ ግለሰቡ ሥራውን ሲለቅ የሚፈጠረውን ችግር ባለመፈለጋቸው ያላቸውን ይፈጽማሉ። ከዚያ በኋላስ? እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን ሠራተኛ እየመጣ ደመወዝ እንዲጨመርለት ይጠይቃል። ለሁሉም ሠራተኛ የፈለገውን ያህል ጭማሪ ለማድረግ የሚያስችል ገንዘብ ከየት ይመጣል? ውሳኔው ቤተ ክርስቲያን ገንዘቧን እንድትጨርስ ከማድረጉም በላይ፣ ሠራተኞቹ ገንዘብ ካልተሰጣቸው የበለጠ እንዲበሳጩ ያደርጋል። በዚህ ጊዜ ከሌሎች አገልግሎቶች (ለምሳሌ፣ ከወንጌል ስርጭት) ገንዘብ ወስደው የሠራተኞችን ደመወዝ ሊከፍሉ ቢችሉም፣ ቀጣይነቱ አስተማማኝ ካልሆነ፣ ሠራተኞቹ ቤተ ክርስቲያኑን ፍርድ ቤት ከሰሰው ችግሮችን ሊፈጥሩ ይችላሉ። ስለሆነም፣ ውሳኔ በምንሰጥበት ጊዜ ሁሉ አሁን ለችግሩ መፍትሔ መስጠታችንን ብቻ ሳይሆን የረዥም

ጊዜ ውጤቱን ጭምር ማሰብ አለብን:: ዛሬ መፍታት ያለባቸውን ችግር ለነገ የሚያሳድሩት ፈሪ መሪዎች ብቻ ናቸው::

7. «ሥራ በዝቶብን ደክመናል:: ስለዚህ ቶሎ ብለን ውሳኔውን ሰጥተን እንሂድ::» ሌላው ብዙውን ጊዜ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጥሩ ውሳኔ የማይሰጡበት ምክንያት ከችግሩ ጋር የተያያዙትን ችግሮች ሁሉ ለመዳሰስ የሚያስችል በቂ ጊዜ ስለማይወስዱ ነው:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በአብዛኛው በስብሰባ ላይ ጊዜያቸውን በአግባቡ አይጠቀሙም:: ብዙ ጊዜያቸውን በሪፖርቶችና በቤተ ክርስቲያኒቱ ላይ የረዥም ጊዜ ተጽዕኖ የማያስከትሉትን ነገሮች በመወያየት ያጠፋሉ:: ከዚያም በተዳከሙና ስብሰባው የሚጠናቀቅበት ሰዓት ሲደርስ፣ አስቸጋሪዎቹን ጉዳዮች እናነሣለን:: በዚህ ጊዜ ጥርት አድርጎ ማሰብ ከባድ ከመሆኑም በላይ፣ ሁሉም ሰው ወደ ቤቱ መሄድ ይፈልጋል:: ነገር ግን ውሳኔው መሰጠት እንዳለበት ሁሉም ያውቀዋል:: ስለዚህ ፈጣን ውሳኔዎችን እንሰጣለን:: ብዙውን ጊዜ እነዚህ የችኮላ ውሳኔዎች ችግሩን ያባብሱታል:: ስለሆነም፣ መሪዎች በስብሰባዎች ላይ ጊዜ በሚመድቡበት ጊዜ ብዙ ማሰብ የሚጠይቁትን ጉዳዮች ማስቀደምና፣ ያን ያህል አስፈላጊ ያልሆኑትንና ብዙ ማሰብ የማይጠይቁትን ወደ በኋላ መወያየት ይኖርባቸዋል::

8. «ይህ በጣም የሚያስደስተኝ ጉዳይ ስለሆነ፣ ራሴው ለመወሰን እፈልጋለሁ::» መሪዎች በአንድ ነገር ውስጥ ስሜታዊ ተሳትፎ ካላቸው፣ ጥሩ ውሳኔ ላይሰጡ ይችላሉ:: በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉትን አስፈላጊ ነገሮች ሁሉ ቸል በማለት፣ እኛ የምንፈልገው ጉዳይ ከሁሉም የበለጠ ነው ብለን እናስባለን:: ስለሆነም አንድ መሪ በአንድ ነገር ውስጥ ስሜታዊ ተሳትፎ በሚያደርግበት ጊዜ፣ አመለካከቱን ማካፈልና ሌሎች ውሳኔውን እንዲሰጡ ማድረግ ይኖርበታል:: ለምሳሌ፣ ጉዳዩ የመሪውን ዘመድ የሚመለከት ከሆነ፣ ውሳኔው በዝምድና ላይ ተመሥርቶ እንዳይሰጥ ወይም ሌሎች ሰዎች እንዲህ ዓይነት አመለካከት እንዳይኖራቸው ለመከላከል ሲባል፣ ውሳኔውን ሌሎች መሪዎች መስጠት አለባቸው:: ወይም ደግሞ ወንጌላዊ የሆነ ሰው ከሌሎች



ወንጌላውያን ካልሆኑት ሰዎች ጋር ውሳኔ መስጠት አለበት:: ይህም አመለካከቱን ሚዛናዊ ለማድረግ ያስችላል:: በሽማግሌዎች መካከል ጸብ ቢፈጠርና ሰብሳቢው ከሁለቱ ጸበኛ ቡድኖች የአንዱ ደጋፊ ከሆነ፣ ስለ ጉዳዩ ውሳኔ በሚሰጥበት ጊዜ እርሱ ተሳታፊ መሆን የለበትም:: ሰዎች ውሳኔውን ሊያከብሩ የሚችሉት አድልዎ የሌለበት ነው ብለው ሲያስቡ ብቻ ነው:: ካልሆነ ግን፣ የአድልዎ ቅሬታ ይሰማል::

31ኛ ጥያቄ:- ሀ) መሪዎች ሰዎችን ለማስደሰት በማሰብ አሳባቸውን በተደጋጋሚ ሲቀይሩ የተመለከትከው እንዴት ነው? ይህ በችግሩ ዘለቄታዊ ገጽታ ላይ ምን አስከተለ? ሰዎች ለመሪው የነበራቸው አክብሮት ጨመረ ወይስ ቀነሰ? ለ) አንድ መሪ በወቅቱ የነበረውን ችግር የፈታና ዳሩ ግን በኋላ ይበልጥ አስከፊ ችግር ያስከተለ ውሳኔ የሰጠበትን ሁኔታ ግለጽ:: ሐ) የወቅቱን ችግር ከመቅረፍ በተጨማሪ ወደፊትም ችግሮች እንዳይከሰቱ ለማድረግ ይቻል ዘንድ ውሳኔው ምን ዓይነት መሆን ነበረበት? መ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በእነዚህ ስምንት ወጥመዶች ሲያዙ የተመለከትከበትን ሁኔታ ግለጽ::

## አራተኛ ቀን

ትናንት አንድ መሪ ጥሩ ውሳኔ እንዲሰጥ ስለሚያስችለው ክህሎት ተምረናል:: ጥሩ ውሳኔ ካልተሰጠ፣ የእግዚአብሔር ሥራ ይደናቀፋል:: ችግሮች እንደ አሾህ በቅለው የቤተ ክርስቲያኒቱን ውጤታማነት ያንቃሉ:: ስለሆነም የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጥሩ ውሳኔዎች መስጠትንና ውሳኔዎችን በግል ደረጃ ሳይሆን በኮሚቴ ወይም በቦርድ መስጠትን መማር አለባቸው::

አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ ሁለት ዓይነት ውሳኔዎችን በመስጠቱ በኩል ክህሎቱን ሊያዳብር ይገባል::

በመጀመሪያ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪውን ውሳኔ የሚጠይቁ ጉዳዮች አሉ:: እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን መሪ በኃላፊነቱና በሥልጣኑ ክልል ውስጥ ብዙ ውሳኔዎችን የመስጠት ኃላፊነት አለበት:: እነዚህንም ውሳኔዎች በጥሩ ሁኔታ መስጠት አለበት::

ሁለተኛ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪው እንደ ኮሚቴ ወይም ቦርድ ያለውን አካል በመርዳት ውሳኔ እንዲሰጡ የሚያደርጋቸው ጉዳዮችም አሉ:: አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ የትኞቹን ውሳኔዎች ራሱ መስጠት እንዳለበትና የትኞቹን ከቦርዱ ጋር ማሳለፍ እንዳለበት ማወቁ በጣም አስፈላጊ ነው:: ነገር ግን ከመሪነት አስፈላጊ ሚናዎች አንዱ ቦርዱ ወይም ኮሚቴው ጥሩ ውሳኔ መስጠቱን ማረጋገጥ ነው:: መሪው ቦርዱ ጥሩ ውሳኔዎችን እንዲሰጥ መምራት አለበት::

መሪዎች ውሳኔዎችን በሚሰጡበት ጊዜ ሁለት ነገሮችን ማስታወስ አለባቸው::

1. አንድ መሪ በቅጡ ባልታሰበባቸው ጉዳዮች ላይ ውሳኔ እንዲሰጥ ግፊት በሚደረግበት ጊዜ፣ «እሺ» ከማለት ይልቅ «አይሆንም» ማለት አለበት:: ነገር ግን ሰዎችን ለማስደሰት ስለምንፈልግና «እሺ» የምትለው ቃል ደስታ እንደምትሰጣቸው ስለምናውቅ፣ ይህንን ማድረጉ ከባድ ነው:: መጀመሪያ «አይሆንም» ማለቱ የተሻለ የሚሆንባቸው ምክንያቶች አሉ:: በመጀመሪያ፣ የችኮላ ምላሽ በመስጠት በኋላ ለማስተካከል የሚያስቸግር ጥፋት ልንፈጽምና «አይሆንም» ከሚለው የባሱ የረዥም ጊዜ ችግሮችን ልንጋብዝ እንችላለን:: ሁለተኛ፣ ሰዎች መጀመሪያ «እሺ» ከተባሉ በኋላ «እምቢ» ከመባል ይልቅ መጀመሪያውኑ «አይሆንም» የሚል ምላሽ ቢሰጣቸው ይመርጣሉ:: የተፈለገውን ሥራ ማከናወን እንደምንችል ካወቅን በኋላ «እሺ» የሚል ምላሽ ልንሰጣቸው እንችላለን:: ነገር ግን «እምን» ካልን በኋላ ቃላችንን የማንጠብቅ ከሆነ፣ የሰዎች ስሜት በከፍተኛ ደረጃ ሊጎዳ ይችላል:: ይህም መጀመሪያውኑ አይሆንም ከማለት የከፋ ውጤት ያመጣል::

| |
|---|
| 32ኛ ጥያቄ:- ሀ) አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ በፍጥነት «እሺ» ማለቱ እንዴት ችግሮችን ሊያስከትልበት እንደ ተመለከትክ ግለጽ:: ለ) መጀመሪያ «እሺ» ካለ በኋላ «አይሆንም» ማለቱ መጀመሪያውኑ ነገሩ የማይቻል መሆኑን ከመግለጽ የከፋ የስሜት መጎዳት ያስከተለው እንዴት ነበር? |

2. ብዙ መዘዞችን የሚያስከትሉ ውሳኔዎች በመሪው ብቻ ሳይሆን፣ በቡድን መሰጠት አለባቸው:: እግዚአብሔር ለዎች አንድን



ጉዳይ በጥበብ እንዲወስኑ የሚያደርገው የሰዎችን ቡድን በመጠቀም ነው (ምሳሌ 15:22):: ስለሆነም፣ ጉዳዩ አጣዳፊ እስካልሆነ ድረስ፣ ጊዜ ወስደን የሌሎች ሰዎችን አስተዋጽኦ ልናካትት ይገባል::

| |
|---|
| 33ኛ ጥያቄ:- የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከግል ይልቅ በቡድን ቢወስኑ የተሻለ ውጤት ይኖራቸዋል የምትላቸውን ነገሮች ዘርዝር:: |

**እንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ ወይም የቤተ ክርስቲያን ቦርድ ጥሩ ውሳኔ ለመስጠት ሊከተሏቸው የሚገቡ ደረጃዎች::**

እንደ ማንኛውም ክህሎት፣ ጥሩ ውሳኔ መስጠትን ለመማርም ጊዜ ያስፈልገዋል:: መጀመሪያ አካባቢ፣ ከታች የተጠቀሱት ደረጃዎች ጊዜ የሚወስዱና የማይመቹ ሊመስሉ ይችላሉ:: ነገር ግን፣ ክህሎቱን እያዳበርን ስንሄድ፣ እነዚህ ነገሮች የባሕርያችን አካል ይሆኑና ስለ ሂደቱ ሳናስብ ልናከናውናቸው እንችላለን:: ስለሆነም፣ እነዚህ ነገሮች የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና ቦርዶች ጥራት ያላቸውን ውሳኔዎች እንዲሰጡ የሚያግዟቸው ስለሆኑ ሊጠቀሙባቸው ይገባል::

1. መጀመሪያ ችግሩ ወደ ቤተ ክርስቲያን መሪው በሚመጣበት ጊዜ፣ መሪው ማን በዚህ ጉዳይ ላይ ውሳኔ ሊሰጥበት እንደሚገባ መመርመር አለበት:: ይህ መሪው ራሱ ሊሰጥ የሚገባው ነው? ወይስ ከእርሱ ኃላፊነትና ሥልጣን ውጭ የወጣና ሌላ ሰው ወይም ቡድን ሊሰጥ የሚገባው ውሳኔ ነው? ወይስ ይህን ውሳኔ ሌሎች ሰዎች እንዲሰጡ ሊወክላቸው ይችል ይሆን? ብዙውን ጊዜ የቤተ ክርስቲያን መሪው አንድን ውሳኔ መስጠት ያለበት፣

ሀ. ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት ስለ ጉዳዩ ለመጸሰይ የሚያስችል በቂ ጊዜ ካለው፣

ለ. ውሳኔውን ለመስጠት የሚያስችል ሥረ-መሠረትና ብቃት ካለው፣ እንዲሁም

ሐ. ጉዳዩ በጠቅላላይቱ ቤተ ክርስቲያን ላይ ተጽዕኖ የሚያስከትል የረዥም ጊዜ አስከትሎት ከሌለው ነው::

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ነጥቦች መሪው ማን ውሳኔውን መስጠት እንዳለበት እንዲወስን የሚያግዙት ናቸው:-

ሀ. ጉዳዩ ለሌላ ሰው (ለምሳሌ፣ ለቤተ ክርስቲያን የወንጌል አገልግሎት) በውክልና ተሰጥቶ ከሆነ፣ መሪው ውሳኔውን ለዚሁ ሰው ማስተላለፍ አለበት:: መሪው ራሱ ውሳኔውን የሚሰጥ ከሆነ፣ ውክልና የሰጠውን ግለሰብ ኃላፊነት ተጭኖታል ማለት ነው::

ለ. ጉዳዩ ከራሱ የሥልጣን ደረጃ በላይ ከሆነ፣ መሪው ጉዳዩን ለቀጣይ የአመራር እርከን ማስተላለፍ አለበት:: በአመዛኙ መሪው ስለ ጉዳዩ የራሱን አስተያየት በመስጠት፣ ውሳኔ የመስጠት ኃላፊነት ያለባቸው የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ውሳኔውን እንዲሰጡ ቢያደርግ መልካም ነው:: ከሥልጣን ክልሉ ውጭ ለሆኑት ጉዳዮች ውሳኔ መስጠቱ አያሌ ችግሮችን የሚፈጥር አደገኛ ነገር ነው::

ሐ. መሪው (ወይም ቦርዱ) ውሳኔ የመስጠት ኃላፊነት ካለባቸው፣ እና መሪው (ወይም ቦርዱ) ጊዜና ሥረ-መሥረት ካላቸው፣ ነገር ግን ችግሩ የረዥም ጊዜ መዘዞችን የሚያስከትል ከሆነ፣ አንድ ቡድን ተለይሞ ውሳኔ በመስጠቱ በኩል አብሮት እንዲሠራ ቢደረግ መልካም ነው::

መ. መሪው (ወይም ቦርዱ) ውሳኔ የመስጠት ኃላፊነት ካለበት፣ እና ነገር ግን ለመጸለይና ስለ ጉዳዩ በጥልቀት ለማሰብ የሚያስችል ጊዜ ከሌለው ወይም ደግሞ ውሳኔውን ለመስጠት የሚያስችል ልምድ ከሌለው፣ የቤተ ክርስቲያን መሪው ውሳኔውን የሚሰጡ ሌሎች ሰዎችን መወከል አለበት:: ማንኛውም መሪ ደካማና ጠንካራ ጎኖች አሉት:: ሁላችንም የራሳችንን ደካማና ጠንካራ ጎኖች ማወቅ አለብን:: ውሳኔው ጠንካራ ጎኖቻችንን የሚመለከት ከሆነ፣ በውሳኔው ውስጥ መሳተፍ ወይም ውሳኔውን መስጠት ይኖርብናል:: ነገር ግን ውሳኔው በደካማ ጎኖቻችን በኩል ከሆነ፣ በዚያ ጉዳይ ላይ ጠንካራ ጎን ያላቸው ሰዎች በውሳኔ አሰጣጡ ላይ እንዲሳተፉ ወይም ውሳኔውን እንዲሰጡ ማድረግ ይኖርብናል:: ለአንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ ምንም በማያውቀው ጉዳይ ላይ ሊቅ መስሎ መታየት ሞኝነት ነው:: ሌሎች ከእርሱ የተሻለ እውቀት ካላቸው፣ በጥልቀት አስበውበት ውሳኔ እንዲሰጡ ማድረግ አለበት:: ለምሳሌ፣ መሪው ወንጌላዊ ካልሆነ፣ ስለ ወንጌል ስርጭት ወይም የቤተ ክርስቲያን ተከላ ቀዳሚው ወሳኝ እርሱ መሆን የለበትም:: በዚህ በኩል ልምድ ያለው ሰው መፈለግና ውሳኔውን እንዲሰጥ ማድረግ ይኖርበታል:: የቤተ ክርስቲያን መሪ ው የቡድኑ አካል በመሆን ውሳኔ መስጠት፣ ወይም ቡድኑ ውሳኔ ከሰጠ በኋላ ውጤቱን እንዲያመጣለት ማድረግ ይኖርበታል::

የቤተ ክርስቲያን መሪው አንድን ጉዳይ ለአንድ ሰው በውክልና ከሰጠ ውሳኔያቸውን ሊሽር እንደማይችል እርግጠኛ መሆን አለበት:: የተወከለው ሰው በቂ መረጃ ከሌለው ወይም የተሳሳተ መ ረጃ ይዞ ከሆነ፣ ጉዳዩን እንደገና እንዲያጤኑት ሊጠይቅና ጥያቄ ዎችን በመጠየቅ ሊመራቸው ይችላል:: ነገር ግን ውሳኔያቸውን የሚሽር ከሆነ፣ ወደ ፊት ስለ ጉዳዩ በጥልቀት ለማሰብ አይፈልጉም:: ምክንያቱም የሚሰጡትን ውሳኔ መሪው እንደሚሽርባቸው ስለሚያስቡ ነው:: ጉዳዩ መሪው የራሱን አመለካከት ማካተት የሚፈልግ ከሆነ፣ መሪው ስለ ጉዳዩ የሚወያየው ቡድን አካል መሆን አለበት::

> 34ኛ ጥያቄ:- ሀ) ብዙ መሪዎች እውቀት ያላቸው ሰዎች ውሳኔ እንዲሰጡ ከማድረግ ይልቅ ራሳቸውን የሁሉም ነገር ሊቆች አድርገው የሚመለከቱበትን ምክንያት ግለጽ:: ለ) አንድ መሪ ብዙም በማያውቀው ጉዳይ ላይ የማይረባ ውሳኔ ሲሰጥ ያየህበትን ሁኔታ አብራራ::

2. መሪው ወይም ቦርዱ በተቻለው አቅም፣ በጉዳዩ ላይ አስቀድመው የተያዙትን አሳቦች ማስወገድ አለበት:: መሪው ስለ ጉዳዩ ጥናት ከማድረጉ በፊት መልሱ ይሄ መሆን አለበት የሚል አቋም ከያዘ፣ ጉዳዩን ከተለያዩ አመለካከቶች አንጻር ሊዳስስ አይችልም:: ለምሳሌ፣ እንዲት ጥሩ ቤተ ክርስቲያን አልባሳት ያላቸው ኳየሮች፣ ኪቦርድና የድምጽ ማጉያ ሊኖራት ይገባል ብሎ የሚያስብ ከሆነ፣ ቤተ ክርስቲያኒቱን ለማጠናከር ምን መድረግ አለበት? በሚል ውይይት ላይ የእርሱ አቋም እነዚህን ነገሮች ማሟላት ያስፈልጋል የሚል ይሆናል:: ወይም ደግሞ ሰዎችን ማሠልጠን የሚቻለው በክፍል ውስጥ ብቻ ነው የሚል እምነት

ካሰው፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ለማሠልጠን የተለያዩ የፈጠራ መንገዶች መጠቀምን አይቀበልም።

በተጨማሪም፣ የቤተ ክርስቲያን መሪው አእምሮውን ከየትኛውም ዓይነት ጥላቻ ማጽዳት አለበት። ስለሆነም ጉዳዩ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን፣ አንድን ዘመድ ወይም ጓደኛ፣ ከእርሱ ወይም ከጎሳው ጋር ጥሩ ግንኙነት የሌለውን የሌላ ጎሳ አባል የሚመለከት ከሆነ፣ ቀደም ሲል ስለ እነዚህ ሰዎች የነበረውን ጥሩ ያልሆነ አስተሳሰብ ከአእምሮው ለማውጣትና በንጹሕ መንፈስ ውሳኔ ለመስጠት መጣር አለበት። እያንዳንዱን ጉዳይ ከመጥፎ አስተሳሰብ በጸዳ አመለካከት ለመዳሰስ ካልሞከረ፣ ጥሩ ውሳኔ ሊሰጥ አይችልም። አንዳንድ ጊዜም ራሱን ከውሳኔው በማግለል የጥላቻ ስሜት የሌላቸው ሰዎች አድልዎአዊነት በሌለው መንፈስ ውሳኔውን እንዲሰጡ ቢያደርግ መልካም ነው።

> *35ኛ ጥያቄ፡- ሀ) መሪዎች ቀደም ሲል በአእምሯቸው ውስጥ ባቆሯቸው አሳቦች ምክንያት ጥሩና ሚዛናዊ ውሳኔ ለመስጠት የሚቸገሩባቸውን መንገዶች ግለጽ። ለ) ጥላቻ አንድ መሪ አስተዋይነት የሞላበት ውሳኔ እንዳይሰጥ እንዴት እንደሚከላከል ግለጽ።*

3. የቤተ ክርስቲያን መሪው ወይም ቦርዱ ስለ ጉዳዩ መወያየት ከመጀመራቸው በፊት ጉዳዩን በተመለከተ መረጃዎችን ማሰባሰብ አለባቸው። መረጃዎች ካልተሰባሰቡ፣ ውሳኔው የግምት ሥራ እንጂ በመረጃ ላይ የተመሠረተ ሊሆን አይችልም (ምሳሌ 24:3-4፤ 18:13)። መሪው በጥንቃቄ እውነቱን መመርመር እንጂ፣ በወሬ ወይም በሚሰማው ስሜት ላይ ተመሥርቶ ውሳኔ መስጠት የለበትም። በቂ መረጃ በማይኖረን ጊዜ፣ በአብዛኛው ውሳኔ የምንሰጠው በግምት፣ ትክክል ነው ብለን በምናስበው መንገድ ወይም የወደፊቱን በቅጡ ሳናስብ የአጭር ጊዜ ችግሮችን ለመፍታት ብቻ ይሆናል።

4. መረጃው ከተሰባሰበ በኋላ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪው ወይም ቦርዱ ውሳኔውን ለመስጠት እንዲችል መረጃውን መገምገም



አለበት። መረጃውን በምንገመግምበት ጊዜ፣ የሚከተሉትን ዓይነት ጥያቄዎች መጠየቅ አለብን፡-

ሀ. መጽሐፍ ቅዱስ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ስለ ጉዳዩ የሚያስተምረው ምንድን ነው?

ለ. በምጸልይበት ጊዜ እግዚአብሔር ለልቤ የሚያስተላልፈው መልእክት ምንድን ነው?

ሐ. በእውነት የምንፈልገው የእግዚአብሔርን ፈቃድ ነው ወይስ የራሳችንን ጥቅም?

መ. ስለ ጉዳዩ መንፈሳዊ ምክር ሊሰጠኝ የሚችለው ማን ነው? (ምሳሌ 11:14)

ሠ. እግዚአብሔር ስለሚፈልገው ነገር ከሁኔታዎች ምን ልንማር እንችላለን? (ምሳሌ 19:2)

መሪዎች ቀላል መልሶችን ከመፈለግ ይልቅ በሚነጋገሩበት ሁኔታ ውስጥ የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን እንደ ሆነ ለማወቅ ቁርጥ ውሳኔ ማድረግ ይኖርባቸዋል።

5. የቤተ ክርስቲያን መሪው ወይም ቦርዱ ከችግሩ ወይም ከጉዳዩ ከመጀመር ይልቅ፣ የውሳኔው ግብ ምን እንደ ሆነ መወሰን አለበት። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ባሉ ሁለት የማይስማሙ ቡድኖች መካከል ሰላም ለማውረድ ነው? ጠንካራ የወንጌል ስርጭት ፕሮግራም ለመመሥረት ነው? ሰዎች «ዲፕሎማ» አግኝተው ጥሩ ስሜት እንዲሰማቸውና የተሻለ ደመወዝ እንዲቀበሉ ለማስቻል ነው? ወይስ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያኖች ብቁ ሥልጠና ያገኙ ሰዎች እንዲኖሯቸው ነው? ብዙውን ጊዜ ሰዎች የጉዳዩ ዓላማ ምን እንደ ሆነ ሳያውቁ፣ ስለ ተግባራዊ እርምጃዎች ይነጋገራሉ፣ ይከራከራሉ። ከዚህ ይልቅ የውሳኔውን ዓላማ ግልጽ ማድረጉ ይሻል ነበር። ግቡ ከታወቀ በኋላ፣ ከዚሁ ግብ ለመድረስ የትኞቹ የተግባር እርምጃዎች እንደሚሻሉ መወሰኑ ቀላል ነው። በአመዛኙ አሰመግባባቶች የሚፈጠሩትና ለጉዳዩ በፈጠራ የታገዘ መፍትሔ ማምጣት የሚያዳግተው የቤተ ክርስቲያን መሪዎች

ለመወሰን ስለሚፈልጉት ጉዳይ ጥርት ያለ አሳብ ስለሌላቸው ነው:: ብዙ ግቦች ካሉ ደግሞ፣ መሪው የትኞቹ ግቦች ቅድሚያ ሊሰጣቸው እንደሚገባ ማሰብ አለበት:: ያን ያህል አስፈላጊ ባልሆኑት ጉዳዮች ላይ ጊዜ ከማባከን ይልቅ፣ ወሳኝ የሆኑትን ግቦች ማስቀደሙ የተሻለ ነው::

*ለምሳሌ፣ በክፍለ ማኅበራት ኅብረት ቦርድ ውስጥ አንድ መሪ በአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ውስጥ ለወንጌል ስርጭት የገንዘብ ማሰባሰቢያ ቀን እንዲካሄድ ጠየቀ እንበል:: ይህንን ተግባር በሚመለከት ሁለት አማራጮችን መጠቀም ይቻላል::*

*አንደኛ፣ የገንዘብ ማሰባሰቢያውን ቀን እንዴት ውጤታማ ማድረግና በተቻለ መጠን ብዙ ገንዘብ ማግኘት ስለሚቻልበት መንገድ ልትነጋገሩ ትችላላችሁ:: ይህ ጥልቅና የረዥም ጊዜ ጉዳዮችን የማያገናዝብ የአጭር ጊዜ አስተሳሰብ ነው::*

*ሁለተኛ፣ ጉዳዩን ሰፋ አድርጎ በመመልከት፣ «የወንጌል ስርጭቱ ዓላማ ምንድን ነው? ይህንን ግብ ለመምታት ከሁሉም የሚሻለው መንገድ የትኛው ነው?» የሚሉትን ጥያቄዎች ማንሣት ይቻላል:: የወንጌል ስርጭቱ ዕለት የውይይቱ አካል ሊሆን ቢችልም፣ ጉዳዩን ሰፋ አድርጎ መመልከቱ ቤተ ክርስቲያን የወንጌል ስርጭት ተካፋይ የምትሆንበትን መንገድ ለማወቅ ፈጠራ የታከለበትን አሳብ ለማብላላት ያስችላል:: ገንዘብ ለማሰባሰብ ከዚህ የተሻለ መንገድ አለ ወይ? አስፈላጊው ነገር ገንዘብ ማሰባሰብ ነው ወይስ ወንጌላውያንን መላክ? ልዩ የገንዘብ ማሰባሰቢያ ቀን ሳያዘጋጁ ወንጌላውያንን ለመላክ የሚቻልበት ሌላ መንገድ ቢኖርስ? ትኩረታችሁን በአንድ የተግባር እርምጃ በገደባችሁ መጠን፣ የፈጠራ አሳቦችን የማግኘት ዕድላችሁም የጠበበ ነው:: ነገር ግን ግቡን ካወቅን፣ ለምሳሌ፣ ግባችን ወንጌላውያንን ወደ ሁሉም አካባቢዎች መላክ ቢሆን፣ ጉዳዩን ከተለያዩ አቅጣጫዎች በመመልከት የተሻለ ውሳኔ ልንሰጥ እንችላለን::*



| |
|---|
| 36ኛ ጥያቄ:- ሀ) አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ ውሳኔ መስጠት ያለበትን አንድ ጉዳይ ጥቀስ:: ለ) የውሳኔው ግብ ምንድን ነው? ሐ) በአንድ የተግባር እርምጃ ላይ ከማተኮር በፊት ግቡን ግልጽ ማድረጉ የተሻለ ውሳኔ እንድትሰጥ አስችሎሃል? መልስህን አብራራ:: |

ችግር በሚኖርበት ጊዜ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪው መፍትሔ ከመፈለጉ በፊት የችግሩን መንሥኤ መፈለግ አለበት:: ብዙውን ጊዜ ለአንድ ጉዳይ ጊዜያዊ መፍትሔ ልንሰጥ ብንችልም፣ የችግሩን ምንጭ ስለማናደርቅ፣ እንደገና ተመልሶ ይመጣብናል:: ውሳኔዎች የቅርቡን ሁኔታ ብቻ ሳይሆን፣ የችግሮቹን ምንጭ ጭምር መዳሰስ አለባቸው:: ጥሩ ውሳኔ የሚባለው ምርጥ የአጭር ጊዜ ውጤት ያለው ሳይሆን፣ ምርጥ የረዥም ጊዜ ውጤት ያለው ነው::

*ለምሳሌ፣ እንበልና ወጣቶች በፈለጉት መንገድ እንዲያመልኩ ስላልተፈቀደላቸው ሽማግሌዎቹ በመንፈስ ቅዱስ ስላልተሞሉ ነው ከዚህ ውሳኔ ላይ የደረሱት የሚል ወቀሳ ይሰነዝራሉ:: ለዚህ ችግር መፍትሔ ለማምጣት ተጠርተሃል እንበል:: በዚህ ጊዜ ሁለቱን ቡድኖች ሰብስበህ ስለ አንድነት ስብከት ልታደርግና ይቅር እንዲባባሉ ልትጠይቃቸው ትችላለህ:: ይህ ግን ችግሩን ሳይፈታ ይችላል:: ወጣቶቹን፣ «ምንድን ነው የምትፈልጉት?» ብለህ ልትጠይቅና፣ «አዲስ ኪቦርድና የድምጽ ማጉያ ተገዝቶልን ሙዚቃውን ጮክ አድርገን ማምለክ እንፈልጋለን» ሊሉ ይችላሉ:: በዚህ ጊዜ ወደ ሽማግሌዎች ዘወር በማለት ለወጣቶች እነዚህ ነገሮች ሊደረጉላቸው እንደሚገባ ልትመክራቸው ትችላለህ:: ነገር ግን ይህ በሽማግሌዎችና በወጣቶች መካከል የተፈጠረውን ችግር ሊፈታ ይችላል? ወጣቶቹ ሽማግሌዎች አይሰሙንም፣ የቤተ ክርስቲያንን አሠራር በተመለከተ የእኛን አሳብ የሚሰማ የለም የሚል አስተሳሰብ ካላቸውስ? ሽማግሌዎቹ ወጣቶች በቂ እውቀት የላቸውም ብለው ይንቁናል የሚል አስተሳሰብ ካላቸውስ? የችግሩ ምንጭ እስካልደረቀ ድረስ፣ ሽማግሌዎቹ የተባሉትን የሙዚቃ መሣሪያዎች ቢገዙ እንኳን፣ በአጭር ጊዜ ውስጥ በሽማግሌዎቹና በወጣቶቹ መካከል ሌላ ችግር መፈጠሩ የማይቀር ነው:: ስለዚህ፣ መጀመሪያ ሁለቱን ቡድኖች ለማስታረቅ የተጠቀምንበት ጊዜ*

*መከኗል ማለት ነው:: ይህም የሆነው የችግሩን ምንጭ ሳንመለከት ጊዜያዊ መፍትሔ በመስጠታችን ነው::*

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አንድን ችግር ለመፍታት ጥረት በሚያደርጉበት ጊዜ፣ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ማንሣት ይኖርባቸዋል:-

ሀ. አንድን የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ወይም መርሕ እየጣስን ነው ወይ?

ለ. ይህ ውሳኔ በችግሩ ሳቢያ የተጎዱትን ሰዎች ችግር ይቀርፋል ወይ?

ሐ. ሕዝቡ መፍትሔው ተግባራዊ እንዲሆን ድጋፍ ይሰጣሉ ወይ?

መ. ውሳኔው ሌሎችን ችግሮች ሊፈጥር ይችላል?

ሠ. ውሳኔው ወደፊት ችግሩ ተመልሶ እንዳይመጣ ይከላከላል?

ረ. ይሄኛው መፍትሔ ከሌሎች መፍትሔዎች የሚሻለው ለምንድን ነው?

37ኛ ጥያቄ:- ሀ) መሪዎች የችግሩን ሥር የማያጠፋ ውሳኔ በመስጠታቸው ምክንያት ችግሩ በተደጋጋሚ የተከሰተበትን ሁኔታ ግለጽ:: ለ) ሁለት አብያተ ክርስቲያናት ጸብ በመፍጠር ላይ ናቸው እንበል:: ይህን ችግር በተመለከተ ላይ ላዩን ብቻ ላይሆን መሠረታዊ ችግሮችን ለማወቅ የምታነሣቸው ጥያቄዎች ምን ምንድን ናቸው?

6. መሪው ወይም ቦርዱ አያሌ አማራጭ መፍትሔዎችን መዘርዘር አለበት:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በችኮላ አንዱን መፍትሔ ከመረጡ፣ ይህ ጉዳዩን ከተለያዩ አቅጣጫዎች የመመልከት ችሎታቸውን ይገድበዋል:: የተመረጠውም መፍትሔ ብዙውን ጊዜ ውጤታማ አይሆንም:: ነገር ግን መሪዎች ዓላማቸውን ለማሳካት የሚያስችሉትን አያሌ አማራጮች ከዘረዘሩ በኋላ፣ እያንዳንዱን መፍትሔ በመመርመር ከሁሉም የተሻለውን ሊመርጡ ይችላሉ::



አንዳንድ መሪዎች ከቡድን ጋር በሚሠሩበት ጊዜ ዓበይት ውሳኔዎችን ለመስጠት የሚፈልጉት በሚከተለው መንገድ ነው:- ችግሩ በግልጽ ከተብራራ ወይም የተፈለገው ዓላማ ከተወሰነ በኋላ፣ መሪው በቦርዱ ወይም በኮሚቴው ውስጥ ያሉት ሰዎች ምርጥ ነው ወይ? ብለው ሳያስቡ በፍጥነት ይሆናል ያሉትን መፍትሔ እንዲሰጡ ይጠይቃል:: እያንዳንዱ ሰው የሚናገረው ነገር (በጊዜው ጥሩ መስሎ ባይታይ እንኳን) ይጻፋል:: ሁሉም የፈጠራ አሳቦች (አንዳንድ ምክንያታዊና ምክንያታዊ ያልሆኑት ጭምር) ተዘ ረዝረው ካለቁ በኋላ፣ ቡድኑ እያንዳንዱን መፍትሔ ተራ በተራ ይመረምራል:: ጥሩ መፍትሄዎች አይደሉም የተባሉት ወዲያውኑ ይወገዳሉ:: ነገር ግን እዚህ ጋ ቡድኑ ጥንቃቄ ማድረግ አለበት:: ምክንያቱም መጀመሪያው ላይ የማያረቡ የሚመስሉ አሳቦች ወደ በኋላ ጠቃሚዎች ሆነው ሊገኙ ይችላሉ:: በመጨረሻው ላይ ቡድኑ መፍትሔዎቹን ወደ ሁለት ወይም ሦስት ምርጥ አሳቦች ያወርዳል::

7. መሪው ወይም ቦርዱ የመፍትሔዎቹን አዎንታዊና አሉታዊ ገጽታዎች በመመርመር ዓላማዎቹን ከሁሉም በተሻለ ሁኔታ የሚያሳኩትን ወይም መሠረታዊውን ችግር የሚቀርፉትን አሳቦች ይመርጣል:: የውሳኔው ትኩረት በጊዜያዊ ጉዳዮች ላይ ሳይሆን፣ በዘለቄታዊ መፍትሔዎች ላይ መሆን አለበት::

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሚጋፈጧቸው አብዛኞቹ ውሳኔ ዎች ወይም ችግሮች ዘለቄታዊ ተጽዕኖ የሚያስከትሉ ናቸው::

የቤተ ክርስቲያን መሪው አሁን ችግሩን ከቀረፉ በኋላ እስከፊ መዘዝ ከሚያስከትሉት መፍትሔዎች ይልቅ ዘለቄታዊ ውጤት በሚያመጡት ላይ ማተኮር አለበት:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ቀላል በሚመስሉ ውሳኔዎችም ላይ ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው:: ውሳኔው ቀላል ቢሆን ኖሮ፣ እስከ የቤተ ክርስቲያን መሪው ድረስ መምጣት አያስፈልገውም ነበር:: ውሳኔው ቀላልና ግልጽ የሚመስል ከሆነ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪው ችግሩን በጥልቀት አልተመለከተም ማለት ነው:: ውሳኔውን ውስብስብ የሚያደርጉትን አስከትሎቶች በሙሉ አላጤነም ማለት ነው::

ውሳኔው የቅርብ ጊዜ ጉዳዮችን የሚመለከት ከሆነ፣ መሪው ጥብቅና የተረጋገጠ ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል፡፡ ነገር ግን ውሳኔው ወደ ፊት የሚመጡትን ረዥም ጊዜያት የሚመለከት ከሆነ፣ በኋላ የተሻለ ውጤት ሊያመጡ ይችላሉ የሚባሉ መፍትሔዎች ሁሉ ሊዘረዘሩ ይገባል፡፡ መሪውም በውሳኔው ላይ ተለማጭነትን ማሳየት አለበት፡፡ የወደ ፊቱን የሚያውቅ እግዚአብሔር ብቻ ነውና፡፡

መሪዎች ልንለውጥ የማንችላቸው አንዳንድ ችግሮችም መኖራቸውን መገንዘብ አለባቸው፡፡ ውሳኔ የሚያሻቸውን ጉዳዮች በምንመለከትበት ጊዜ፣ በእኛ አቅም መፍትሔ ሊያገኙ የሚችሉትንና ከእግዚአብሔር በቀር ሌላ ሰው መፍትሔ ሊሰጥ የማይችላቸውን ችግሮች ለይተን ማወቅ አለብን፡፡ ለአንድ መሪ ሊፈታ ስለማይችላቸው ችግሮች ብዙ ማሰቡ ጊዜ ማባከን ነው፡፡ መሪውና ቦርዱ ጉዳዩን በጸሎት ለእግዚአብሔር አሳልፈው ሊሰጡና በሌሎች ሊፈቱ በሚችሏቸው ጉዳዮች ላይ ትኩረት ሊያደርጉ ይገባል፡፡

8. ምርጥ ነው የተባለው መፍትሔ ከተመረጠ በኋላ፣ በረዥም የጊዜ ሂደት ውስጥ ሊያስከትል የሚችለው ችግር ካለ እንደገና ማጤኑ አስፈላጊ ነው፡፡ ብዙውን ጊዜ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የአጭር ጊዜ እፎይታ ቢሰጥም በኋላ ችግር ይፈጥራል የሚል ግንዛቤ ይዘው ውሳኔዎችን ለማሳለፍ የሚገደዱባቸው ጊዜያት አሉ፡፡ ይህ በሚሆንበት ጊዜ የሚፈጠሩትን ችግሮች በመለየት ችግሮቹን ለመቀነስ የሚቻልባቸውን መንገዶች መወሰን አለባቸው፡፡

*ለምሳሌ፣ በአውራጃው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሰላም ለመፍጠር በማሰብ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪው በአንድ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንድ ወንጌላዊ ይመድባል፡፡ ነገር ግን ለአንድ ቤተ ክርስቲያን ወንጌላዊ ከተመደበ፣ ሌሎችም አብያተ ክርስቲያናት ለእኛም ይመደብልን እንደሚሉ ያውቃል፡፡ ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ጥያቄውን በሚያነሡበት ጊዜ በቂ ወንጌላውያን እንደሌሉት ወይም አካባቢው ትልቅ ትኩረት የሚሰጠው እንዳልሆነ በመግለጽ ወንጌላዊ ላይመድብላቸው ይችላል፡፡ ይህ ግን የሰዎቹን ስሜት በመጉዳት ወደ ክፍፍል ሊመራቸው ይችላል፡፡ እንዲህ ዓይነት ቤተ*



*ክርስቲያንን የሚከፋፍሉ የአድልዎ ወቀሳዎችን ለመከላከል፣ አስተዋይ መሪ ጥረት ያደርጋል፡፡ ወይም ደግሞ ለአንድ አካባቢ ወንጌላዊ በሚመድብበት ጊዜ ለሌሎች ምን ዓይነት መልስ እንደሚሰጣቸው አጥብቆ ያስባል፡፡ ወይም ደግሞ ፍትሐዊና ጥያቄዎች ምላሽ የሚያገኙበትን መመሪያ ያዘጋጃል፡፡ ይህም ሰዎች ግሰሰቡ ለአንድ አካባቢ አያዳላ አይደለም ብለው እንዲያስቡ ያደርጋቸዋል፡፡*

9. መሪው ወይም ቦርዱ ውሳኔ የሚፈልጉትን ጉዳዮች እንደ አስፈላጊነታቸው ቅድሚያ መስጠት አለበት፡፡ መሪዎች በፍጥነት መፍትሔ ማግኘት ያለባቸውንና ያንን ያህል አስፈላጊ ያልሆኑትን ጉዳዮች መለየት አለባቸው፡፡ አስተዋይ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በዓበይትና አጣዳፊ ጉዳዮች ላይ ጊዜያቸውንና ትኩረታቸውን በማሳረፍ፣ ያን ያህል አስፈላጊ ያልሆኑትን ጉዳዮች የሚፈቱበትን ሌላ ዘዴ ያስባሉ፡፡ ብዙም አላስፈላጊ የሆኑትን ጉዳዮች በአጀንዳው ላይ ወደ ኋላ በማድረግ ለመፍታት ጊዜ እንዳላቸው ወይም ለሌላ ቀን ማስተላለፍ እንዳለባቸው ይወስናሉ፡፡

መሪው ወይም ቦርዱ ዓበይትና አነስተኛ ጉዳዮችን በአንድ ስብሰባ ላይ ማስተናገድ ካለባቸው፣ አነስተኛ ጉዳዮችን በፍጥነት ፈትተው ቢያልፉ የተሻለ ነው፡፡ ሰዎች ለትንንሽ ጉዳዮች ብዙም ሳይጨነቁ ውሳኔ ሰጥተው ሊያልፉና በአስቸጋሪ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡ እዚህ ላይ መሪው ጥንቃቄ ማድረግ አለበት፣ ምክንያቱም ሰዎቹ በአነስተኛ ጉዳዮች ላይ እየተወያዩ ረዥም ጊዜ ከወሰዱ፣ ዋናው ጉዳይ በሚመጣበት ሰዓት ሊደክማቸው ይችላል፡፡ መሪው አጀንዳውን ለመጨረስ ከመጣደፍ ይልቅ፣ የቤተ ክርስቲያኒቱን ዐበይት ችግሮች በቅጡ ለመፍታት መጣር አለበት፡፡ በመሆኑም፣ መሪውና ቦርዱ ከአነስተኛ ጉዳዮች ይልቅ ወሳኝ በሆኑት ጉዳዮች ላይ ጊዜያቸውንና ጉልበታቸውን ማዋላቸውን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡ ብዙውን ጊዜ የቤተ ክርስቲያን ስብሰባ ጊዜ የሚያልቀው ሪፖርቶችን በመስማትና ለመዘምራን ልብስ ስለ መግዛት እና ስለ መሳለሉት ጉዳዮች በመከራከር ነው፡፡ ይህ ማኅበረሰቦቻችንን እንዴት በወንጌል እንድረስ? የሚሉትን

ዓይነት ዋንኛ ጉዳዮች እንሥተን እንዳንወያይ ያግደናል። ብዙውን ጊዜ የጥሩ ውሳኔ ጠላት አላስፈላጊ ለሆኑት ጉዳዮች ብዙ ጊዜ መውሰድ ነው።

> 38ኛ ጥያቄ:- ሀ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በወርሐዊ ስብሰባዎቻቸው ላይ የሚነጋገሩባቸውን አምስት ነገሮች ዘርዝር። ለ) ለእግዚአብሔር መንግሥት ካላቸው ጠቀሜታ አንጻር ለእነዚህ ነገሮች ከአንደኛ እስከ አምስተኛ ያለውን ደረጃ ስጥ። እነዚህ አምስት ነገሮች ለእግዚአብሔር መንግሥት አስፈላጊ የሚሆኑት እንዴት ነው? ሐ) ከእነዚህ አምስት ነገሮች ላይ፣ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ብዙ ጊዜያቸውን የሚያጠፉት ስለ የትኞቹ በመነጋገር ነው? ይህ ጥሩ ነው ወይስ አይደለም? መልስህን አብራራ።

*10.* *መሪው ወይም ቦርዱ አስቸጋሪ ውሳኔ ከገጠመው፣* ብዙውን ጊዜ ጉዳዩን በመከፋፈል በክፍል በክፍል መወሰኑ እና መመልከቱ ጠቃሚ ነው። ለምሳሌ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ስለ ወንጌል ስርጭት የሚነጋገሩ ከሆነ፣ ይህ ሰፊ ርእሰ-ጉዳይ ነው። ስለሆነም፣ ርእሰ-ጉዳዩን በሚከተሉት ዓይነት ሦስት ወይም አራት ክፍሎች መከፋፈሉ ጠቃሚ ይሆናል። ሀ) የወጣቶች የወንጌል አገልግሎት፣ ለ) የማኅበረሰብ የወንጌል አገልግሎት፣ ሐ) የአካባቢ የወንጌል አገልግሎት፣ መ) ብሔራዊ የወንጌል ስርጭት ፕሮግራም። ይህ በእያንዳንዱ አካባቢ ላይ ግልጽ ዕቅዶችን ለማውጣት ያስችላል። በትላልቅ ጉዳዮች ላይ የሚቀርቡ ብዙ አሳቦች በሚኖሩበት ጊዜ፣ በየትኛውም ጉዳይ ላይ ዕቅድ ማውጣቱ አስቸጋሪ ይሆናል።

*11.* *ውሳኔውን ተግባራዊ ለማድረግ ቁርጠኛ አቋም ካልያዝን፣* የትኛውም ውሳኔ ለውጥ ሊያመጣ አይችልም። ውሳኔዎች ከተሰጡ በኋላ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በጥንቃቄ ኃላፊነቶችን ለሰዎች በመወከል የትግበራ ሂደትን መጀመር አለባቸው። ይህ ካልሆነ፣ ውሳኔው ከውሳኔነት አልፎ እውነታ ሊሆን አይችልም። ይህ ውሳኔውን ለመስጠት የተሰባሰቡትን ሽማግሌዎች ጊዜ ከማባከኑም በላይ፣ ጉዳዩ እልባት ባለማግኘቱ ምክንያት ወደ ፊትም እንዲሰባሰቡና ተጨማሪ ጊዜ እንዲያጠፉ ያስገድዳቸዋል። እያንዳንዱ ውሳኔ መጠናቀቅ ያለበት ማን ተግባራዊ



እንደሚያደርገው በመግለጽ መሆን አለበት። ለምሳሌ፣ *«ጊታር ላለመግዛትና ወንጌላዊ ለመላክ ተስማምተናል። ወንድም እገሌ ወደ መዘምራኑ በመሄድ ለምን ጊታር ላለመግዛት እንደ ወሰንን አብራራላቸው። ከዚያም፣ ከወንጌላውያን ጋር በመሆን አንድ ወንጌላዊ መርጣችሁና አሠልጥናችሁ ላኩ። በሚቀጥለው ስብሰባ ላይ ስለ አፈጻጸሙ ለሁላችንም ሪፖርት ታቀርብልናለህ፣» ማለት ይቻላል።*

12. ብዙውን ጊዜ የቤተ ክርስቲያን መሪ ወይም ቦርድ ከሚሰጣቸው ውሳኔዎች አንዱ የገንዘብ አጠቃቀምን የሚመለከት ነው። በአብዛኛው የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ገንዘብ የሚያወጡት አስፈላጊ ነው ለሚሉት ጉዳይ ነው። እንግዳ ቢመጣባቸው፣ ምግብ ለማዘጋጀት የቤተ ክርስቲያንን ገንዘብ ይጠቀማሉ። ወይም ደግሞ ስለ ወንጌል ስርጭት አንድ ልዩ ስብከት ከተዘጋጀ፣ ሽማግሌዎች ከቤተ ክርስቲያን የመባ ገንዘብ ለዚህ አገልግሎት ያውላሉ። የዚህ ዓይነቱ መስጠት ከሚያስከትላቸው ችግሮች አንዱ ከቤተ ክርስቲያን ገንዘብ አብዛኛው ያን ያህል አስፈላጊ ወይም ስልታዊ ላልሆኑ ወጪዎች መዳረጉ ነው። ከዚያ በኋላ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለአንድ አስፈላጊ ነገር ገንዘብ በሚፈልጉበት ጊዜ፣ ሊያገኙ አይችሉም።

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እግዚአብሔር በባለአደራነት የሰጣቸውን ገንዘብ በአስተዋይነትና ሚዛናዊነት ባለው መንገድ ለመጠቀም ከፈለግን፣ አጠቃቀሙን በተመለከተ ዕቅድ ማውጣት ይኖርብናል። ዕቅድን አስቀድሞ ማውጣት «በጀትን መወሰን» በመባል ይታወቃል። የገንዘብ አጠቃቀማችን ብዙም ዕቅድ እንደማናወጣ ወይም ቅድሚያ የምንሰጣቸው ነገሮች ምን ምን እንደ ሆኑ ያሳያል። አብዛኛው የቤተ ክርስቲያን ገንዘብ አስፈላጊ ነው ለምንለው ነገር የማይውል ከሆነ፣ በአፋችን አስፈላጊ ነው የምንለውን ነገር በልባችን አስፈላጊ ነው ብለን እናምንም ማለት ነው። (ለምሳሌ፣ የወንጌል ስርጭት አስፈላጊ ነው ልንል እንችላለን። ነገር ግን ገንዘባችን በሙሉ የሙዚቃ መሣሪያ በመግዛቱ ላይ የሚውል ከሆነ፣ ይህ የወንጌል ስርጭት ለእኛ ያን ያህል አስፈላጊ አለመሆኑን ነው የሚያሳየው።)

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በጀት በሚወስኑበት ጊዜ የሚከተ ሉትን ነገሮች ማስታወስ አለባቸው:-

ሀ. ቤተ ክርስቲያኒቱ ከአሥራትና መባ ምን ያህል ገንዘብ እንደምታገኝ አስቀድማ ልታውቅ ስለማትችል፣ ትክክለኛ የበጀት ዕ ቅድ ማውጣቱ አስቸጋሪ ነው:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ምን ያህል ገቢ ሊገኝ እንደሚችል ለመገመት ያለፈውን ዓመት የቤተ ክርስቲያኒቱን ገቢ እንደ መነሻ መጠቀም አለባቸው:: ካለፈው ዓመት ያነሰ ወይም የበለጠ ገንዘብ እንደሚገኝ ለማወቅ ደግሞ የቤተ ክርስቲያናቸውን ዕድገት ማጤን አለባቸው:: የአካባቢው ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ በቤተ ክርስቲያኒቱ ላይ ምን ያህል ተጽዕኖ ሊያስከትል እንደሚችልም ማሰብ ይኖርባቸዋል:: ለምሳሌ፣ ለገጠር ቤተ ክርስቲያን በአካባቢው የጤፍ ወይም የቡና ዋጋ ካለፈው ዓመት ከፍ የሚል ከሆነ፣ ቤተ ክርስቲያኒቱ ገቢዋ እንደሚያድግ ልትገምት ትችላለች:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እነዚህን የአካባቢ ሁኔታዎች ካጤኑ በኋላ፣ ምን ያህል ገንዘብ ከአሥራትና መባ ሊገኝ እንደሚችል ሊገምቱ ይችላሉ:: መሪዎች ይህንን በጸሎት ማድረግ አለባቸው:: እንዲሁም ደግሞ ሕዝቡ የበለጠ እንዲሰጥ እግዚአብሔ ር እንዲያነሣሣው በመጠየቅ በእምነት ማከናወን አለባቸው::

ለ. መሪዎች በሚቀጥለው ዓመት ምን ያህል ገንዘብ እንደሚኖራቸው ከገመቱ በኋላ፣ በዚያው ዓመት ገንዘብ የሚጠይቁትን ነገሮች መዘርዘር አለባቸው:: ይህ የሚከተለውን በሚመስሉ ምድቦች ሊከፋፈል ይችላል:: 1) ለአንግዶች፣ 2) ለሕንጻ፣ 3) ለወንጌል ስርጭት፣ 4) ለደቀ መዝሙርነት፣ 5) ለወጣቶች፣ 6) ለደመወዝ፣ 7) ለቢሮ ወጪዎች፣ 8) ለጉዞ፣ ወዘተ. . .

ሐ. የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ገንዘብ የሚያውሉባቸው የቤተ ክርስቲያን ወጪዎች በሙሉ ከተዘረዘሩ በኋላ፣ ዝርዝሩን በመከለስ ለእነዚህ ጉዳዮች ገንዘብ ለማዋል ሁሉም ይስማሙ እንደ ሆነ ማረጋገጥ ያሻል:: ያን ያህል አስፈላጊ ባለመሆናቸው ወይም ከሌላ ምንጭ ገንዘብ የሚያገኙ በመሆናቸው ከቤተ ክርስቲያን



ገንዘብ ወጪ የማያስፈልጋቸው ነገሮች ካሉ፣ እነዚህ ነገሮች ከዝርዝሩ መውጣት አለባቸው::

መ. በመቀጠል የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ገንዘብ የሚያስፈልጋቸውን ነገሮች በአስፈላጊነታቸው ቅደም-ተከተል ማስፈር አለባቸው:: በሚከተለው መስፈርት መሠረት ቅደም-ተከተ ሉን መሥራት ይኖርባቸዋል:-

1) እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያናቸው ውስጥ ሊያደርግ የሚፈልገውን ነገር ለማከናወን እጅግ ስልታዊ የሆኑ ነገሮች የትኞቹ ናቸው? መሪዎች በትምህርት ዘጠኝ ስበሳል ቤተ ክርስቲያን አስፈላጊዎች ናቸው ያልናቸውን ነገሮች ማስታወስ አለባቸው::

2) የቤተ ክርስቲያኒቱ አገልግሎት እንዲቀጥል ለማድረግ የሚያስፈልጉ ነገሮች የትኞቹ ናቸው? ለቤተ ክርስቲያን እድገት ቀዳሚውን ስፍራ ባይዙም፣ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችም አሉ:: እነዚህ የቤተ ክርስቲያንን ሕንጻ እንደ መጠጋገን ያሉ ሥራዎች ሊሆኑ ይችላሉ::

3) ገንዘቡ የሚያስፈልገው መቼ ነው? መሪዎች የረዥም ጊዜ ግባቸውን ከአጭር ጊዜ ፍላጎቶቻቸው ጋር ማመጣጠን አለባቸው::

4) መሟላት ያለባቸው የገንዘብ ጉዳዮች የትኞቹ ናቸው? መሪዎች ቤተ ክርስቲያን አገልግሎቷን እንድትቀጥል መከፈል ያለባቸውን ወጪዎች (ለምሳሌ፣ የሠራተኞች ደመወዝ፣ ውኃ፣ መብራት፣ የሕንጻ ጥገና፣ ወዘተ . . .) ማስታወስ አለባቸው::

ዝርዝሩ የግድ መፈጸም «ያለባቸውን እና መሪዎች ጌታ ገንዘብ ከሰጠን እናደርጋቸዋለን ብለው «ተስፋ የሚያደርጓቸውን» ነገሮች ለይቶ ማሳየት አለበት:: ተስፋ የሚደረጉት ነገሮችም እንደ አስፈላጊነታቸው ቅድሚያ ሊሰጣቸው ይገባል:: በእመዛኙ በጣም አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች አስቸኳይ ነገሮች አይመስሉም:: ነገር ግን ለእነዚህ ነገሮች በጀት ካልተመደበ እውን ሊሆኑ ስለማይችሉ፣ እጅግ አስፈላጊዎቹ የቤተ ክርስቲያን ጉዳዮች በጭራሽ እውን

ሳይሆን ይቀራሉ ማለት ነው:: ሰይጣን ገንዘባችንን ከረዥም ጊዜ እጅግ ጠቃሚ ነገሮች ይልቅ ለአጭር ጊዜ ችግሮች እንድናውል ይፈልጋል::

ሠ. ቤተ ክርስቲያን በመጭው ዓመት ምን ያህል ገቢ ሊኖራት እንደሚችል ከገመቱ በኋላ፣ መሪዎች ለእያንዳንዱ የአገልግሎት ዘርፍ ምን ያህል ገንዘብ መመደብ እንደሚያስፈልግ መስማማት ይኖርባቸዋል:: ይህ ማለት ብዙውን ጊዜ የተለያዩ አገልግሎቶች የሚፈልጉትን ያህል ገንዘብ አያገኙም ማለት ነው:: ነገር ግን የቤተ ክርስቲያኒቱን ግቦች ለመምታት የሚያስችል የተወሰነ ገንዘብ ይሰጣቸዋል::

*ለምሳሌ፣ ሽማግሌዎች ለቤተ ክርስቲያናቸው የመጭውን ዓመት በጀት በመሥራት ላይ ናቸው::*

*ሀ. ካለፈው ዓመት መዝገባቸው አባላት በአማካይ በወር 200 ብር አስራትና መባ መስጠታቸውን ተገነዘቡ:: ነገር ግን በዚህ ዓመት ሁለት ቤተሰቦች ቤተ ክርስቲያናቸውን ስለ ተቀላቀሉና የአካባቢው ኢኮኖሚ ካለፈው ዓመት የተሻለ መሆኑን በመረዳታቸው በአማካይ በወር 300 ብር፣ በዓመት ደግሞ 3600 ብር ከእያንዳንዱ አባል እንደሚያገኙ ገመቱ::*

*ለ. ከዚያም በሚቀጥለው ዓመት የሚገጥሟቸውን ወጪዎች ዘረዘሩ:-*

*1) ለወንጌላዊ ደመወዝ:- 150 ብር (150 X 12=1800 ብር)*

*2) ለበላይ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደራዊ አካል የሚሄድ ልገሳ:- በወር 25 ብር (12 X 25=300 ብር)*

*3) ለመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ክፍያ:- በወር 75 ብር (75 X 9 = 675 ብር)*

*4) ለቤተ ክርስቲያን ጣሪያ ጥገና:- 200 ብር*

*5) ለደቀ መዝሙርነት ፕሮግራም መጀመሪያ:- 200 ብር ለመጻሕፍት መግዣ*

*6) አዲስ የመዘምራን ልብስ ማሰፊያ:- 1000 ብር*



*7) አዲስ ጊታር:- 2000 ብር*

*8) ሌሎች ሃይማኖቶችን በሚከተሉ ሰዎች መካከል ለሚያገለግል ወንጌላዊ ደመወዝ:- በወር 50 ብር (600 ብር)*

*9) ለሽማግሌዎች ስብሰባ ምግብ:- በወር 20 ብር (240 ብር)*

*10) ለእንግዶች ምግብ:- በወር 20 ብር (240 ብር)*

*ሐ. ቤተ ክርስቲያን የሚያስፈልጋት ገንዘብ (7255 ብር) ከአባላት እናገኛለን ተብሎ ከታሰበው የ3655 ብር ብልጫ ስላለው፣ ሽማግሌዎች ዝርዝሩን በመከለስ «የግድ» መኖር ያለባቸውን ወጪዎች መለየት አለባቸው:: የወንጌላውያን ደመወዝና የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ክፍያ የግድ መፈጸም እንዳለባቸው ግልጽ ነው:: የቤተ ክርስቲያኒቱ ሕንጻ ጣሪያም ቢሆን፣ ዝናብ በሚኖርበት ጊዜ ሰዎች በሰላም እንዳያመልኩ እያደረገ በመሆኑ፣ መጠገን አለበት:: ይህ ማለት «የግድ» መኖር ያለባቸው ወጪዎቻቸው 2675 እንዲሆን ያደርጋል:: ቀሪ 925 ብር ይኖራቸዋል ማለት ነው::*

*መ. ከዚያ በኋላ የእግዚአብሔርን መንግሥት ለማስፋፋት «ስልታዊ» ጠቀሜታ አለው ብለው ከሚያምኑት ነገር የቀረው የትኛው እንደ ሆነ ይመለከታሉ:: የመዘምራን ልብስን፣ ደቀ መዝሙርነትንና ወደ ሌሎች ሃይማኖት ተከታዮች መድረስን በሚያነጻጽሩበት ጊዜ፣ ደቀ መዝሙርነትና የሌሎች እምነት ተከታዮችን መድረስ አስፈላጊ መሆናቸውን ያምናሉ:: በዚህ ጊዜ 800ውን ብር ለደቀ መዝሙርነት ይመድቡና ወንጌላዊውን ለመርዳት ይወስናሉ:: ከዚያም 125 ብር ይቀራቸዋል::*

*ሠ. ለበላይ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ገቢ የማስገባት ግዴታ ስላለባቸው፣ 125 ብር ለመስጠት ይወስናሉ::*

*ረ. ለሽማግሌዎችና ለእንግዶች የምግብ ወጪ ማድረግን በተመለከተ፣ ከቤተ ክርስቲያን ገንዘብ ከመውሰድ ይልቅ፣ ሽማግሌዎቹ በየተራ ለሻይ ቡናና ለቀላል ምግብ ከኪሳቸው ለመክፈል*

*ይስማማሉ:: ለእንግዶችም እንዲሁ ከቤተ ክርስቲያን ከማውጣት ይልቅ ሽማግሌዎች በየተራ በቤታቸው ለማስተናገድ ይስማማሉ::*

*ለ. የኳየሩን ልብስና ጊታር በተመለከተ፣ ሽማግሌዎች በልዩ መባ ለኳየሩ ልብስ ለመግዛትና ጊታሩን ደግሞ በቀጣዩ ዓመት ልዩ መባ አሰባስበው ለመግዛት ወሰኑ::*

*እንዲህ ዓይነቱ የበጀት ምደባ የግድ መከናወን ያለባቸውን ተግባራት እውን ለማድረግ፣ እንዲሁም ቅድሚያ ትኩረት ለሚያሻቸውና ስልታዊ ለሆኑት ነገሮች ገንዘባችንን እንድናውል ያስችለናል:: ያን ያህል ጠንካራ ስልታዊ እሴት ለሌላቸው የሰዎች ፍላጎቶች ማሟያ የተለያዩ የፈጠራ ዘዴዎችን እንጠቀማለን::*

| |
|---|
| 39ኛ ጥያቄ:- ሀ) የበጀት ምደባ ዘዴ ባለመጠቀማቸው መሪዎች የቤተ ክርስቲያንን ገንዘብ ተገቢ ባልሆነ መንገድ እንዲባክን ሲያደርጉ የተሰመለከትክበትን ሁኔታ ግለጽ:: ለ) 1) በሚቀጥለው ዓመት ቤተ ክርስቲያናችሁ ገንዘብ ልታወጣባቸው ይገባል የምትላቸውን ነገሮች ዘርዝር:: 2) ከተዘረዘሩት ነገሮች መካከል «የግድ» መከናወን ያለባቸውን እና «አስፈላጊ» የሆኑትን ለይ:: 3) ከዚያም ቅድሚያ ትኩረት የሚያሻቸውን ነገሮች በማስቀደም ዝርዝሩን አዘጋጅ:: 4) 5000 ብር ቢኖርህ፣ ገንዘቡን እንዴት ታብቃቃዋለህ? ሐ) በጀቱን በዚህ መንገድ ማዘጋጀት ምን ዓይነት ጥቅሞች እንዳሉት ግለጽ:: |

13. ትክክለኛ ያልሆኑ ወይም የተሳሳቱ ውሳኔዎችን በምታደርግበት ጊዜ ምን ይከሰታል? ማንም ሰው ይሳሳታል:: በአብዛኛው ስሕተት የሚፈጠረው ትክክለኛ መረጃ ባለማግኘታችን፣ በመቸኮላችንና ለውሳኔያችን ግድየለሽ በመሆናችን፣ ወይም ያልተጠበቀ ነገር ሲከሰት ነው:: አንድ መሪ እሳሳታለሁ ብሎ የሚፈራ ከሆነ፣ ምን ጊዜም ውሳኔ ሊሰጥ አይችልም:: ከዚህ ይልቅ፣ ሌሎች ውሳኔ እንዲሰጡ ይገፋፋቸውና ችግር በሚፈጠርበት ጊዜ ውሳኔ የሰጡትን ሰዎች ይወቅሳል:: እንዲህ ዓይነቱ ሰው መሪ ነው ማለት አይቻልም:: መሪ ውሳኔ መስጠትና ለውሳኔው ኃላፊነቱን መውሰድ አለበት:: ሰው እስከ ሆነ ድረስ፣ ሊሳሳት እንደሚችል አስቀድሞ ያውቃል:: ነገር ግን ስሕተቶቹን ከመፍራት ይልቅ፣ እነዚያ ስሕተቶች እንዲያድግ የሚረዱት መሆናቸውን መረዳት



ይኖርበታል:: መሳሳቱ የተሻሉ ውሳኔዎችን እንዲያደርግ ያስተምሩታል:: እግዚአብሔር ታላቅ በመሆኑ ስሕተቶችን ለክብሩ እንደሚጠቀም ይገነዘባል::

አንድ መሪ ለስሕተቶች ወይም ለደካማ ውሳኔዎች የሚሰጠው ምላሽ ስሕተቶቹ እንዲያድግ የሚያግዙት ወይም እርሱንና አመራሩን የሚያዳክሙ መሆናቸውን ያሳያል:: ከዚህ በታች አንድ መሪ ደካማ ውሳኔ ሲያደርግ ወይም ሲሳሳት ምን ማድረግ እንዳለበት የሚያስታውሱ ዓበይት እውነቶች ተዘርዝረዋል:: (ማስታወሻ:- ከእነዚህ አሳቦች አብዛኞቹ ባሕላችን እንድናደርግ የሚያስተምረን አይደሉም:: ነገር ግን እግዚአብሔር መሪዎች ትሑት የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች እንዲሆኑ እንደ ተናገረ ማስታወስ አለብን:: ትሑት አገልጋይ የሚጨነቀው ለራሱ ሳይሆን ለእግዚአብሔር መንግሥት ብቻ ነው:: መሪ እግዚአብሔር የቤተ ክርስቲያንን አመራር አገልግሎት በሸክላ ዕቃ ውስጥ እንዳኖረ (2ኛ ቆሮ. 4:7) ስለሚያውቅ፣ ደካማና ሊሳሳት የሚችል መሆኑን ይገነዘባል::)

ሀ. የቤተ ክርስቲያን መሪዎች መሳሳታቸውን እንዳወቁ፣ ትክክለኛ ውሳኔ አለመስጠታቸውን አምነው መቀበል አለባቸው:: ይህ በጣም አስፈላጊ ነው:: አንድ መሪ ስሕተት መሆኑን እስካልተገነዘበ ድረስ እርማት መውሰድ አይጀምርምና:: አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ ስሕተቶቹን አምኖ ሳይቀበል በሚቆይበት ጊዜ፣ ውሳኔው ጎጂነቱን እየጨመረ ሊሄድ ይችላል::

ለ. መሪ ለተፈጠረው ስሕተት ኃላፊነቱን መውሰድ አለበት:: መሪ እስከ ሆነ ድረስ ዋናው ኃላፊነት የእርሱ ነው:: ስለሆነም፣ ጉዳዩን ለሌላ ሰው በውክልና አስተላልፎ ቢሆን እንኳን፣ ግለሰቡን በአግባቡ መከታተል የእርሱ ተግባር በመሆኑ፣ ዞሮ ዞሮ ስሕተቱ የራሱ ነው:: የአገልግሎታችን ክፍል ውክልና ወስዶ የተባረከ ተግባር በሚያከናውንበት ጊዜ የክብሩ ተካፋይ እንደምንሆን ሁሉ፣ የወቀሳውም ተካፋይ መሆን አለብን:: የተወከለው ግለሰብ የተሰጠውን መመሪያ ችል ብሎ በዐመፅ መንፈስ ሥራውን አስካላከናወነ ድረስ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪው ኃላፊነቱን መውሰድ

አስበት፡፡ መሪው ማንንም ሳስመውቀስ ጥንቃቄ ማድረግ አስበት፡፡ ስሕተቱንም ለመደበቅ መሞከር የለበትም፡፡ ከቁጥጥሩ ውጭ የሆነ አንድ ያልተጠበቀ ነገር እስካልተፈጸመ ድረስ፣ ብዙ ማመኻኛዎችንም መደርደር የለበትም፡፡ አንድ መሪ በጥሩ ሁኔታ ላላከናወናቸው ተግባራት ኃላፊነት የማይወስድ ከሆነ፣ ከስሕተቶቹ ሊማር ወይም ባሕርዩን ሊያሳድግ አይችልም፡፡ ስሕተቱ ከፍተኛ ሊሆንና በዚሁ ምክንያት የተጎዱ ሰዎች ብዙ ሲሆኑ፣ መሪው በይፋ ጥፋቱን መግለጽ አስበት፡፡

ሐ. ችግር በሚፈጠርበት ጊዜ፣ መሪው ችግሩ ያስከተለውን የአደጋ መጠን መገምገም እሰበት፡፡ ውሳኔው የጎዳው አንድን ሰው ነው ወይስ ብዙ ሰዎችን? መሪው የደረሰውን ጉዳት ሳያጋንን ወይም ሳያሳንስ በትክክል መገምገም እሰበት፡፡ ጉዳቱን ምን እንደ ሆነ እስካላወቀ ድረስ ችግሩን ለማስወገድ ዕቅዶችን ሊያወጣ አይችልም፡፡ ብዙ ሰዎች የተጎዱ እንደ ሆነ፣ መሪው ጉዳቱን ለማስቆም እርምጃ መውሰድ አሰበት፡፡ ውሳኔው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ክፍፍልን ከፈጠረ፣ ችግሩ መመለሻ የሌለው ከመሆኑ በፊት መፍትሔ ማግኘት እሰበት፡፡

መ. ስሕተት ብዙውን ጊዜ ጥሩ የመማሪያ መሣሪያ ነው፡፡ ነገር ግን ስሕተት የመማሪያ መሣሪያ ሊሆን የሚችለው ስሕተቱ ለምን እንደ ተፈጠረና ችግሩ ምን እንደ ነበረ ለማወቅ ጊዜ ወስደን ስናስብ ነው፡፡ ስለሆነም፣ አንድ መሪ የማይረባ ውሳኔ በሚሰጥበት ጊዜ፣ የስሕተቱን ምክንያት መመርመር አሰበት፡፡ ዝም ብሎ ሌሎችን የሚወቅስ ከሆነ፣ ሊያድግ አይችልም፡፡ የተሳሳተበትን ምክንያት ለማወቅ የማይሞክር ከሆነም፣ እንደገና ያንኑ ስሕተት ይደግመዋል፡፡ አንድ ጊዜ መሳሳት ሰው የመሆን እውነታ በመሆኑ፣ ማንም እንደ ትልቅ ችግር አያየውም፡፡ ነገር ግን ከስሕተታችን ሳንማር ቀርተን ደጋግመን የምናጠፋ ከሆነ፣ ሰዎች ለሁለተኛ ጊዜ ይቅርታ ለማድረግ ሊቸገሩ ይችላሉ፡፡ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሚከተሉትን ጥያቄዎች በማንሣት ከስሕተቶቻቸው ሊማሩ ይችላሉ፡-



1) ስሕተቱ የተፈጠረው መሪው ባለው መረጃ ከሁሉም የተሻለ ውሳኔ ለመስጠት በሚጥርበት ጊዜ የተሳሳተ ብይን በመስጠቱ ምክንያት ነበር? እንዲህ ከሆነ፣ መሪው የጥፋተኝነት ስሜት ሳይሰማው ችግሩን እንዴት እንደሚያስተካከል ማሰብ አሰበት፡፡ ምክንያቱም የሚችለውን ጥረት አድርጓልና፡፡

2) ችግሩ የተከሰተው ጥሩ ዕቅድ ባለመውጣቱ ምክንያት ነበር? እንዲህ ከሆነ፣ ዕቅዱ ጥሩ ያልነበረው፣ ሀ) መሪው ውሳኔውን ለመስጠት በቂ ጊዜ ባለመውሰዱ ነበር? ለ) ክትትሉን ለማጠናቀቅ የሚያስፈልገውን ጊዜና ጉልበት በትክክል ባለመገመቱ ይሆን? ሐ) ከእርሱና ከሌሎችም ሰዎች አቅም በላይ በመሆኑ ነበር? መ) ተገቢውን ክትትል ባለማድረጉ ነበር? ሠ) ሰዎችን በትክክል ባለማሠልጠኑ ምክንያት ነበር? ወይስ ረ) መሪው ነገሮች በተጠበቀው መንገድ በማይሄዱበት ጊዜ የሚጠቀምበት አማራጭ ዕቅድ ስላላዘጋጀ ይሆን? እንዲህ ከሆነ፣ መሪው የተፈጠረውን ችግር ለማስተካከል ጥረት በሚያደርግበት ጊዜ የተሻለ ዕቅድ ለማውጣት መጣር አሰበት፡፡

3) ስሕተቱ የተፈጠረው መሪው ጥሩ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችል በቂ መረጃ ስላልነበረው ነበር? ይህ ሰዎች መረጃ በመደበቃቸው ወይስ መሪው ጊዜ ወስዶ መረጃዎችን ለማሰባሰብ ባለመጣሩ ምክንያት የተፈጠረ ችግር ነበር? ትክክለኛ መረጃ ያላገኘ እስተዋይ መሪ የእርሱን ያህል አስተዋይነት ሳይኖረው ትክክለኛ መረጃ የያዘውን ሌላ መሪ ያህል ጥሩ ውሳኔ ሊሰጥ አይችልም፡፡

4) ስሕተቱ ትክክለኛ ካልሆነ ውክልናና ክትትል የመነጨ ነበር? ወይስ ሠራተኛው ለነፍ ወይም መመሪያዎችን የማይከተል የመሆኑ ውጤት ነው? ወይስ ሰዎች አብረው እንዳይሠሩ ያደረገ ጸብ ወይም አለመተማመን ነበር?

5) ችግሩ ከአቅም በላይ ወይም የተሻለ ውጤት ማግኘት የሚቻልበት ነበር? ችግሩ ከአቅማችን በላይ ከሆነ፣ ራሳችንን ብዙ መውቀስ የለብንም፡፡ ነገር ግን እኛ ልንቆጣጠረው የምንችል

ከሆነ፣ ለምን ችግሩ እንዳይፈጠር ጥረት አላደረግንም? በሚቀጥለው ጊዜ የተሻለ ውጤት የምናመጣው እንዴት ነው?

መሪው ለእነዚህ ጥያቄዎች ምላሽ ከሰጠ በኋላ፣ ራሱን በመውቀስ ጉልበቱን ማባከን የለበትም። በሚቀጥለው ጊዜ እንዴት የተሻለ ተግባር እንደሚያከናውን ለመማር ከውድቀቱ መረጃ መውሰድ አለበት።

ሠ. የቤተ ክርስቲያን መሪው ለስሕተቱ ትልቅ አስተዋጽኦ ያደረገውን ምክንያት ማወቅ አለበት። መሪው ስሕተት የተፈጠረበትን ምክንያት (ወይም ምክንያቶች) ካወቀ በኋላ፣ በሚቀጥለው ጊዜም ተመሳሳይ ችግር እንዳይፈጠር ለመከላከል በእነዚህ ምክንያቶች ላይ መሥራት አለበት። ባለፈው ጊዜ ጥሩ ውክልና ካልሰጠ፣ ለወደ ፊት በዚህ ጉዳይ ላይ ጥንቃቄ ማድረግ አለበት። የችግሩ ምክንያት ሌላ ከነበረም፣ ለዚሁ ምክንያት መፍትሔ መፈለግ አለበት።

ረ. የቤተ ክርስቲያን መሪው ያስተላለፈው ጥሩ ያልሆነ ውሳኔ የሚያስከትላቸውን ችግሮች ለመቀነስ ጥረት ማድረግ ይኖርበታል። ተሳስቻለሁ ማለቱ ብቻ በቂ አይደለም። ነገር ግን የውሳኔው አሉታዊ ተጽዕኖዎች እንዳይስፋፉ በፍጥነት የማረሚያ እርምጃዎችን መውሰድ ይኖርብናል።

ሰ. የተሳሳተውን ውሳኔ በለጠን ጊዜ ለማድረግ የፈለግነውን ውጤት የሚያመጣ አዲስ የተግባር ዕቅድ ማውጣት አለብን። ዕቅዳችንን ለማሳካት የመረጥነው አንድ መስመር ካላዋጣን፣ ሌላ መንገድ መምረጥ አለብን። ይህንን ውሳኔ በፍጥነት በመስጠት ሰዎች እርማት ለማድረግ መጣራችንን እንዲያውቁ ማድረግ አለብን። ነገር ግን ሰዎች ውሳኔ የመስጠትና የመሪነት ችሎታ የለውም ብለው አመኔታ እንዳያጡ ጥሩ ውሳኔ መስጠት አለብን። አዲሱ ዕቅድ ተግባራዊ በሚሆንበት ጊዜ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪው ጥንቃቄ የተሞላበትን ክትትል በማድረግ መሪዎችና ምእመናን የሚፈልጉትን ውጤት ለማምጣት መጣር ይኖርበታል።



ግልጽ ሆነን ስሕተት መሥራታችንን በምንቀበልበት ጊዜ፣ ሰዎች ከበፊቱ የበለጠ ያከብሩናል። ሰዎች በመሆናችን ልንሳሳት እንደምንችል ይገነዘባሉ። ብዙውን ጊዜ ጥሩ ያልሆነ ውሳኔ በምንሰጥበት ጊዜ፣ ሰዎች ስለሚያውቁት ስሕተታችንን ደብቀን ብዙ ልንጓዝ አንችልም። ስለሆነም፣ ውሳኔያችን ጥሩ አለመሆኑን በግልጽ በምንቀበልበት ጊዜ፣ ይቅር ብለው አክብሮት ይሰጡናል። ነገር ግን ይህ አክብሮት የሚኖረው 1) ትክክለኛ ውሳኔ ለማድረግ መጣራችንን ሲያውቁ፣ እና 2) እኛም ከስሕተታችን ስንማርና ተመሳሳይ ስሕተት የማንደግም እስከ ሆን ድረስ ነው። ይቅርታ ከጠየቁ በኋላ ለውጥ ለማምጣት አለመጣሩ ይቅርታችን ልባዊ እለመሆኑን ያሳያል። ከስሕተታችን የማንማር ከሆነ ደግሞ፣ የቤተ ክርስቲያን ምእመናን ለእኛና ለአመራራችን አክብሮት አይኖራቸውም። ይህ አክብሮት ሳይኖር ደግሞ፣ ቤተ ክርስቲያንን መምራት አይቻልም - ምን እንኳን «የቤተ ክርስቲያን መሪዎች» የሚል ስም ቢሰጠንም።

40ኛ ጥያቄ፡- ሀ) በቤተ ክርስቲያናችሁ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጥሩ ውሳኔ ባለመስጠታቸው ምክንያት የተፈጠረን አንድ ችግር ግለጽ። ለ) የስሕተቱ መንሥኤ ምን ይመስልሃል? ሐ) መሪው ወይም መሪዎች ለተፈጠረው ችግር ጥፋተኞች መሆናቸውን አምነው ተቀበሉ? ካልሆነ፣ ለምን? ከሆነ፣ መሪዎቹ ይቅርታ በጠየቁ ጊዜ የቤተ ክርስቲያን ምእመናን ምን አሉ? መ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከላይ የተሰጡትን ሐሳቦች ቢከተሉ ውጤቱ እንዴት የተሻለ ይሆን እንደ ነበረ ግለጽ።

## አራተኛ ቀን- ለሳምንታዊ ስብሰባ በመዘጋጀት የዚህን ሳምንት ትምህርት ክለስ።

## ሳምንታዊ ስብሰባ

### የውይይት ጥያቄዎች፡-

1. ሀ) በቤተ ክርስቲያን መሪዎች መካከል፣ እንዲሁም በቤተ ክርስቲያን መሪዎች እና በምእመናን መካከል የመተሳሰብና የመዋደድ ሁኔታዎች አሉ? ካልሆነ፣ ለምን? ለ) በመተማመን ላይ የተመሠረቱ ግንኙነቶች እለመኖራቸው በቤተ ክርስቲያናችሁ

ውስጥ ሊኖር በሚገባው ዕድገትና ውጤታማ አመራር ላይ ያስከተለውን ችግር ግለጹ። ሐ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በመካከላቸው በመዋደድና በመተማመን ላይ የተመሠረተ ግንኙነት እንዲኖር ሊያደርጉ የሚችሏቸውን ነገሮች ዘርዝሩ። መ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከምእመናን ጋር በመዋደድና በመተማመን ላይ የተመሠረተ ግንኙነት እንዲኖር ሊያደርጉ የሚችሏቸው ነገሮች ምን ምንድን ናቸው? ሠ) ግንኙነትን ለማሳደግ ያስችላሉ ተብለው በዚህ ትምህርት ውስጥ የቀረቡትን ስድስት መንገዶች ብንከተል፣ ይህ በሰዎች መካከል የሚኖረውን እምኔታ እንዴት ያሳድገዋል?

2. ሀ) የቤተ ክርስቲያናችሁ ሽማግሌዎች ባለፈው ዓመት ለመወሰን የተገደዱባቸውን ሦስት ከባባድ ውሳኔዎች ዘርዝሩ። ለ) በዚህ ዓመት የቤተ ክርስቲያናችሁ ሽማግሌዎች የተጋፈጧቸውን ሦስት አደገኛ ውሳኔዎች ግለጽ። ሐ) የቤተ ክርስቲያናችሁ ሽማግሌዎች በዚህ ዓመት ለመፍታት የተገደዱባቸውን ሦስት ችግሮች ግለጽ። መ) መሪዎች ውሳኔ በሚሰጡበት ጊዜ ማስታወስ ያለባቸውን መሠረታዊ መርሖዎች ከልሱ። እያንዳንዱ መርሕ አስፈላጊ የሚሆነው ለምንድን ነው? መሪዎች ውሳኔ በሚሰጡበት ጊዜ እያንዳንዱን መርሕ ካልተከተሉ ምን ችግር ይከሰታል? ሠ) የተለመዱት ወጥመዶች መሪዎች ጥሩ ውሳኔ እንዳያደርጉ ሲገድቡ የተመለከታችሁት እንዴት ነው?

3. ሀ) ቤተ ክርስቲያናችሁ የተጋፈጠችውን ዓቢይ ውሳኔ ግለጹ። ለ) በእንድ ሁኔታ ውስጥ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ስለ ማወቅ በዚህ ትምህርት ውስጥ የተሰጡትን ነጥቦች በመጠቀም፣ ለዚህ ውሳኔ የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንዴት ማወቅ እንደሚቻል ተወያዩ። ሐ) ብዙ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በእንድ ጉዳይ ላይ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በመሻት በቂ ጊዜ ያሳልፋሉ ብላችሁ ታስባላችሁ? ካልሆነ፣ ለምን? የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ ሳይሞክሩ የተሻለ የሚመስላቸውን ውሳኔ የሚሰጡ ከሆነ፣ ምን ዓይነት አሉታዊ ነገሮች ይከሰታሉ?



4. አንድ መሪ ወይም ቦርድ ጥሩ ውሳኔ ለመስጠት መከተል ያለባቸውን ደረጃዎች ከልሱ። እነዚህ ደረጃዎች ለምን አስፈላጊ እንደ ሆኑ አብራሩ።

# ትምህርት አሥራ ሦስት

## አንደኛ ቀን

ባለፈው ሳምንት የአንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ ውጤታማነት ጥሩ ውሳኔ በመስጠት ክህሎቱ ላይ እንደሚደገፍ አጥንተናል። አንድ መሪ አስቸጋሪ ውሳኔ ለመስጠት የሚፈራ፣ ወይም የቤተ ክርስቲያንን ውሳኔዎች በመምራት ወደ መንፈሳዊ ብስለት እንድትደርስ የማያስችላት ከሆነ፣ እግዚአብሔር የሚጠብቅበትን መንፈሳዊ አመራር እየሰጠ አይደለም ማለት ነው። ከዚህም በላይ የእስተዋይነት ውሳኔዎች መስጠታቸውን ለማረጋገጥ ሌላም አንድ በጣም አስፈላጊ የሆነ ጉዳይ አለ። እነዚህም ቤተ ክርስቲያኒቱን በሚያስተዳድሩ ቦርዶች የሚሰጡ ውሳኔዎች ናቸው። (ማስታወሻ:- ጥሩ የቦርድ ውሳኔዎችን ለመስጠት የሚያግዙ አሳቦች በትናንትናው ትምህርት ውስጥ ቀርበዋል።)

## ጥሩ የቦርድ ውሳኔዎችን እንዴት መስጠት እንደሚቻል

> 1ኛ ጥያቄ:- ሀ) የቦርድ ስብሰባ ተካፍለህ ታውቃለህ? ለ) ከሆነ፣ ቦርዱ የተወያየባቸው ጉዳዮች በቤተ ክርስቲያን ላይ ለውጥ የሚያመጡ ጠቃሚ ጉዳዮች ነበሩ? ሐ) የሽማግሌዎች ቦርድ ዓላማ ምን ይመስልሃል? የአውራጃ ቤተ ክርስቲያን ቦርድ ዓላማስ?

ከቤተ ክርስቲያን ዐበይት ውሳኔዎች ብዙዎች የሚሰጡት በኮሚቴዎች ወይም በቤተ ክርስቲያን ስብሰባዎች አማካኝነት ነው። (ለምሳሌ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ኮሚቴ፣ የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ፣ የዞን የቦርድ ስብሰባዎች፣ ወዘተ. . .) ውሳኔዎችን ለመስጠት ኮሚቴዎችን ወይም ቦርዶችን መጠቀሙ በጣም ውጤታማ ወይም በጣም ጊዜ የሚያባክን ሊሆን ይችላል። ብዙውን ጊዜ ቦርዶች በማይረቡ ጉዳዮች ላይ ሲከራከሩ ጊዜያቸውን ሙጥጥ አድርገው